እ

ኢትዮጵያዊነት!

ታሪካዊ ልብወለድ

አሳምነው ገብረወልድ ደመቀ

1996 ዓ.ም

አሳታሚ ዜጋ አሳታሚና ማስታወቂያ ድርጅት

Publisher Zega Publishing and Advertising Enterprise

Tel. 72-77-91/72-84-96 P.O. Box 24434 - code 1000 Addis Ababa Ethiopia

© ዜጋ ስላታሚና ማስታወቂያ ድርጅት

1996 ዓመተ ምህረት

☎ 72-77-91

✉ 24434 ኮድ 1000

ውጭ ሀገር *Web Page: WWW. Zegaa. Com*

e-mail- Zegaa @ aol. Com

ሀገር ውስጥ E-Mail Address: Zpae @telecom.net.et

ኮምፒዩውተር ግራፊክ ዲዛይነር
ዕጌሬዳ ዓባይ

መግቢያ

እንባቢ ሆይ!

ይህ መጽሐፍ በረጅሙ የኢትዮጵያዊነት ጉዞ ላይ ያንጻበበውን የሰቆቃ ደመናና የፈተና ነበልባል ከተራ ዜጐች ህይወት አንፃር የሚተርክ ነው።

የአቀራረቡ ስልት ታሪካዊ ልብወለድ ነው። የሚነገረው የኢትዮጵያዊነት ስብዕና ትግልና መስዋዕትነት መሠረት የሆኑት አብዛኞዎቹ ጉዳዮች በዓይን ታይተው፣ በጆሮ ተሰምተው፣ በህሊና ተመዝነውና ታሪክ ሆነው ያለፉ ናቸው። ፍትህ የተነፈጉ በመሆናቸው ደግሞ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የመናገር እድል የተሰጣቸው ገፀ-ባህርያት ኤሉሄያቸውን ለትውልድ ያሰማሉ።

ታሪካቸውንና የኢትዮጵያዊነት ልምዳቸውን የሚያወጉን አራት ኢትዮጵያውያን ባለፉት ሠላሳ ዓመታት የተለያየው የህብረተሰብ ክፍል ለኢትዮጵያዊነት የከፈለውን መሰዋዕትነት ያንፀባርቃሉ።

በአጠቃላይ ገበሬው፣ ወታደሩ፣ ምሁሩና፣ የህክምና ባለሙያው ያላቸውን ልምድ በቃሪያነቱ፣በብስለቱና በመራራነቱ እናያለን፤ ከአራቱ መራ ጋር እንጓዛለን።

በአጋጣሚ ካልሆነ በቀር በመጽሐፉ ውስጥ የተጠቀሱት ገፀ ባህርያት ጻድቃንም ይሁኑ ኃጢአን የፈጠራ ሰዎች ናቸው።

አሳምነው ገ/ ወልድ ደመቀ

መታሰቢያነቱ

ይህ መጽሐፍ የትዳር ጓደኝነቷ፣ ምክርና፣ ትዕግሥቷ፣ ፍቅርና የመንፈስ ጥንካሬዋ ለህይወቴ የብረት ዘንግ ለሆነው ባለቤቴ መርከብ ዋቅቶላ ቦኩና ለእናቴ ለዘርጊባቸው ወልደመድህን አዳፍር በመታሰቢያነት የተበረከተ ነው።

ደራሲው ።

«ኢትዮጵያዊነት ስቃይና መከራ ነው፤
ኢትዮጵያዊነት ኩራትና ክብርም ነው።
ኢትዮጵያዊነት ጭቆናና ጥቃት ነው፤
ኢትዮጵያዊነት አሻፈረኝና እምቢባይነትም ነው።»
— ፕሮፌሰር መስፍን ወልደማርያም

«የካም ፀዳል ጀግኖች እናት፣
እምቅድመ ዓለም ፍናት አላት
የዘለዓለም ችቦ ብርሃን፣ የማትሻር ህያውነት፣
ራዕይ ናት ኢትዮጵያዊነት።»
— ባለ ቅኔ ሎሬት ፀጋዬ ገብረመድኅን

«አንቺ አገሬ! ኢጦቢያ ውነት በድየሽ ተሆነ ነፍሴን አይቀበላት። አልበደልሁሽ ተሆነ ወንድ አይብቀልብሽ»
— አባ ኮስትር ደጃች በላይ ዘለቀ ጃንሜዳ ሲሰቀሉ የተናገሩት

አዲስ አበባ ውስጥ አራት ኪሎ በመባል በሚታወቀው ሠፈር አንድ ከሸክላ የተሰራ ሀንፃ አለ። በአጤው ምኒልክ ቤተ–መንግስት በኩል አልፎ ሽቅብ ወደ እንጦጦ በሚወስደው ታላቅ ጐዳና በግራ በኩል፤ በፓርላማው ፊት ለፊት ይገኛል።

ልጅ በነበርኩበት የአጤው ኃይለሥላሴ ዘመን ይህን ህንፃ ሳውቀው «የአርበኞች ህንፃ» ይባል ነበር። ለኢትዮጵያ፣ ለኢትዮጵያውያንና ለኢትዮጵያዊነት ክብር፣ ነፃነትና ህልውና ታላቅ የላብ፣ የደምና የህይወት መስዋዕት ላቀረቡ፤ ራሳቸውን መባዕ ላደረጉ፤ በጦር ሜዳ ውለው የጀግንነት ገድል ላስመዘገቡ የአገር ልጆች መታሰቢያ እንዲሆን የተሠራ ህንፃ ነው።

በዚያው በአጤው ዘመን፣ ሽበቶአቸው በደጋን የተነደፈ ጥጥ የሚመስል፣ መላጣቸው እንደመስታወት የሚያብረቀርቅ፣ አረማመዳቸው እንደ አንበሳ ኩራት የተመላበት አርበኞች ወደዚሁ ህንፃ ሲወጡና ሲገቡ ይታዩ ነበር። በአጋጣሚ በዚሁ ህንፃ ውስጥ ወዳለው መሰብሰቢያ አዳራሽ ወይም ሻይ ቤት ጐራ ለማለት የቻለ ሰውም አንበሶቹ በቆላ፣ በደጋ፣ በበረሃ፣ በዱር ወጥተው ወርደው በአገራቸው በኢትዮጵያ ስም ስለፈፀሙት ጀብዱ በኩራት ሲጫወቱ፣ ሲያስተውሱ፣ በእስተርጅናም እንኳ ዘራፍ ብለው ሲያገሱ ይሰማ ነበር።

አጤ ጃንሆይ ከታላላቅ ሰዎች ጋር ዘብጥያ ወርደው መንበረ–መንግሥቱ በዘመናዊ ሽፍታ ከተያዘ በኋላ «በአርበኞች ህንፃ» አካባቢ አርበኞች አልታዩም። ህንፃው በተለምዶ የ«አርበኞች ህንፃ» ተብሎ መጠራቱ ቢቀጥልም ማን እንደሚያዝበት በውል አይታወቅም። በውል የሚታወቀው አርበኞች ቀደም ሲል በአገር፣ በህብረተሰብና በመንግሥት ዘንድ የነበራቸው ክብር መገፈፉና አርበኛ የሚያሰኛቸው የከበረ ምግባርም መራከሱ ነው።

እንዴት ይሉ ይሆናል።

እንግዲያማ አንባቢ፣ ንሳ አድምጠኝ። ጆሮህን ለአንደበቴ፣ ልቦናህን ከአንደበቴ ለሚወጣው አውስ።

በዚህ በገለጥኩልህ የአርበኞች ህንፃ ሥር ዘወትር ከጠዋት እስከ ማታ ተቀምጦ ከአላፊ ከአግዳሚው፣ ከወፄ ከወራጁ ሰው እጅ ምፅዋት የሚጠብቅ አንድ ከፉኛ የተጐሳቆለ ነዳይ አለ። ከአንደበቱ የልመና ቃል አይወጣም። ሣንቲምም ሆነ ዳቦ ቸረውት የሚያልፉ ሰዎችንም ቢሆን ቀና ብሎ ሲያመሰግን አይሰማም። ላላወቀው ዱዳና ደንቆሮ ይመስላል። ብዙዎችም የሚገምቱት እንዲህ ነው ብለው ነው።

አንገቱ ዘወትር እንዳቀረቀረ፣ ዓይኑም ከፊቱ ካለው አስፓልት ላይ እንደተተከለ ነው። ቀና አይልም። አንገቱን ዞር አድርጐም በአካባቢው የሚሆነውን ለማየት አይጥርም

ከግራ እጁ በቀር ማናቸውም የሰውነት አካሉ ሲንቀሳቀስ አይታይም። ግራ እጁም ቢሆን በእግሩ ላይ ያለውን ቁስል ከዝንብ የመከላከል ግዳጅ ባይኖርበት ኖሮ እንደሌላው አካሉ በድን ይመስል ነበር።

ደግነቱ፣ የግራ እጁ መንቀሳቀስ ዝንብ ከመከላከሉ ሌላ ይህ ነዳይ ህይወት ያለው መሆኑን ለተመልካች ይጠቁማል። ይህ ባይሆን ኖሮ ማዘጋጃ–ቤት ከነነፍሱ ከምን ስርቻ ወስዶ እንደሚጥለው አይታወቅም ነበር። እንዲያው ለትዝብቱ እንጂ ይህ ነዳይ በህይወት የመጨረሻ ምዕራፍ ላይ ያለ በመሆኑ ማዘጋጃ–ቤቱ ወስዶ ቢኮችመው ብዙ የሚያሳማው አይሆንም።

ቀረብ ብሎ ለተመለከተው ነዳዩ የመንቀሳቀስ ፍላጐቱም ሆነ ችሎታው ያለው አይመስልም። የችግርና የበደል እሳት ህይወትና ኑሮውን አመድ ትቢያ አርጐት ያለፈ መሆኑን ግን መላ ቁመናው ይመሰክራል።

የለበሰው ኮት ቀኝ እጀታ ከንዱ ላይ ተቋጥሯል። ይህም ቀኝ እጁን ከክንዱ ላይ ያጣ መሆኑን ያመለክታል። ቀኙ ዱሽ ነው።

ገፁ ቢነኩት የሚንቋቋ የደረቀ አንጋሬ ይመስላል። ወዝ የለውም። ህይወት ያለው የማይመስል የተሞነማጨረና የነጣ ነው።

ምላጭ ከነካው ብዙ ጊዜ የሆነው ሪዙ ድርቅ ወይም ውርጭ ቅጠሉን አራግፎት በጭራሮነቱ ብቻ ገሮ የቀረ ደን ይመስላል። የተቆጣጠረና የተመሰቃቀለ ነው።

በሪዙ መካከል ያሉት ከንፈሮቹ ሲታዩ ከመሰነጣጠቃቸው የተነሳ የደረቀ ወንዝ ይመስላሉ። እንደአጋጣሚ አፉን ከፈት ሲያደርግም ቅጠልያ ጥርሶቹ ወራጅ ውኃ ሸርሽሮት እንዳለፈ አለት ብቅ ይላሉ።

የጉንጮቹ አጥንት ከመግጠጣቸው የተነሳ የአገሬን የቁም አምባን ገደል ይመስላሉ። በእነዚህ ገደሎች መካከል አፍንጫው ሲታይ እንደተራራ የቆመ ነው።

በዚህ ገደል በሚመስል ገፁ መካከል የጐደጐዱ አይኖቹ ሲታዩም የዝንጀሮ ዋሻ ይመስላሉ። አንደኛው የአይኑ ዋሻ በርቀት ላይ ያለ የሚመስል የብርሃን ጭላንጭል ይታይበታል። ሌላው የአይኑ ዋሻ የቀኝ አይኑ ሙሉ በሙሉ ጨለማ ነው። ብርሃን የለውም።

የነዳዩ የቀኝ ዓይን ፈሷል። በግንባሩ ላይም ያለው ቆዳ ከመሸብሸቡ የተነሳ ደማቅ ቅንድቡ የገጠመ ይመስላል።

የራሱ ፀጉር ሦስት ቀለማት አሉት። ጥቁር፣ ነጭና ቀይ ናቸው። ጥቁሩ ከልጅነት ጊዜ ጀምሮ የነበረው የተፈጥሮ ፀጉሩ ነው። ነጩ ደግሞ የእድሜውን መግፋት የሚገልፅና ጥቁሩን እየተካ የበቀለ ሽበት ነው።

ቀዩ ፀጉርሳ ይሉ ይሆናል። አንባቢ በራስህም ሆነ በትውልድህ እንድታየው የማልመኘው ነው። አየህ! ቀይ ፀጉር የጠኔ ምልክት ነው። ረሀብ ከአንጀት አልፎ አእምሮን ማስጨነቅ ሲጀምር የራስ ፀጉር ይቀላል። ይህ በሚሆንበት ጊዜ ረሀብ ረሀብ መሆኑ ይቀርና ጠኔ ይሆናል። ጠኔ የሚባለው ወደ አፍ የሚገባ እህል ጠፍቶ ሰውነት ራሱን በራሱ ሲበላ ነው።

ይህ የእኛ ሰውም፤ በጠኔ ተይዞ በሥርና በጅማት የተሳሰረ ሥጋ–አልባ አፅሙ አንድ–ሁለት ተብሎ ሊቆጠር የሚችል ነው።

የለበሰው የተቀዳደደና ያደፈ ልብስ የሰውነቱን ጉዳት የሚደብቅ አይደለም። ሆኖም ግን ልብሱ ስለሰውየው የሚገልጠው ሌላ ነገር አለ።

ቀረብ ብሎ ለተመለከተው ነዳዩ የለበሰው የተቀዳደደና ያደፈ ልብስ የመኩንን ልብስ ነው። ያውም መኩንኖች የሚለብሱት የዘወትር ልብስ ሳይሆን በበዓል ቀን ለክብር የሚለብሱት አይነት ነው።

በግራ በኩል ካለው የኮቱ ደረት ኪስ ላይ ቀለማቸው የለቀቀ አራት ሜዳልያዎች ተደርድረዋል። ከሜዳልያዎቹ አጠገብ አንድ ኒሻን ተንጠልጥሏል። የኒሻኑ ቀለም አለቀቀም። የወርቅ ኒሻን ነው። ከኮቱ ሁለቱም ትከሻዎች ላይ ሦስት ኮከቦች ተደርድረዋል።

ሜዳልያና ኒሻኖቹ በጦር ሜዳ ለኢትዮጵያና ለኢትዮጵያውያን ክብር ለከፈለው መስዋዕትነት በአድናቆትና በምሥጋና ተሰጥቶት የነበረ ነው። በማየት ብቻ የዋለበት የጦር ሜዳ የት እንደነበር ባይታወቅም፣ የከፈለውን መስዋዕት በክፊል ይገነዘቧል።

ነዳዩ ተፈጥሮ ከለገሰው ጥማድ ጥማድ አካሎቹ አንዳንዶቹ ጉለዋል። አንድ እግር፣ አንድ እጅ፣ አንድ አይን ነው ያለው። አካሉን ቆርሶ ለአገሩ ሰጥቷል።

በትከሻው ላይ ያሉት ሦስት ኮከቦች የሚያመለክቱት የመኩንን ማዕረጉን ነው። ሻምበል ነበር።

ከዚህ በስተቀር ይህ በአርበኞች ሀንፃ ስር የተቀመጠው ነዳይ በርቀትም ሆነ በቅርበት ሲያዩት፣ በአካባቢውና ባለበት ከተማ፣ በአዲስ አበባ ውስጥ ከሚገኙ ሌሎች እልፍ አእላፍ ነዳያን የሚለይበት የለም።

እሱም እንደሌሎች ቀን፣ ህብረተሰብና መንግሥት እንደ አሮጌ ሰፌድ የጣለው ነው። እንደዚህ እንደ ነዳዩ ቁራሽ እንጀራ ለምነው የሚጉርሱ፤ እፍኝ ውኃ ለምነው የሚጠጡ፤ ውሎአቸው በጉዳና፤ አዳራቸው በመቃብር–ቤት የሆነ እያሌ የምድሪቱ ልጆች አሉ።

ሁሉም ባይሆኑ፣ አብዛኞዎቹ እንደዚህ ታሪኩን እንደምናመጣው ነዳይ ያሉት የአገርና የህዝብ ባለውለታዎች ናቸው። ኢትዮጵያዊነታቸውን በመወለድና በመፈከር ሳይሆን በደማቸው ፍሳሽም ያስመሰከሩ ናቸው።

የእነሱም ደም አንተ አንባቢና እኔ የተጠመቅንበት

የኢትዮጵያዊነት የዮርዳኖስ ወንዝ መሆኑን ከወዲሁ ማስታወሱ አይከፋም። በዚህ ወንዝ ያልተጠመቀ አንድም አይድንም፤ አለያም ከዲል እንዲሉ።

ለአገራቸው ውለታ ምላሽ የውርደት፣ የችግርና የበደል መስቀል ተሸክመው የህይወታቸውን የመጨረሻ ምዕራፎች ይጓዙ ዘንድ ከተገደዱት መካከል ስለዚህ በአርበኞች ሀንፃ ስር ስለወደቀው ነዳይ ለምን ላጫውትህ እንደፈለግሁ ቀስ እያልክ ትገነዘበዋለህ።

ተዋወቀው!!

ነዳዩ ወላሌ ዡማነህ ይባላል። ሻምበል ወላሌ ዡማነህ ከጥቂት ዓመታት በፊት «የኢትዮጵያ ጀግና» ተብሎ በመላው ህዝብ ዘንድ ስሙ በኩራት የሚጠራ፣ የሚቀናበትና የሚታፈር ሰው ነበር።

ከ1960 ጀምሮ ኢትዮጵያንና የኢትዮጵያን ህዝብ በወታደርነት ላቡን አንጠፍጥፎ፣ ደሙን አፍሶ፣ አጥንቱን ከስክሶ፣ አካሉን አጉሎ፣ ህይወቱንም እንኳ ሳይቀር ዘብ አቁሞ አገልግሏል።

የሻምበል ወላሌ ዡማነህ ኢትዮጵያዊነት እንደምን በእሳት ነበልባል፣ በጥይት በፈንጅ፣ በፈተና በውጥረት ተፈትኖ የከበረ–ድንጋይ አባት–እንቁነቱን–እንዳስመሰከረ እኔ ላንተ ላንባቢውም ሆነ ለሌላው ሰው በቀላሉ መንገር የምችለው አይደለም።

እውነት እልሃለሁ፣ የጀግናን ገድል ጀግና ሲያወራው ነው የሚያምረው። እኔ ሻምበል ወላሌ ዡማነህን የመሰሉ ጀግኖችና አርበኞች ከዋሉበት ያልዋልኩ ሰው ስለጀግና ልናገር ብል በደንቡ አይቋጭልኝም።

ከእኔ ይልቅ ስለሻምበል ወላሌ ዡማነህ የከበረ ብቻ ሳይሆን ብርቅ ኢትዮጵያዊነት ደሙ የፈሰሰባቸውና አካሉ የተሰዋባቸው የኦጋዴን በረሃ አሸዋዎችና የኤርትራ ተራራዎች፣ ጋራና ሸንተረሮች እንደበት ኖሯቸው ቢናገሩት ይሻላል።

ቀኝ እጁ ከላዩ ተጉምዶ የቀረባት ካራማራ፣ አንድ አይኑ የፈሰሰባት ከረን፣ የእግሩ አጥንት የረገፈባት ምፅዋ

መናገር ቢችሉ ስለሻምበል ወላሌ ማንነትና ምንነት ማስረዳት ይችላሉ።

ይህም ካልሆነ፣ ሻምበል ወላሌ ዠማነህ በአካለ-ሙሉነቱም ሆነ በአካለ-ጉደሎነቱ ለኢትዮጵያ፣ ስለኢትዮጵያና ኢትዮጵያን ብሎ፤ በሰንደቅ-ዓላማ ክብር ኮርቶ፣ ነፃነትና አንድነትን አላስደፍር ብሎ፤ የኢትዮጵያዊነትንም ህልውና አስከብር ብሎ እየመራና እየተመራ ታግሎ ያታገላቸው የትግል ባልንጀሮቹ በህይወት ካሉ እነሱ ስለእሱ ማንነት፣ ኢትዮጵያዊነት ይናገሩ።

አዎ፣ መናገር ቢችሉ ግዑዟ የኢትዮጵያ ምድርና በላይዋ የምትውለበለበው የቃል-ኪዳን ሰንደቅ ዓላማ እንኳ ስለሻምበል ወላሌ ዠማነህ ብዙ ባስረዱ ነበር። እማኝ ናቸው፤ የደም ምስክሩ ናቸው።

ሻምበል ወላሌ ዠማነህ እንደምን ሆኖ አንቱ በተባለበት፤ ስሙ የሽለላና የፉከራ ቤት መምቻ በሆነበት፤ የአዛውንት-የባልቴት መመኪያና መኩሪያ፤ የወጣቶችም መቅኛ በሆነባት አገር የኋላ ዘመኑን እንዲህ በችግር ተቆራምዶ፣ በብስጭት ጋይቶ፣ በውርደትም ተገንዞ ያሳልፍ ዘንድ አውራ ጐዳና ላይ እንደተጣለ ለመገንዘብ እንድትችል ታሪኩን ከስር-መሰረቱ ከአልፋው ጀምሬ አመጣዋለሁ።

ከዚህ ከወደቀበት አስከፊ ቦታም አንስቼ የህይወቱ መጀመሪያ ወደሆነው አገርና አምባም እወስደዋለሁ። በዚያም ላጫውትህ የምወደው ስለኢትዮጵያው ጀግና ስለሻምበል ወላሌ ዠማነህ ሳይሆን ስለ አብሮ አደጌ፣ ስለባልንጀራዬ፣ የህልም፣ ምኞትና ተስፋ ተቋዳሺ ስለነበረው የመራምባው ተወላጅ ወላሌ ዠማነህ ነው።

ከያ በፊት ግን ታሪኩ አብሮ ሊነገር የሚገባ አንድ እንደ ወላሌ ዠማነህ ቀን፣ ጊዜ፣ አገር፣ መንግሥትና ወገን የጣለው ሌላ ህይወት አለና እሱን ላመጣልህ እወዳለሁ።

ወላሌ ዠማነህ ባለበት በአራት-ኪሎ ላይ አርፎ የነበረ ሀሊናህንም አንቀሳቅስና ተከተለኝ። ከመንግሥት መዲና ራቅ ብሎ ወዳለ ቦታ ይዤህ እጓዛለሁ።

* * *

ከአዲስ አበባ 180 ኪሎ ሜትር ርቆ የሚገኝና በሁለት ወንዞች የታቀፈ ቆላማ አገር አለ። መርሀቤቴ ይባላል። በዚህ አገር ውስጥ አንድ ቆፍና የምትባል የገጠር ከተማ አለች።

በዚህች ከተማ ዙሪያ ያለውን ኮረብታ ጥግ-ጥግ ይዞ ወደዠንበር መጥለቂያ ጥቂት ሲጓዙ ከአንድ ታላቅ ግቢ ይደረሳል።

ይህ ግቢ ቁመቱ አሥር ክንድ ያህል በሚሆን ግንብ ዙሪያውን የታጠረ ነው። በግንቡ ላይ ደግሞ ጉጥ ያለው ሽቦ እየተወሳሰበ ዙሪያውን ተዘርግቷል። በግንቡ አራት ማዕዘኖች ላይ ከቆርቆሮ የተሰሩ አራት ቆጦች አሉ። በእነዚህ ቆጦች ላይ መሣሪያ አነጣጥረው የሚጠብቁ ወታደሮች አሉ። በእያንዳንዱ ቆጥ ላይ ሁለት፣ በጠቅላላ ስምንት ወታደሮች መሆናቸው ነው።

የወታደሮቹ ሥራ ወደዚህ ታላቅ ግቢ የሚገባውን፣ የሚወጣውንና በአካባቢው የሚያገድመውን ሰው እንቅስቃሴ መቆጣጠር ነው። በግቢው ውስጥም ሆነ ውጭ ያልተፈቀደለት እንቅስቃሴ ካዩ ያለምንም ጥያቄ ቃታቸውን ይስባሉ። ቋሚ ትዕዛዛቸው ስለሆነ የቃታቸው መሳብ ያስፈነጠረው ጥይት በሚያደርሰው ጥፋት አይጠየቁም።

ወደዚህ ግቢ የሚያስገባና የሚያስወጣ አንድ የብረት በር በምዕራብ በኩል አለ። ብረት ከታጠቁ ጠባቂዎችና አለቆቻቸው በቀር በአብዛኛው ወደዚህ ግቢ የሚገባ እንጅ የሚወጣ የለም።

በውጭ በኩል፣ ከበሩ ግራና ቀኝ በየቀኑ በፆታውና በእድሜው የተለያየ ብዙ ሰው ይሰበሰባል። ሽማግሌዎች፣ አሮጊቶች፣ ጐልማሶች፣ ኮረዶችና ህፃናት ይታያሉ።

ሁሉም ያዘኑ፣ የተከዙ፣ የተቸገሩ፣ ስለፍትህ ብዙ ያለቀሱ-ፍትህም ብዙ ያፌዘባቸው እንደሆነ ለመረዳት አያዳግትም።

እለት በእለት በዚህ ታላቅ ግቢ የውጭ በር ስር የሚኮለኮሉት ወደግቢው ተጉትተው ገብተው የቀሩ

ልጆቻቸውን፣ አባቶቻቸውን፣ እናቶቻቸውን፣ ወንድምና እህቶቻቸውን– አለያም የአክስትና የአጐቶቻቸውን የደህንነት ወሬ ለመስማት ነው።

አንዳንዶቹ ለእስረኛ ዘመዶቻቸው ጠባቂዎች ይሰጡልናል ብለው ያመጡትን ጭብጦ፣ ድርቆሽ፣ ቆሎ፣ እንጀራና የመሳሰለውን የእስረኛ ምግብ በአገልግል፣ በኮሮጆና በሳህን ይዘዋል።

ተጐትተው ወደዚህ ግቢ የገቡት ዘመዶቻቸው በህይወት መኖርና አለመኖራቸውን፣ ቢኖሩም እንኳ ያመጡትን ምግብ ጠባቂዎቹ ስለማድረሳቸው የሚያውቁት የለም። በተስፋ የሚኖሩ በመሆናቸው ሁሉንም ነገር የሚያደርጉት በተስፋ ነው።

የዚህን ግቢ የውጭ የብረት በር አልፈው ወደ ውስጥ ሲገቡ የእስር–ቤቱን መቀመቅነት ይመሰክሯል።

በቀኝ በኩል፣ ከበሩ አንስቶ እስከ ግቢው ሩብ ድረስ በግንብ የተሰሩ ጠባብ ጠባብ ክፍሎች አሉ። እያንዳንዱ ክፍል ወደውስጥ የሚያስገባና የሚያስወጣ ቀዳዳ አለው።

ወደእነዚህ ጠባብ ክፍሎች የሚላኩት እስረኞች የሚገቡት ተኝተው በቀዳዳው ውስጥ እንደ ውሻ ወይም ድመት እየተሳቡና እየተንሸራተቱ ነው። በህይወትም ሆነ በሞት የመውጣት እድል ያጋጠመው እስረኛ ቢኖር፣ መውጫው በገባበት ሁኔታ ከውስጥ በኩል ተንሸራትቶ፣ ከሞተም ተገፍቶ ነው።

ቀዳዳው ከመውጫና መግቢያ በቀር በሣምንት አንድ ቀን ለእስረኞቹ ሦስት ደረቅ ሽልጦና አንድ ባሊ ውሃም የሚቀበልበት ነው። በእያንዳንዱ ክፍል ውስጥ ከአስር እስከ ሃያ እስረኛ ሊኖር ይችላል። የእስረኛው ቁጥር ይብዛም ይነስ የሚሰጠው ቀለብ ይኸው ነው።

በዚህ በር ወይም መስኮት በሌለው ክፍል የታጐሩት እስረኞች አየር የሚያገኙትም በዚህ ቀዳዳ አማካኝነት ብቻ ነው።

በዚሁ ቀዳዳ አማካኝነት ወደ ውጭ የሚወጣውን የጠረን ድብላቂ ይኼ ነው ብሎ ለመለየት አይቻልም። ሆኖም፣

ጠረንን አሽቶ የመለየትና የመሰየም ችሎታ ያለው ሰው ወይም መሣሪያ ከተገኘ፣ ከድብልቁ ጠረን መካከል አብዛኛው የቁስል፣ የሽንት፣ አይነ–ምድር፣ የላብ ጠረን እንደሚሆን አያጠራጥርም። ሁሉም አንድ ላይ ነው።

ከእነዚህ ጠባብ እስር ቤቶች ቀጥሎ በዚያው በግንቡ ዳር ዳር እስከ ዋናው በር ግራ ድረስ አዳራሽ መሰል እስር ቤቶች አሉ። የእያንዳንዱ አዳራሽ የፊትለፊት አጥር ከብረት የተሰራ ሆኖ የአውሬ ማጐሪያ ይመስላል። ስድስት ኪሎ እንዳለው የአንበሶች ማጐሪያ ዓይነት ነው።

በዚህ አዳራሽ ውስጥ ያሉት ሰዎች የተለያየ አካል በሰንሰለት ታስሯል። እጃቸው፣ እግራቸው፣ አንገታቸው፣ ወገባቸው፣ በሰንሰለት የታሰረ ነው።

በእነዚህ በሁለቱ ዓይነት እስር ቤቶች መካከል አንድ የተለየ እሲር–ቤት አለ።

ከሩቅ ሲታይ እስር–ቤት መሆኑን የሚያሳይ ምንም ነገር የለውም። አጥር፣ ግድግዳ፣ መዝጊያ የመሳሰሉት የማይታይበት እስር–ቤት ነው።

ለጥቆ ሜዳ ነው። ሜዳውን ይዘው ትንሽ ሲራመዱ፣ ከቆርቆሮ የተሰራ የበር መዝጊያ ወድቆ ያያሉ። ይህ መዝጊያ ግን ያለምክንያት ሜዳ ላይ የወደቀ አይደለም።

መዝጊያውን ብድግ ቢያደርጉት ጥልቀቱ ሃያ ክንድ፣ ስፋቱ ደግሞ ሦስት ክንድ የሆነ ጉድጓድ ያገኛሉ።

ይህም መቀመቅ ቢኖር፣ እውነተኛው መቀመቅ ሊባል የሚገባው የጉድጓድ እስር–ቤት ነው። የሚታሰሩበትም በምስጢር፣ በከፍተኛ ጥንቃቄና ጭካኔ በበዛት እጅ የሚጠበቁ «ወንጀለኞች» ናቸው።

በዚህ በጉድጓድ እስር ቤት ውስጥ «ወንጀለኛ» ተብላ በቁም የተቀበረች አንድ ሴት አለች። ወንጀሏ፣ የደርግ መንግሥት ከወደቀ በኋላ የቆመው መንግሥት የወንጀል ሁሉ እናት አድርጐ የቆጠረው «ትምክህተኛነትና ነፍጠኛነት» ነው።

እንዲህ ያለ ወንጀል ስለመኖሩ፣ ቢኖርም እንኳ ይህችን የጉድጓድ እስረኛ የሚያስወነጅል ስለመሆኑና ስላለመሆኑ ከዚህ እሰጥ አገባ፤ በላ ልበልሃ፤ ብለን አታካራ አናነሳም።

አንባቢ፣

በህሊናህ እንዲስተዋል የምፈልገው የጉድጓድ እስረኛዋ ያለችበትን ሁኔታ ነው። ላሁን ይህን ከተገነዘብክልኝ ይበቃል።

ዝግ ብዬ እንደምነግርህ፣ ከእስረኛዋ ጋር የእድሜ ልክ ትውውቅና ቅርበት አለኝ። በዚህም የተነሳ ያለችበትን ሁኔታ የምገልጥልህ ሰውነቴ በአንድ በኩል በቁጣ እንደ ሰደድ እሳት እየጋዬ፤ በሌላ በኩል በጥልቅ ሀዘን ኩፍኝ እንደያዘው እየተንቀጠቀጠ ነው።

ጉድጓዱ አፋፍ ላይ ሆኖ ወደ ውስጥ ሲታይ መጀመሪያ የሚታየው የእስረኛዋ ራስ ነው። ፀጉሯ ተላጭቷል።

ራሷ ብዙ ቦታዎች የተሸረካከተ ስለሆነ ፀጉሯን የተላጩችው በፊላ(ምላጭ) ነው ለማለት ያዳግታል። የጠርሙስ ስባሪ እላጫለሁ እያለ የሸረካከታት ሊሆን ይችላል።

አለያም በምላጭ በወጉ ተላጭታ ለምርቃት ያህል በበትር ወይም በአለንጋ ተፈንክታ ሊሆን ይችላል። ያም ሆነ ይህ፣ ቁስልና የደረቀ ደም ያለበት ራስ ለእስረኛዋ ስቃይ፣ ለዝንቦች ደግሞ ደስታ ሰጥቷል። ከልካይም የላቸው፤ እንዳሻቸው ይቦጠቡጡታል።

የቀጋ ፍሬ ይመስል የነበረው መልኳ በዚህ በታፈነ ጉድጓድ ውስጥ የፀሐይ ብርሃን ተነፍጉት በመቆየቱ ኩፍ ያለ ሊጥ መስሏል። ለምጥ የያዘውን ሰው መልክ ይመስላል።

ከንፈሮቿ ተሰነጣጥቀዋል። አይኖቿ ብርሃን ይኑራቸው አይኑራቸው ለማወቅ አይቻልም። በአበጡ ቅንድቦቿ ተሸፍነዋል። አይኖቿ ዳር ያሉት የፊቷ አጥንቶች ቆዳ የተላላጠ ስለሆነ የቅንድቦቿ ማበጥ በጥፊ፣ በእርግጫ ወይም በሌላ ነገር ተመታ የደረሰ ሳይሆን አይቀርም።

የመጀመሪያ መልኩ ምን እንደነበረ ለማወቅ የማይቻል አፈር የመሰለ የውስጥ ልብስ ብቻ ነው የለበሰችው። እጀታ የሌለው ባለማንጠልጠያ ስስ የውስጥ ልብስ ነው። ብዙ ሴቶች የአገር ልብስ ሲለብሱ ወይንም ለመኝታ ሲዘጋጁ የሚለብሱት ዓይነት ነው።

በሁለት እጆቿ ጉልበቶቿን ታቅፋለች። በታቀፈቻቸው

ጉልበቶቿ ላይ ደግሞ አገጯን አንተርሳለች። እንዲህ ተቀምጣ ወገቧ እልፎ እልፎ ወደፊትና ወደኋላ ሲንቀሳቀስ ይታያል።

ጠጋ ብሎ የተመለከተ፣ እስረኛዋ ጉልበቷን ታቅፋ መቀመጧ ወዳ ያደረገችው አለመሆኑን ይገነዘባል። ሁለት እግሮቿና እጆቿ በአንድነት በሰንሰለት ተከርችመዋል። በዚህም የተነሳ መቀመጥ የምትችለው በዚህ ባለችበት ሁኔታ ብቻ ነው።

መተኛት ብትፈልግ፣ ያላት አማራጭ እጅና እግሯ በአንድነት እንደታሰረ ፍንግል ማለት ብቻ ነው።

እንዲህ ስትሆን ነው በሰውነቷ ላይ የደረሰው ሌላው ጉዳት የሚታየው። ሁለቱም የውስጥ እግሮቿ መልካም ገበሬ ያረሰው ማሳ፣ ወይንም ባለሙያ ሴት የጋገረችው አምባሻ ይመስላሉ። ብዙ ተገርፈዋል። ግርፋቱ ካረፈበት ቦታ ያሉት ቁስሎች ነፍርቀው ደምና ሌላ እንደውኃ ያለ ፈሳሽ ያዝሉ።

ጀርባዋም እንዲሁ በተመሳሳይ መንገድ ተገርፎ ጋራና ሸለቆ መስሏል። ብዙ ቦታዎች ላይ የጀርባዋ ቆዳ እንዳለ ተገፏል። እልፎ እልፎም ከቆዳዋ እልፎ ሥጋዋ ተነስቶ አጥንቷ ተጋልጧል።

አንባቢ!

ይህች ከህይወት ባሻገር፣ ከሞት ወዲህ ባለ ቀጭን የሽግግር ድልድይ ላይ ቆማ ስቃይን የምትተነፍሰው እህት በሙያዋ ነርስ ነች። በዚህ ሙያ የሰለጠነችው፣ ቀድሞ የቀዳማዊ ኃይለስላሴ ዩኒቨርስቲ በኋላ ደግሞ የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ በሚባለው ነው።

ከዚያም ወደ ባህር ማዶ ተሻግራ እስራኤሎች አገር ሀዳሳ ሆስፒታል በሚባል የህክምና ማዕከል የብዙ ወራት ስልጠና አድርጋለች።

ከስልጠናዋ በኋላ፣ ወደ አገሯ ወደ ኢትዮጵያ ተመልሳ የከተማ ምቾት፣ ተድላና ደስታ ሳያምራት ወደየባላገሩ በመጓዝ ከህብረተሰባችን ውስጥ እጅግ የተጐዱትን፣ መንግሥት ማንኛውንም ዓይነት የጤና አገልግሎት የነሳቸውን ዜጐች በማከም ብዙ ዓመታት አሳልፋለች።

መኪና በሚደርስበት ቦታ በመኪና፣ መኪና በማይደርስበት ቦታ ደግሞ በከብትና በእግሯ እየተጓዘች ቁጥራቸው ይህ ነው ተብሎ የማይገመት በኑሮአቸው ድሃና ኋላ ቀር የሆኑ ዜጎችን ከደዌ ፈውሳለች። በብዙ መንደሮች፣ ወረዳዎችና አውራጃዎች የጤና ጣቢያዎችን በማቋቋም፣ ሌላው ቢቀር ህብረተሰቡን ከቀላል በሽታዎች እንዲድንና እንዲከላከል አድርጋለች።

ለዚህም አገልግሎቷ ከአገር ውስጥ ቀርቶ ከውጭው አገር እንደ የዓለም–ጤና ጥበቃ ድርጅት፣ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የዓለም ባንክና ከመሳሰሉት አያሌ ሽልማቶችንና የምሥጋና ወረቀቶችን ተቀብላለች።

የህዝብ የሆነች አንድና ብቸኛ ተንቀሳቃሽ ሆስፒታል ነበረች። ህዝብን ከማገልገልና ህሙማንን ከመፈወስ በቀር በህይወቷ ሌላ ምንም ምኞትና ፍላጐት አልነበራትም።

ለአገልግሎቷና ለድካሟ ከህብረተሰብ፣ ከአገር ወይም ከመንግሥት የጠየቀችው አንዳችም ነገር አልነበረም። ሌላው ቀርቶ ህሙማንን ለመፈወስ የሚያስፈልጋትን የህክምና መሣሪያና መድሃኒቶች እንኳ ከኢትዮጵያ መንግሥት ተቀብላ የማታውቅ ናት።

እንበለ ድካም የኢትዮጵያን ህዝብና ኢትዮጵያን ታገለግል የነበረው በልመና ነው። መድሃኒቱን፣ የህክምና መሣሪያውን፣ የጤና ጣቢያ ማቋቋሚያውን ሌላ የሚያስፈልገውን ወጭ ሁሉ ከውጭ ዜጎች በኤምባሲዎቻቸውና በዓለም–አቀፍ ድርጅቶቻቸው አማካኝነት እየለመነች ነበር የምታመጣው።

የራሷ የሆነ የግል ሀብት፣ ንብረት የላትም። ቤቴ የምትለው እንኳ የላትም። ቤቷ ተንቀሳቃሽ ድንኳን ነው። ከዚህ የተሻለ የኖረችበት ቢኖር አልቤርጐ ነው።

የራሴ ህይወት የምትለው እንኳ የላትም። ህይወቷ የኢትዮጵያ ህዝብ ነበር። መላ ህይወቷን ለዚህ ህዝብ ህሙማን አገልግሎት በረከት አድርጋ የሰጠች ነበረች።

እየህ እንባቢ፣

የዜግነት መመዘኛ ካለ፤ ኢትዮጵያዊነት የሚለካ

ቢሆን፣ ይህች እህት ትክክለኛ ሚዛኑና መለኪያው ነበረች። ኢትዮጵያዊነትን በፍፁማዊነቱ፣ በብፁዕነቱ፣ በክቡርነቱ፣ በድንግልናው የምትመስል እነሆ ይህች እህት ነበረች።

ታዲያ እንደምን ሆኖ ይህች ሴት ጉድጓድ እስር–ቤት ውስጥ ታስራ ሳትሞት በቁሟ ሰውነቷ ይፈራርስ፣ ይበሰብስ– አሳሯም ከኢዮብ ስቃይ እጅግ የከፋ ይሆን ዘንድ ተፈረደባት??

ጥያቄዬን በቀላሉ ልመልስልህ ብችል ኖሮ ምንኛ ደስ ባለኝ ነበር። መልሱን ባውቅ እኔም እፅናና ነበር። ይህችን እህት እያሰብኩ በምፅፍልህ በዚህ ወረቀት ያለማቋረጥ የሚፈሰው እንባዬም ላመል ይገታ ነበር።

ይህ ግን አይደለም።

እየህ እንባቢ፣ ይህች ጉድጓድ ውስጥ የተዘጋባት እህት ዞማለም የሰውሰው ትባላለች። የአንድ አገርና የአንድ መንደር ልጆች ነን። አብሮ አደጌ፣ ባልንጀራዬና፤ ቀደም ሲል እንደነገርኩህ እንደ ወላሌ ዠማነህ የተስፋና የምኞቴም ነፀብራቅ ናት።

በተወለድንበትና ባደግንበት አካባቢ «መራ–ሀኪም» እየተባለች ነው የምትጠራው። መራ–ሀኪም ዞማለም ለተወለደችበት አንድ ተራ ልጅ ብቻ ሳትሆን የተወለደችበት እምባና አገር ህብረተሰብ የተስፋ ሰንደቅም ነበረች። በእርሷ ላይ የደረሰውም ሰንደቁ በሆነችለት ህብረተሰብ ላይ የደረሰው ነፀብራቅ ነው።

* * *

እንባቢ! ንሳ ደግሞ ነርስ ዞማለም የሰውሰው፣ ወይንም እንደአገሬው አጠራር፣ መራ–ሀኪም ዞማለም በእስር ካለችበት ቦታ በእግር አራት ሰዓት ያህል ተጉዞ ወደሚደረስበት መራምባ የተባለ መንደር ልውሰድህ። ከፌጥራ ከተማ ጉን፣ ወደ ፍቼ በሚወስደው መንገድ ዳር ይገኛል።

መራምባ ዙሪያውን በኮረብታዎች የተከበበ የአምስት አባወራዎች መንደር ነው። ከአምስቱ አባወራዎች መካከል

አንደኛው አባወራ ሊያሰኘው የሚችለው ብዙም የለ። ቤተሰብ፣ እርሻ፣ ከብት የመሳሰሉት የሉትም። ያለው ጨለማ ሲመጣ ገብቶ የሚያርፍበት ቤት ብቻ ነው።

ይህ ሰው ጊዜውን የሚያሳልፈው እንደሌሎቹ የመራምባ ሰዎች ቆላ ወርዶ በእርሻ፣ ደጋ ወጥቶ በቁፋሮ ሳይሆን ከጠዋት እስከ ማታ ከመራምባ ኮረብታዎች በአንደኛው ላይ ወጥቶ በመቀመጥ ነው። የሰውየውን ማንነትና አዘውትሮ ከሚቀመጥበት ኮረብታ ጋር ያለውን ግንኙነት ያላወቀ ሰው ሁኔታውን ተመልክቶ እብድ ወይም ቦዘኔ አርጐ ሊገምተው ይችላል። ምንጊዜም ተሟልቶ እረፍትና ደስታ በማይገኝባት የገጠር ዓለም ሰው ለህይወትና ኑሮው ቀን በፀሐይ፣ ሌሊት በኮከብ ሲባክን፣ ሲባዝቅ የዚህ ሰው ተቀምጦ መዋል እብድ ወይም ቦዘኔ ቢያሰኘው አያስገርምም።

ነገሩ ግን ወዲህ ነው።

እየህ አንባቢ፣

ሰውየውን አተኩረህ ብትመለከት የጉልማሳነት ጊዜውን አገባዶ ከአዛውንትነት መዳረሻ ላይ ያለ መሆኑን ትገነዘባለህ። በህምሳዎቹ የእድሜ ገደብ ላይ ይገኛል። ጤንነቱ የተሟላ መስሎ ቢታይም የተዳከመ ሰው ነው። ብዙ የተጉሳሳ፣ መከራን ያየ፣ የሰቆቃ መጋረጃዎች ተደጋግመው የተከፈቱበት እንደሆነ ገጡ ይመሰክራል። ይህም በመራምባ መንደር ሰዎች ዘንድ የታወቀ ነው።

ነዋሪዎቹ እንደሚያውቁት ይህ መራምባ ኮረብታ ላይ ተቀምጦ ጊዜውን የሚያሳልፈው ሰው በመንደሩ የተከበረ፣ የታወቀና አንቴ የተባለ ገበሬ ነበር። የማን ዘር፣ የማን ቤተሰብ እንደሆነም የታወቀ ነው። አባቱ በመራቤቴ በሞላ እረኛ በዘፈኑ፣ ጐረምሳ በቀረራና ሽለላው ስማቸውን ከሚጠራው የአገር ጀግኖች የአንደኛው ልጅ ነው። የጀግና ልጅ።

የራሱ ቤተሰብና ሞቅ ያለ ቤትም ነበረው። ባለሙያ ሚስትና ሁለት ልጆች፤ ወንድና ሴት ነበሩት።

ዛሬ ግን ብቸኛ ነው። ብቸኛ ስለሆነም ነው ኮረብታ ላይ እየወጣ ጊዜውን የሚያሳልፈው። በአእምሮው ላይ ምን

እንደሚመላለስ ማወቅ የፈለገ ሰው ረጋ ብሎ የሰውየውን ዋሽንት ማዳመጥ ይኖርበታል። አዎ! ይህ ሰው ኮረብታ ላይ ተቀምጦ ዋሽንት መንፋት ልማዱ ነው።

የዋሽንቱ ድምፅ ሰውየው ካለበት ቦታ ተነስቶ በሌሎች የአካባቢው ኮረብታዎች እያስተጋባ ወደቆላው ሲወረወር ቆም ብሎ ላደመጠው ጥሪ የሚያስተላልፍ ይመስላል። ጥሪው ግን በአካባቢው ላለ ለማንም ሰው የተደረገ ሳይሆን ከደመና ማዶ፣ ከህይወት ባሻገር ያለ መንፈስ የሚጠራ ይመስላል። የአገሬው ሰውም ይህን ስለሚያውቅ የዋሽንቱን ድምፅ በሰማ ቁጥር በሀዘን አንገቱን እየነቀነቀ በተሰማራበት ጉዳይ ይቀጥላል።

ሰውየው በዋሽንት ድምፅ የሚጠራው አባቱን ሊሆን ይችላል። ከረጅም ጊዜ በፊት አባቱ ከዚሁ ከተቀመጠበት ኮረብታ ላይ በአጤ ንጉሥ ትዕዛዝ በስቅላት ነው የተገደሉት። ለምንና እንዴት እንደሆነ ወደፊት እናመጣዋለን።

ሌላ ሰውየው በቀጭን የዋሽንት ድምፅ የሚጠራው ባለቤቱንም ሊሆን ይችላል። ከጥቂት ዓመታት በፊት ከረሀብ፣ ከጠኔ ትድናላችሁ ተብለው በመንግሥት አስገዳጅነት ሠፈራ በሄዱበት አገር በሞት ተለይታዋለች። ሞቷ ሳይሆን የአሟሟቷ ሁኔታ ህሊናውን ረፍት ነስቶት ያባዝቀዋል። አሶሳ በሚባል የሰፈራ መንደር በእሳት እንደህፃኑ ቅዱስ ቂርቆስ ጋይታ የሞተች መሆኑም ራሱ ሰውየው በአንደበቱ ይነግርሃል። ላሁኑ አንተን አንባቢውን የሰው ሥጋ ሲንጨረጨር ምን እንደሚሸት በማውራት ላውክህ አልሻም።

ሰውዬው በዋሽንት ድምፅ የሚያስታውሰው የተለዩት ወንድና ሴት ልጁንም ሊሆን ይችላል። ወንድ ልጁ እንደአባቱ መልካም ገበሬ ነበር። ታዲያ ምን ያደርጋል መንግሥት ከድሃ ገበሬ ቤቱ ነጥቆ ወስዶ ጦር ሜዳ ማግዶታል። ለብሔራዊ ውትድርና ግዳጅ ተወስዶ ኤርትራ ውስጥ በፈንጅ ተበላሽቷል። ፈንጅው ለቀብር የሚሆን አፅም እንኳ ሳያስቀር አመድ፣ ትቢያ ነው ያደረገው።

ሴት ልጁ ማለፊያ ኮረዳ ነበረች። በሙያዋና በቁንጅናዋ ከዠማ እስከ ወንጭት የተነገረላት፣ ብዙው ለትዳር

የተመኛት። ግን ሠርጓ ተደግሶ ማጉላ ሳትገባ፣ በድንግልናዋ ታላቁ ጠኔ አግዟታል። አንድ እፍኝ ማሽላ፣ አንድ ጥሬኝ ውኃ በጠፋበት በዚያ በታላቁ ጠኔ ዘመን አባት እንደታቀፋት ልጅ ህቅ ብላ አክትማለች።

ይህ ሰው በዋሽንት ድምፅ የሚያስታውሰውና የሚጠራው የቤተሰቡን መንፈስ ላይሆን ይችላል። የእድሜ ልክ ምኞቱ፣ ትግሉና ልፋቱ ከአቅሙ ባሻገር በሆነ ሁኔታ በመፈራረሱ ቀራንዮ እንደተሰቀለው «ኤሎሄ ኤሎሄ፣ ላማሰበቅታኒ» ማለቱ ይሆናል። አለያም የቆየውን የጥንቱን የመራምባን አባቶች መንፈስ እየጠራ ለመጨረሻና ለወሳኝ ትግል ብርታት እንዲሰጡት እየተማፀነ ይሆናል።

አንተ አንባቢ ይህ ሰው ማነው ብለህ ራስክን እንዳታስጨንቅ ላስተዋውቅህ። ቀደም ሲል እንደነገርኩህ እንደወላሴና እንደዞማለም አብሮ አደጌ፣ ባልንጀሬና በመራምባ ውስጥ መሪ–ጌታ በመባል የሚታወቅ ገበሬ ነው። ስሙ እንባቆም ቢሆንኝ ይባላል። ስለኢትዮጵያዊነት ጉዞ ራሱ እንባቆም ያጫውትሃል። ከያ በፊት ግን ለንባብህ እልባት እንዲሆን ስለአራተኛው መራ፣ ታሪኩን ስለሚነግርህና አገር መሪ–ሃይማኖት ብሎ ስለሚጠራው አንድ አጉናፍር በቃሉ ጥቂት ላውጋህ።

* * *

አንባቢ፣ ቆላው አገር መርሀቤቴ የነበረው ሀሊናህን ሰብሰብ አድርግና ና ወደ አዲስ አበባ ለጊዜው አብረኸኝ ተመለስ። ወደ ቦሌ አይሮፕላን ጣቢያ ነው የምወስድህ።

ቀኑ እሁድ ነው። ረፋዳው ላይ፣ በአምስት ሰዓት ገደማ ከለንደን በካይሮና በአሥመራ በኩል አድርጐ የመጣው የኢትዮጵያ አየር መንገድ አርፎ መንገደኞች እየወረዱ ወደ እንግዳ መግቢያው አዳራሽ በመግባት ላይ ናቸው።

ከመንገደኞቹ መካከል አንድ እድሜው ወደ ሃምሳ ዓመት የሚጠጋ ሰው የደስታና የስጋት ነፋስ ሀሊናውን ከወዲያ ወዲህ እያዋዠቀው ለፓስፖርትና ለጉምሩክ ፍተሻ

ቆሟል። ጺሙ በአጭሩ የተከረከመ፣ ረዘም ያለ ቀጭን ሰው ነው። የጺሙ ደመቅ ብሎ መታየት የራሱን በራነት ይሸፍናል። በልጅነቱ ጋሜና ቁንጮው ከነበረበት ቦታ ላይ ያለው ጠጉር እንዳለ ሄዷል።

ይህ ሰው ፍተሻ ወረፋውን በመጠበቅ ላይ እንዳለ ደስታ የሚሰማው ከረጅም ዓመታት በኋላ ወደአገሩ በመምጣቱ ነው። በኢትዮጵያ ውስጥ ስላለፉት የመቅሰፍት ደመናዎች ሰምቷል እንጂ አላየም። በእድሉም ይሁን በብልጠቱ፣ የመቅሰፍት ደመና አንጃቦ የመከራ ዶፉን ከመጣሉ በፊት ከአንዴም ሁለቴ ወደ ፈረንጅ አገር እየሄደ ድኗል።

በዚህ እሁድ ቀን የሚመጣው ከአሜሪካ አገር ነው። ስጋት የሚሰማው ደግሞ እስካሁን ከመቅሰፍት የሰወረው እድሉ ወይም ብልጠቱ ዛሬም ሊገጥመው ከሚችለው ሊያድነው መቻሉን በትክክል አለማወቁ ነው። ወደ አገር ከመመለሱም በፊት ለችግር ከለላ ሊሆኑኝ ይችላሉ የሚላቸውን ሁኔታዎች አመቻችቷል።

የኢትዮጵያ መንግሥት ከውጭ የሚመለሱ አንዳንድ ዜጐቹን ከቦሌ እየተቀበለ ወደ ወህኒ ያግዛል የሚል ወሬ ስለሰማ የአሜሪካ ዜጋ ሆኖ የመጣው በአሜሪካ ፓስፖርት ነው። በሁለመናው ኢትዮጵያዊ በመታወቂያው ግን አሜሪካዊ ነው። ፍራቻው ያለምክንያት አይደለም። አንድ እሱ ከመጣበት አገር «እናት–አገሬ» ብሎ ምንም ሳይጠራጠር የመጣ ሰው ወህኒ እንደወረደ ቀርቷል።

ሌላው ስጋቱ ወደ አገር በተመለሰበት ዘመን እሱ ከተወለደበት አካባቢ የመጡ ሰዎች በመም በመንግሥት እንደበት በተለያየ የጠላትነት ስም እየተጠሩ መወንጀላቸው ነው። ከመወንጀልም አልፈው ብዙዎቹ ጊዜ ከፍ ከፍ ባደረጋቸው የአካባቢ አብሪተኞች በግፍ ተገድለዋል፣ ታስረው ተሰቃይተዋል። እንደእሱ በስደት ያሉትም ቢሆን ከውንጀላው አልዳኑ። «ነፍጠኛ»፣ «ትምክህተኛ» በሚል ወንጀል እየተከነኑ ጦር ይሰበቅባቸዋል።

ከዚህ ሌላ የዚህ ሰው አመጣጥ አገር ናፍቆት፣ ዘመድ

አሳስቦት ለጥየቃ አልነበረም። የአገርም ሆነ የዘመድ ናፍቆትን በስደት ጠበል ተጠምቆ ከራሱ ካስወገደው ብዙ ጊዜ ሆኖታል።

ወደ አገሩ የተመለሰው የልጅነት ጓደኞቹ ብቻ ሳይሆኑ ኢትዮጵያዊነትን ሲያይባቸው የነበሩት ህያው መነጥሮቹ ስለተሰባበሩ ስባሪዎቹን ለመልቀም ነው። ስባሪዎቹን ለመገጣጠም ሲሞክር ደግሞ ብዙ ጣጣ ሊመጣ ይችላል።

ይኸ ሰው ይህን ሁሉ እያሰላሰለ ወደፈታሹ ቀረብ ሲል—

«ፓስፖርት» አለ ፈታሹ

መንገደኛው በእጁ የያዘውን የአሜሪካን ፓስፖርት አስረከበ።

ፈታሹ ፓስፖርቱን አገላብጦ ካየ በኋላ መንገደኛውን ቀና ብሎ ተመለከተ። በስሙና በመልኩ ብቻ ጠላት መስሎ የታየው ይመስላል። አመለካከቱ «እንኳን ደህና መጣህ» የሚል አይደለም። ግልምጫ ይመስላል።

ጥቂት ፓስፖርቱን ካገለባበጠና መንገደኛውን ከተመለከተ በኋላ «ይቆዩኝ» ብሎ ፓስፖርቱን ይዞ ወደ አንድ ቢሮ ሔደ። ቢሮው ውስጥ አንድ አስር ደቂቃ ከቆየ በኋላ ሌላ ሰው አስከትሎ መንገደኛውን ወደ ቢሮ እንዲሄድ በእጁ አመለከተው።

ፈታሹን ተከትሎ የመጣው ሰውና መንገደኛው ቢሮ ከገቡ በኋላ በሩ ተዘጋ።

«ዜግነትህ ምንድነው?»
«ፓስፖርቱ ላይ የሚያነቡት»
«ምን ይላል?»
«አሜሪካዊ»
«ከዚያ በፊት ምን ነበርክ?»
«ኢትዮጵያዊ»
«ብሔርህ ምንድነው?»
«ኢትዮጵያዊ»
«ብሔረሰብህስ?»
«ኢትዮጵያዊ»
«ትውልድህስ?»

«ከመርህቤቴ»
«ቋንቋህ ምንድነው?»
«አማርኛ፣ አረብኛ፣ እብራይስጥ፣ እንግሊዝኛ»
«አማራ ነህ?»
«አይደለሁም»
«አረብ ነህ?»
«አይደለሁም»
«አይሁድ ፈላሻ ነህ?»
«አይደለሁም»
«ታዲያ ማነኝ? ምንድነኝ ትላለህ?»

«ኢትዮጵያን ሊጎበኝ የመጣ በዜግነቱ አሜሪካዊ፣ በትውልዱ ኢትዮጵያዊ የሆነ መንገደኛ»

እንዲህ ዓይነቱ ጥያቄና መልስ ለጥቂት ጊዜ ከቆየ በኋላ ከውጭ አንድ ሌላ ሰው መጥቶ ለጠያቂው በጆሮው የሆነ ነገር ነገረው። መንገደኛው ምን እንደተነገረ አላወቀም። ሆኖም ለእሱ የሚጠቅም መሆኑን ወዲያው ተገንዝቧል።

ጠያቂው ከተቀመጠበት ቦታ ብድግ አለና በፈገግታ «አጉናፍር በቃሉ፣ እንኳን ደህና መጣህ፤ ውጭ ከአሜሪካ ኤምባሲ ሊቀበልህ የመጣ ሰው ስላለ እቃህን ያዝና ግባ» ብሎ አሰናበተው።

መንገደኛው ወደ አገር ከመመለሱ በፊት ከአሜሪካ ኤምባሲ ሰው እንዲቀበለው አመቻችቶ ነበር።

አንባቢ፣ እንግዲህ ይህ ሰው የሦስቱን መራ ታሪክ የሚያጫውትህ አራተኛው መራ ነው። መራ-ሃይማኖት በመባል በትውልድ አገሩ ይታወቃል። አንተ ግን አጉናፍር በቃሉ ብለህ ብትጠራው ይበቃል። ሰውየው አጉናፍርም እኔው መሆኔ ነውና፣ ና በህሊናህ ተከተለኝ። የእነዚህ ታሪካቸውን የምትሰማው ሰዎች ኢትዮጵያዊነት ወደሚጀምርበት አገር ይዤህ ልጓዝ።

የመራ ልጆች

ከብቸና ወዲህ፣ ከሰላሌ ባሻገር፣ ከመንዝ በስተግርጌ፣ ከተጉለት በስተጀርባ ዦማና ወንጭት በሚባሉ ሁለት ወንዞች በእቅፍ ተይዞ ያለው አገር መራቤቴ ይባላል።

ይህ ገደል፣ ጋራ፣ ሸንተረርና ሸለቆ የበዛበት ቆላማ አገር በአብዛኛው ከተጻፈው የኢትዮጵያ ታሪክ ውጭ ሆኖ የቆዬ ነው። የደብተራው ብራናም ሆነ የዘመኑ ምሁር ሉክ አይዘግበውም። ምናልባት ዘግቦት ቢገኝ ከአገዛዝ ጋር በተያያዘ ሁኔታ የጊዜውን ሹም አወድሶ፣ ህብረተሰቡንም ከቁስ–አካል አሳንሶ ነው።

መራቤቴ ከጥንትም ጀምሮ ብራና ፋቂና ቀለም ጠላቂ ደብተራ የማይበቅልበት በመሆኑ፣ ህብረተሰቡ የራሱ የሆነ ታሪክ ዘጋቢ የለውም። ለቡዳ፣ ለምናምንቴ መከላከያ የሚሆን ክታብ የሚፅፍ ደብተራ እንኳ የማይገኝበት አገር ነው።

ከቅርብ ጊዜ ጀምሮ ከተማማ በሆኑ አንዳንድ የመራቤቴ ግዛቶች የአስኳላ ዘር ሳይዘራ አልቀረም። በዚህም ደብተራ ባልበቀለበት እዳሪ አገር ባላስኳላ በቅሎ የአገሩን ታሪክ የህብረተሰቡን ኑሮ በሉኩ ይዘግበዋል የሚል ተስፋ ነበር።

ሆኖም ግን፣ ከቡቃያነትና ከእሸትነት አልፎ ለምርት የበቃ ባላስኳላ እስካሁን በመራቤቴ አልታየም። ቡቃና እሸት የነበረው የመራቤቴ ባላስኳላ የፖለቲካ ጨረባ ነጉዶ፣ የመንግሥትም ጭልፊትና እርኩም እየጠረጠረው፤ የብስጭት እሳት እያጋየው በየእርሻው ቆረቆንዳ፣ በየቤቱ በየደጁና በየወህኒው እመድ ትቢያ እየሆነ ቀርቷል።

ይህ እጣ ያልደረሰው ባለአስኳላም፣ ዘመን ዳግም ከፈጠረው ሄሮድስ አምልጦ በባዕዳን አምባ በባዕድነት ለመኖር ወደ ስደት ወርዷል።

እንዲህም በመሆኑ፣ የገድላማዎቹ አገር ገድላማው መራቤቴ በታሪክ መጣህፍት ውስጥ እንቀጽና ምዕራፍ መያዙ

ቀርቶ በቃልና በዐረፍተ ነገር እንኳ ሳይጠቀስ ታልፏል።

መራቤቴ የታሪክ እመቤት በሆነች አገር በኢትዮጵያ ሲብስ ውላጅ፣ ሲሻል ደግሞ የእንጀራ ልጅ ሆኖ ቆይቷል። ዳሩ ግን አንድን አካባቢና ህብረተሰብ የተፃፈ ታሪክ አለመኖር ታሪክ አልባ ወይም የታሪክ ድኃ አያደርገውም። መራቤቴም አገርና ህብረተሰቡን ሳወቀው የሰፋ ታሪክ ያለው ነው።

እንዴታ! አንባቢ፣

ከተወላጆቹ አንደበት በዘመን አሸንዳ እንደዘረብሩክ ጠበል እየተንቆረቆረ የመጣው የአገሬው የቃል ታሪክ ከህዋ የሰፋ፣ ከውቅያኖስም የጠለቀ ነው።

እንዴ! ደብተራ ቢኖር ብራናው፣ ባላስኳላም ቢኖር ሉኩ ዘግቦ አይዘልቀውም።

ከዚህ አነሳሴ የፍጻሜ ዘመን ትቶ ስላለፈው የብካይ መዘክር ለመንገር ቢሆንም፣ ከቀደመው የመራቤቴ የቃል ታሪክ የሰማሁትን ጨለፍ አድርጌ ከዚህ ፈሰስ ባደርገው የግንዛቤ ህሊናህን ያረጥበዋል። በረጠበ ህሊናህ ላይ ነው ከዚህ ልዘክረው የምወደውን ህይወት ፍሬ መዝራት የምሻው።

እነሆ ተንግዴህም ገድላማው መሬን ከአልፋው ጀምሬ ላምጣው።

የዦማን ወንዝ ከወዲህ ከፍቼ ሰላሌ በኩል ተሻግረህ በመራቤቴ ግዛት ላይ ጥቂት የጉበዝ ምዕራፎች ከተጓዝክ በኋላ ፌጥራ ከሚባል ኮረብታማ ቦታ ላይ ትደርሳለህ። መራቤቴን በአራቱም ማዕዘናት ከቅርብ እስከ ሩቅ ቁልጭ አድርጎ የሚያሳይ ገዥ ቦታ ነው።

ፌጥራ ላይ ቆመህ ወደምሥራቅ ብትመለከት፣ የወንጭትን ወንዝ፣ ደራና ሚዳን ከዚያም ተሻግሮ የጉጃሞቹን አገር ብቸናን ማየት ትችላለህ። በያው በኩል አንገትህን ቀና አድርገህ ካየህም የወረኢሉና የወረሂመኑን ራያ ካራና ግልድሙን ታጥቆ ታየዋለህ።

ወደ ምዕራብ ብትመለከት፣ ከዦማ ባሻገር ከፍቼ እስከ ጅሩ ደጋ ደጋውን ያለውን የኦሮሞን አገር ታየዋለህ።

ዳግመኛም ፌጥራ ላይ ቆመህ ወደ በሜን ብትመለከት

ከዞማ ባሻገር ያለውን የደገኞቹን አገር መንዝን ታያለህ።

እንግዲህ፣ ከአበው እንደበት ሲነገር እንደሰማነው፣ በመራቤቴ የመጀመሪያው ሰው የተፈጠረው በዚህ ዓለምን በሞላ በሚያሳይ ፌጥራ በተባለ ኮረብታማ ቦታ ላይ ነው። በፍጥረት መጀመሪያ ዘመን የነበሩ አበው እንዳወቁትም፣ ዓለም ይህ የጠቀስነው ብቻ ነበር።

ይህ ፌጥራ የተባለ ቦታም ፌጥራ እየተባለ እስከዛሬ ድረስ የሚጠራው የሰው መፈጠሪያ በመሆኑ ነው። ህይወት አንድ ብሎ የጀመረው ከየህ ነው።

በፌጥራ የተፈጠረው የመጀመሪያ ሰውም መራ ይባላል። ከመራ በፊት በመራቤቴ የሰው ዘር አልነበረም።

መራ የመራቤቴዎች አባት፣ የህብረተሰባቸው፣ የሰብዕናቸው፣ በድምሩም የማንነታቸው መሰረት ነው። ዘመንም እህዱ ብሎ የጀመረው ከዚህ ከመራ በኋላ ነው።

መራ በተፈጠረበት ዘመን፣ በዘመን መጀመሪ[...] በሌሎች አገሮችና አካባቢዎችም ሌሎች እንደመራ ያ[...] የትውልድ አባቶች ተፈጥረዋል። እነዚህም በየተፈጠሩበ[...] አካባቢ የትውልድ ሀረጋቸውን ተከለው፣ ህብረተሰባቸው[...] መስርተው ኑረዋል።

ዛሬ መራቤቴ የምንለው አገር የቀደመ ስሙ መራ[...] ቤት ነበር። ይህም የመራ ልጆች ለአባታቸው መታሰቢ[...] እንዲሆን የሰጡት መጠሪያ ነው። የመራ–አገር ማለት ነው[...]

ከጊዜ በኋላ የመጡት የመራ–ቤት ሰዎች አገሩ[...] መራቤቴ ብለውታል። ይህም ትውልድ ከዘመን መጀመሪ[...] እየራቀ በመምጣቱና የአገሩን ስም ከራሱ ህይወትና ኑ[...] ጋር በቀጥታ በማያያዝ ባለአገር፣ ባለርስት ባለቤትነቱ[...] ለመግለፅ ያደረገው ለውጥ ይመስላል።

ባለአገሩም፣ አገርህ የት ነው? ቤትህ ከምና ነው[...] ሲባል መራቤቴ ይላል። ቤትና አገሬ ከመራቤቴ የሆነ የመ[...] ልጅ ነኝ ማለቱ ነው።

የአበው ቃል ትቶት እንዳለፈው፣ መራ ብ[...] ትውልዶችን እስኪያይ ድረስ ረጅም ዘመን በህይወት ኖረዋ[...] በዘመኑም የጊዜውና የኋለኞቹ የመራቤቴ ሰዎች በሰላም[...]

በደስታ ተስማምተውና ተባብረው የሚኖሩበትን ሥርዓት ትቷል።

የዚህም ሥርዓተ መሰረቱ ይህ ነው፦

በመራቤቴ የሚገኙ ኑዋሪዎች ሁሉ በየመንደራቸው እየተሰበሰቡ ከመካከላቸው ሦስት አዛውንትን በኃላፊነት እንዲመሯቸው፣ ህግና ሥርዓት እንዲያስከብሩ፣ የኑዋሪውን የግልና የጋራ የሥራም ሆነ የሌላ የማንኛቸውም ጥረት እንዲያስተባብሩ ይመርጣሉ።

እነዚህ የተመረጡት ሦስት ሰዎችም የመንደሩን «የአዛውንት ሸንጐ» የሚመሩ ይሆናሉ። በመንደሩ ውስጥ የተነሳ፣ የተከሰተ፣ ወይም አሳሳቢ የሆነ ጉዳይ ሁሉ ወደዚህ ወደ አዛውንቱ ሸንጐ እየመጣ ምክርም፣ ብያኔም፣ ቅጣትም ይሰጠዋል።

ሦስቱ «የአዛውንት ሸንጐ» አባላት በማናቸውም ጉዳይ ላይ ውሳኔ የሚሰጡት በአንድነት መክረውና ተስማምተው ነው።

እነዚህ የየመንደሩ «የአዛውንት ሸንጐ» አባላት ደግሞ በአንድነት ይሰበሰቡና ከመካከላቸው ሦስት ሰዎችን የአጠቃላዩ መራቤቴ ህብረተሰብ የበላይ አስተዳዳሪ፣ ኃላፊ፣ መሪና ጠባቂ እንዲሆኑ ይመርጣሉ።

በእንዲህ በአዛውንቱ ሸንጐ የሚመረጡት ሦስት ሰዎችም ከመላው ህብረተሰብ ውስጥ በምግባራቸው፣ በችሎታቸውና በእርዓያነታቸው የላቁ ናቸው። እነሱም የሥልጣን ስም አላቸው።

ከሦስቱ አንዱ መራ–ጌታ የሚል መጠሪያ ይኖረዋል። የመራ–ጌታ ልዩ የሥራ ኃላፊነትም አስተዳደርን በሚመለከት ባሉ ጉዳዮች ላይ ከ«አዛውንት ሸንጐዎቹ» ጋር እየመከረ መወሰን ነው። የበላይ ቢሆንም እንኳ፣ «የአዛውንት ሸንጐዎቹን» ሳያማክርና የጋራ ስምምነታቸውን ሳያገኝ መራ–ጌታ በማናቸውም ጉዳይ ላይ አይወስንም። በዚህም ከእኩዮች መካከል የመጀመሪያ ወይም ሰብሳቢ እንጂ የበላይ አልነበረም።

መራ–ጌታ የሚሆነው ወንድ ብቻ አልነበረም። ሴትም

ተመርጣ መራ–እመቤት ሆናለች፣ ተብላለች።

በ«እዛውንት ሸንጐ» ከተመረጡት ከሦስቱ ሁለተኛው መራ–ሽመል የሚል የሥልጣን ስም ይኖረዋል። መራ–ሽመል የጐበዝ አለቃ ነው። ከውስጥም ሆነ ከውጭ ህብረተሰቡን ለማወክ የሚነሳ እብሪተኛና አመፀኛን መክቶ ከቦታው ያኖረዋል። ህግና ሥርዓት፣ ወግና ባህል ያስፈፅማል። ለዚህም እንዲረዳው ከመራቤቴ መንደሮች በመላ ጐበዝ–ጐበዙን፣ ጠንካራውን እየመረጠ የመራ–ሽመል ሠራዊት ያዘጋጃል።

ለዚህ የመራ–ሽመል ሠራዊት አባልነት የሚመረጥ ጐበዝም በመራ–ሽመል ፊት እየቀረበ «የመራን ቤትና የመራን ልጆች ስኖር በህይወቴ፣ ስሞት በመንፈሴ እጠብቃለሁ፣ ይህን ባላደርግ የመራ ውቃቢ የዶጋ–አመድ ያድርገኝ፤ መሬትም አትረገጠኝ።» ብሎ ይምላል፣ ቃል ይገባል።

በ«እዛውንት ሸንጐ» አባላት የሚመረጠው ሦስተኛው ሰው መራ–ሃይማኖት የተሰኘ መጠሪያ ይሰጠዋል። የዚህ የመራ–ሃይማኖት የሥራ ድርሻም ዳኝነትን፣ የህብረተሰቡን እምነት፣ ወግና ባህል ጥበቃን፣ ታሪክ ሰብሳቢና ነጋሪነትን ይመለከታል። የመንፈስ ጉዳዮች ኃላፊ ነው። የባህል ተንከባካቢና የሥነሥርዓቱም የበላይ ፈጻሚ ነው። ከሁሉም በላይ መራ–ሃይማኖት የሚታወሰውና የሚታወቀው ግን በታሪክ ነጋሪነቱ ነበር። በየዘመኑ፣ በየትውልዱ «መራ–ሃይማኖት እከሌ እንዲህ አለ» እየተባለ ይጠቀሳል።

ከእነዚህ ከጠቀስኳቸው የህብረተሰብ ኃላፊዎችና አገልጋዮች በተጨማሪ አንድ ለህብረተሰቡ እጅግ አስፈላጊ የሆነና ያማከለ ቦታ የሚሰጠውም ሰው ነበር። ይህ ሰው የነበረውን ቦታና ማዕረግ የሚያገኘው እንደሌሎቹ ተመርጦ አይደለም። ከአባት ወደ ልጅ እየተላለፈና እየተወራረሰ ይመጣ የነበር ክብርና ቦታ ነው።

ይህም በህብረተሰቡ ውስጥ መራ–ሀኪም በመባል የሚታወቅ ነው። መራ–ሀኪም ስሙ እንደሚጠቁመው መድኃኒት አዋቂና የህብረተሰቡ ሀኪም ነው። ሥር ነቅሎ፣ ቅጠል መርጦ፣ ቀንና ወራትን ቀምሮ፣ የፀሐይ፣ የጨረቃን

የከዋክብትን አቀማመጥ ሽልጐ ለታመመ ሰው ፍቱን መድኃኒት ይቀምማል።

መራ–ሀኪም ከሚታይ የአካል ቁስል አንስቶ እስከማይታይ የውስጥ አካል ደዌና የአጋንንት መጠናወት ድረስ የማይፈውሰው አልነበረም።

ይህ አይነት ችሎታ የነበራቸው ሰዎች ችሎታና እውቀታቸውን እያወረሱ የሚያልፉት ለልጆቻቸው ነው። እንዲህም በመሆኑ ከሌሎች በተቃራኒ መራ–ሀኪምነት በዘር የሚተላለፍ ክብር፣ ማዕረግ፣ እውቀትና ስጦታ ነበር።

እየሁ አንባቢ፤

የአጤ ዘመን እስከመጣበትና ከኢትዮጵያ ህዝብ ጋር በአገር፣ በመንግሥት፣ በባንዲራና በዓላማ አንድ እስከሆነበት ድረስ የመራቤቴ ህብረተሰብ ከዚህ በላይ በጠቀስኩልህ ኃላፊዎችና አገልጋዮች እየተመከረ፣ እየተባበረና እየተመራ ቆይቷል።

ያንን ከአጤ ዘመን በፊት የነበረ ጊዜም የአበው ቃል የበረከት፣ የሰላም፣ የአንድነት፣ የፍትህ ዘመን ብሎ ያስታውሰዋል። የፀጋ ዘመን ነበር። አባዜ ያልነበረበት፣ ሰውም ሰው በመሆኑ ብቻ ክብር የነበረበት ዘመን ነበር።

በዚያ በቅድመ–አጤ ዘመን የመራ–ልጆች ከውስጥ እብሪተኛና አመፀኛ ሳይበጠብጣቸው፣ ከውጭ ወራሪ ጦር ሳይሰብቅባቸው፤ ብዙው እንደ አንድ አንዱም እንደ ብዙ በመሆን ተስማምተው፣ ተረዳድተው ተከባብረው ኖረዋል።

በያን ዘመን እንኳንስ ሰውና ሰው፣ አውሬና ሰውም በየቦታው ተቻችሎ የኖረበት ጊዜ ነበር። ተፈጥሮም ርኅሩኅ ነበረችና ለሁሉም እንደየፍላጐታቸው የሚሹትን ትለግስ ነበር።

ዛሬ በቀውጢው ዘመን እንጅ ድሮ ተፈጥሮ ሲያቄም አልታየም።

የመራቤቴ ህዝብ ሙያው ግብርና ነው። የእህልን ዘር በያይነቱ በብዛት ያመርታል።

ከጤፍ ዓይነት፣ ነጭ ጤፍን፣ ሠርገኛ ጤፍን፣ ጥቁር ጤፍን፣ ፌሽ ጤፍን፣ ወግዴ ጤፍን፣ ጉራዴ ጤፍን ያመርታል።

ከአገዳ እህል፦ ቆንደል ማሽላን፣ ነጩን፣ ዳለችን፣ ዘንጋዳን፣ ማርያም ዘርን፣ እዋየውን፣ ጉልቴን፣ ቂጥኝ–አይፈሬን፣ ቀዮን፣ ጥቁሬታን፣ ጥንቅሽን፣ ማንኪባና በቆሎን ያፈራል–ያመርታል።

ከጥራጥሬው እህል፦ ባቄላ፣ አተር፣ ጓያ፣ ሽምብራ፣ ምሥር፣ አደንጓሬ ሞልቷል።

ከቅባት እህል፦ ኑግ፣ ተልባ፣ ሠሊጥና ሱፍ ያመርታል።

ከአትክልቱም ቢሆን በያይነቱ አለ። መራቤቴ የእነትርንጉ፣ ብርቱካን፣ ኮምጣጤ፣ መንደሪን፣ ሎሚ፣ ሸንኮራ አገዳ፣ ሙዝና እንኮይ አገር ነው።

ከእነዚህ ሁሉ ግን መራቤቴ የሚታወቅበት በማሽላ አገርነቱ ነው። ማሽላ ከሰውና ከከብት ቀለብነት አልፎ እስኪፈስ ድረስ ይመረትበታል። የህብረተሰቡ ዋና የእለት–እለት ቀለብ ማሽላ ነው።

ማሽላ ተበልቶ፣ ማሽላ ተቅሞ ማሽላም ተጠጥቶ ይታደርበታል። እንጀራው ማሽላ፣ ንፍሮና ቆሎው ማሽላ፣ ጠላውም ማሽላ ነዋ!

በዚህም የተነሳ ይመስላል አንድ በአጤ ዘመን የነበረች አዝማሪ የመራ ሽመሉችን በማሞገስ እንዲህ ብላ ያዜመችው፦

እንጀራው ማሽላ
መጠጡ ማሽላ
ሪጡ ማሽላ
በትንፋሹ ብቻ አንገት የሚቀላ
መጣ የመሬ ልጅ ከታች ከቆላ
ብላችሁ ንገሩ ለምኒልክ መኳንንት
ዱሻቸውን በቶሎ እንዲሰበስቡት።

ይህን ያለችው የአጤው ምኒልክ የመጀመሪያ ሚስት ወይዘሮ ባፈና በምኒልክ ላይ አምፀው ራሳቸው ንግሥተ–ሸዋ ለመሆን በተነሱበት ጊዜ ነበር።

ወይዘሮ ባፈና የመራቤቴ ልጅ ብቻ ሳይሆን መራ—እመቤትም ነበሩና የአገራቸውን የመራ–ሽመል ሠራዊት አሰልፈው ምኒልክን ይወጋሉ ተብሎ ተፈርቶ ነበር። ሆኖም ግን ወይዘሮ ባፈና ምኒልክን ያገቡት የመራቤቴ ሽማግሌዎች፣

–መራ ሃይማኖቱ፣ መራ–ሽመሉና የአዛውንቱ ጉባኤ ሳይፈቅዱላቸው ስለነበር አብሯቸው የሚሸፍት ሠራዊት አላገኙም። ይኼ መችም ታሪኩ ረጅም ነውና ከየህ አናመጣውም።

አዝማሪዋ የምኒልክ መኳንንት ዱሻቸውን ይሰብስቡ ማለቷ ቀደም ብሎ የጉንደሩ እምበሳ አጤው ቴዎድሮስ ሸዋን ወግተው በነበረበት ጊዜ የመኳንንቱን እጅ ለመቀጣጣ ጉማምደውት ስለነበር ነው።

ይኼን እንግዲህ ከዚህ እናኑረውና ወደጉዳያችን እንመለስ።

መችም የመራቤቴ ሰው በአልደፈር ባይነቱ፣ በአትንኩኝ ባይነቱና በጀግንነቱ ታገር እስታገር የታወቀ ነው። ተባህር ማዶ ያለው ፈረንጁ ሁሉ ያወቀው ነገር ነው። ስንኳንስ ሰው፣ ጨረባ ነጉዲው ወፉ ዘፍኖበታል።

መጋል ቀና በል ከድቡ ድረስ፣
የመጣ እንግዳ ጠግቦ እስኪመለስ።
እብሬቱ እብሬት አበባ፣
ከባልንጀሮቹ ውሎ የሚገባ።
ሸልሙኝና አንገቴ ድረስ፣
ግንባር ግንባሩን ብየው ልመለስ።
ምጣድ ተሰብሮ የታለ ገሉ፣
የመራ አንበሳ መጣ ግልገሉ።

ብሎ ጦር የሰበቀ፣ እንካሲ የነቀነቀና ጉራዴ የመዘዘ መራ–ሽመልን የመከተው ከቶ የለም። የመራ–ሽመል ሠራዊት የህብረተሰባቸውን ሰላም፣ መብት፣ ነፃነትና ክብር ለመጠበቅ ታላቅ ተጋድሎ አድርገዋል።

ከያም መራቤቴ የኢትዮጵያ አካል ከሆነችና ህዝቧም ከሌላው የኢትዮጵያ ህዝብ ጋር ተዋህዶ ብዙው አንድ ከሆነ በኋላ፣ የመራ–ሽመል ሠራዊት ለኢትዮጵያና ለኢትዮጵያውያን ነፃነት፣ አንድነት፣ ክብር፣ ሞገስ፣ ሉአላዊነትና የሥልጣኔ ሶምሶማ መግፋት በየጠረፉ፣ በየበረሃው፣ በየፈፋው፣ በቆላ፣ በደጋው እየዘመቱ የሰሩት ገድልና የከፈሉት መስዋዕትነት እንዲህ በቀጭን ብዕር ተፅፎ፣

በአንድ ሰው አእምሮም ተሰልቶ የሚያልቅ አይደለም።

አንባቢ፣

እንዲያው ለአብነት ያህል እንዲሆን ብቻ አንዳንዱን እናምጣው።

የመራቤቴ ህዝብ ከሌላው የኢትዮጵያ ህዝብ ጋር «አገራችሁ አገሬ፣ አገሬም አገራችሁ» ብሎ መዋሃድ የጀመረውና ለአጤ መንግሥትም ያደረው ከአሥራ–ሦስተኛ መቶ ዘመን ጀምሮ ነው ይላሉ።

ይህም እንዲህ ነው፦

የአበው ቃል እንደሚናገረው፣ የአጤ መንግሥት ወኪሎች በአሥራ–አንደኛው መቶ ዘመን ገደማ ወደ መራቤቴ ይመጣሉ። የመጡት በእንግድነትና በጥገኝነት ነው።

በያን ጊዜና ከያ በፊት የአጤዎች ግዛት የነበረው አክሱም በሚባል አገር ነው። ያ አገር ዛሬም በዚሁ ስም እየተጠራ ትግራይ ውስጥ አለ። በዚያ አገርና በአካባቢው ዘራችንና የአጤነት ማዕረጋችን ከእየሩሳሌሙ ንጉሥ ከሰለሞን ተባርኮ የመጣ ነው የሚሉ ነገሥታት ብዙ ዘመን ገዝተዋል።

አገዛዛቸው አመፅና እብሪት የበዛበት፣ ፍትህ የተጓደለበት፣ አድልዎ የገነነበት፣ ሰብአዊ ክብር የተገሰሰበት ነበር። የገዥና የተገዥ፣ የጌታና ያገልጋይ፣ የጨዋና የባሪያ ልዩነትና መደብ በመፍጠር ሲሻቸው ይዘርፋሉ፣ ሲሻቸው ያስራሉ፣ ሲሻቸውም ይገላሉ።

በዚህ የሚገዙት ህብረተሰብ ይቆጣና ያምፅባቸዋል። በአመፅ ተነስቶም መዲናቸው የነበረችው አክሱምን በእሳት በነበልባል ያጠፋል። መሳፍንትና መኳንንቱንም እንደ አውሬ እያደነ ይፈጃል።

ለአክሱማውያን የዘላለም ውርደት እንዲሆንም የአመፀው ህዝብ ከተበዳዮች ሁሉ የበታች የሆነችና በተገዢዎቹ ዘንድ እጅግ የተናቀች አንዲት ሴት በአክሱማውያን የክብር ዙፋን ላይ አውጥቶ ያስቀምጣል። ይህችም ሴት ዮዲት የምትባል የሸማኔና የፋቂ ልጅ ነበረች።

አጤዎችና ቤተሰቦቻቸው እብሪትና ጥጋብ ሲያበዙ፣ ሁሉ የማይሳነው አምላክ እንዲህ ከተናቀው ህዝብ መካከል

የበታች የሆነ ሰው እያነሳ ዙፋናቸው ላይ ያስቀምጣል።

የሸማኔዋና የፋቂዋን ልጅ ዮዲትን አንድ ይሏል። የኮሶ ሻጭዋን ልጅ ቴዎድሮስን ሁለት ይሏል። የአገልጋዩዋን ልጅ መንግሥቱን ሦስት ይሏል። እነዚህ ሁሉ የገዟቸውን በእሳት ሰይፍ እየቀጡ ገዝተዋል።

ከዮዲት የእሳት አለንጋ የተረፉት የአክሱም ንጉሣውያን ቤተሰብ፣ መሳፍንት፣ መኳንንትና ወይዛዝርት አክሱምን ለቀው በሁለት አቅጣጫ ይፈረጥጣሉ።

አንደኛው እኩሌታ ወደመሀል አገር፣ ወደ ወሎ፣ ሸዋ፣ ጐንደርና ጐጃም ይመጣል። ሁለተኛው እኩሌታ ከአክሱም ውጭ ወዳሉት የትግራይ አገሮችና ዛሬ ኤርትራ ወደሚባለው ባህር–ምድር ይሄዳል። ጣጣው እስከዛሬ ያላለቀለት የአክሱማውያን ክፍያ የጀመረው እንግዲህ ያኔ ነው።

ወደመሀል አገር የተሰደዱት አክሱማውያን ለሦስት መቶ ዓመታት ያህል በስደት ከተደባለቁበት ህዝብ ጋር እየተዋሃዱ፣ እየተማሰሉና እየተዛመዱ ከአካባቢው ኑዋሪ ህዝብና ከመጤዎቹ ባህል፣ ሥርዓትና እምነት ጋር የተዳቀለ አዲስ ሥርዓት ይፈጥራሉ።

ቀስ–በቀስም እንደ መራቤቴ ያለውን የሸዋ፣ ወሎ፣ ጐጃምና ጐንደር ሰው በአንድ እምነት፣ በአንድ መንግሥት፣ በአንድ የመግባቢያ ቋንቋና በአንድ ዓላማ ያስተሳስሩታል፣ ያስተባብሩታል። ጥረቱ ሦስት መቶ ዓመታት የፈጀ እንደመሆኑ መጠንም ሥር እየሰደደና እየጠነከረ ይመጣል።

አንድ አገር የተባለው ኢትዮጵያ ነው። አንድ እምነት የተባለው የተዋህዶ ሃይማኖት ክርስትና እምነት ነው። አንድ ቋንቋ የተባለውም አማርኛ ነው። አንድ መንግሥት የተባለውም መሰረቱ አክሱም የሆነው አጤያዊ መንግሥት ነው። ይህ አዲስ መለያ እንግዲህ ወደ ደቡብ የተሰደዱት ካረፉበት ህዝብ ባህል ጋር ባህላቸውን፣ ከቋንቋው ጋር ቋንቋቸውን፣ ከእምነቱ ጋር እምነታቸውን፣ ከሥልጣኔያቸውም ጋር ሥልጣኔያቸውን እያዋሃዱ፣ እያወራረሱና እያዛመዱ የፈጠሩት ነው።

ከብዙው ተነጥሮና ተጨምቆ የመጣ ብሔራዊ ማንነት

ነው።

ሰማህ እንባቢ፣

እንዲህም ሆኖ በአክሱም አሳት አመድ ሆኖ የነበረው የአክሱም አጤያዊ መንግሥት ራሱን ሞአ አንበሳ፣ አገሩን ኢትዮጵያ፣ መለያውን አረንጓዴ-ቢጫ-ቀይ አድርጐ ዳግሚያ ይወለዳል።

ይህን አዲስ የተወለደ ኢትዮጵያዊ ማንነት ከተቀበሉት መካከል የመራቤቴ አባቶችና ህዝብ የመጀመሪያው ናቸው። ለዚህ እምነውና ይበጃል ብለው ለተቀበሉት ኢትዮጵያዊ ማንነት፣ ሥልጣኔና ክብርም ከያን ጊዜ ጀምሮ ራሳቸውን መስዋዕት ሲያደርጉ ቆይተዋል።

የመራቤቴ መራ-ሽመል ሠራዊት በ13ኛው መቶ ዘመን ዛጉዬ ላይ ዘምቶ የኢትዮጵያን አጤያዊ መንግሥት ለባለቤቶቹ ለአክሱማውያን አስመልሷል።

በዚህም አክሱማውያን በደካማነታቸውና በምግባረ-ብልሹነታቸው በሴት የተቀሙትን መንግሥት እንዲያገኙ ከማድረጉም በላይ የታላቋ ኢትዮጵያን መሠረት በደሙ አኑሯል።

አክሱማውያን የኢትዮጵያን መንግሥት በኃላፊነት ከተረከቡ በኋላ የአገሪቱን ዳር-ድንበር በማስፋት፣ በኢትዮጵያ ያልታቀፉ አገሮችና ህዝቦች እንዲታቀፉ በማድረግ፣ የኢትዮጵያዊነት ስብዕናና ዜግነት የፀና መሠረት እንዲኖረው በማድረግ ከፍተኛ እንቅስቃሴ አድርገዋል።

በዚህም የተነሳ ኢትዮጵያዊ ያልነበረው ሁሉ በከፊል በፍላጐቱ፣ በከፊልም በማግባባት፣ በከፊልም በኃይል ኢትዮጵያዊ ሆኗል።

ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት እንዲህ ደረጃ በደረጃ መሠረቱ እየተጣለ፣ ግንቡ እየተገነባና እየፀና ሲሄድ፣ ለመሪነት ኃላፊነት የተሰጠው አጤያዊ መንግሥት ግን በውስጡ በሚነሱ የስልጣን ሽሚያዎች መበጥበጡ፣ የአገሪቱና የህዝቡን አንድነት ማናጋቱ፣ ሰላማቸውንም ማደፍረሱ አልቀረም።

ለዚህም አሁን ባለንበት ጊዜ ለተፈጠረው ሁከትና

እልቂት አግባብ ያለውን አንዱን የአክሱማውያን ነገሥታት ጦስ እናመጣለን።

አስተውል እንባቢ፣

አክሱም በዮዲት ከጠፋች በኋላ መኳንንቱ በከፊል ወደ ደቡብ፣ በከፊል ደግሞ ወደሰሜንና በአቅራቢያው ወዳሉ አካባቢዎች ተሰደዱ ብለናል።

ወደደቡብ የተሰደዱት አክሱማውያን እንዳየነው ከተሰደዱበት አካባቢ ጋር እየተስማሙ፣ እየተዋሃዱና እየተባበሩ አዲስ ባህል፣ ሥርዓት፣ ቋንቋና መለያ ያወጣሉ። የመግባቢያ ቋንቋቸውም አማርኛ ይሆናል።

አማርኛ በመናገራቸውም አማራ ይባላሉ። አማራና አማርኛም ቀደም ሲል በሸዋ፣ በወሎ፣ በጐንደር፣ በጐጃም የነበረው ህዝብና የመጤዎቹ የአክሱማውያን ሁለገብ ድብልቅ ውጤት ነው።

በዚሁ አንጻር ወደ ሰሜን ተሰደው በትግራይና በባህር-ምድር የሰፈሩት ሰሜን አክሱማውያን ከደቡብ አክሱማውያኑ የተለየ የራሳቸውን ቋንቋና ባህል እያዳበሩ ይኖራሉ። የዚህም ውጤት ቋንቋው ትግርኛ የሆነ የትግራይና የኤርትራ ህዝብ ነው።

እነዚህ ሁለት ወገኖች ምንም እንኳ የተለያየ የእድገት ሂደት ቢኖራቸው፣ በአንድ ነገር ላይ ይስማማሉ። ይኸውም የኢትዮጵያ መንግሥት የሚገባው ለአክሱማውያን ነው ማለታቸው ነው። የማይስማሙበት የትኛው የአክሱም ወገን የሥልጣኑ ተረካቢ እንደሚሆን ነው።

እንዳየነው፣ ከዛጉዬ ላይ የአጤነቱን ሥልጣን የተረከቡት አማራ የተባሉት ደቡብ አክሱማውያን ናቸው። ትግሬ የተባሉት ሰሜን አክሱማውያን ዘውድና ሥልጣን ይገባናል የሚሉ እንደመሆናቸው መጠን በደቡብ አክሱማውያን ዘውድና ሥልጣን መያዝ ያቄማሉ።

ይልቁንም፣ ራሳቸውን ሞአ አንበሳ ብለው የጥንት አክሱማውያንን ዘውድና የአጤነት ማዕረግ በመያዝ የኢትዮጵያ ገዥ የሆኑት አማራ የተባሉት ደቡብ አክሱማውያን፣ እኑቶቻቸው የሆኑት የሰሜን አክሱማውያን

ትግሬዎች ለዘውዱና ለአጤነቱ ያላቸውን ፍላጐትና መብት ስለሚያውቁ በጥርጣሬ አይን ያዩዋቸዋል። ከዘውድ አካባቢም ያርቋቸዋል።

ይባስም ብለው የቤተ-መንግሥትንና ሌላውን የኢትዮጵያ የሥልጣን ዳቦ ከትግሬ አጕቶቻቸው ይልቅ ለሌላው እንደ ኦሮሞ ላለው ኢትዮጵያዊ እያቋረሱና እያቋደሱ ይመጣሉ። የትግሬ ባላባትና መኳንንት ቅሬታና ቂም ስር እየሰደደም ይሄዳል።

እንዲያውም የአጤነቱ ማዕረግና የጠቅላላው የመሳፍንቱና የመኳንንቱ መልክ ከአስራ-ስድስተኛው መቶ ዘመን ጀምሮ እየተለወጠ፣ አክሱማዊነቱ እየወየበ እየቀረ ይሄዳል።

አማራ የተባሉት ደቡብ አክሱማውያን ለኢትዮጵያ መሠረት፣ ለሥልጣናቸውም ጥንካሬ ምሶሶ ያደረጉት ኢትዮጵያዊ እየሆነ በመምጣቱም መንበረ-መንግሥቱና ሥልጣነ-መንግሥቱም ይህንኑ የሚያንፀባርቅ ይሆናል። ከብዙ ህዝቦች፣ ጕሣዎች፣ ማህበረሰቦች የተውጣጣ አንድ ብሔራዊ ዜግነትና መለያም ኢትዮጵያዊ ሆኖ እየፀና ይመጣል።

መንበረ-መንግሥቱና ሥልጣነ-መንግሥቱ ከአክሱማዊነት ወደ ሁል-አቀፍ ኢትዮጵያዊነት የመሸጋገሩን ምሳሌ ቢሹም አንዳንዱን ይጠቃቅሷል።

የጐንደር ዘመን የሚባለውን የነገሥታት ጊዜ ያሰቡ እንደሆን፣ ከአጤዎቹ እነባካፋን፣ ከመሣፍንቱም እነራስ አሊን ያስታውሷል። እነዚህ የአክሱማዊት የዘርና የደም ፍንጣቂ የማይገኝባቸው፤ ኢትዮጵያዊ በመሆናቸው ግን ዘውድ፣ የሥልጣን ካባም ላንቃ ያልተነፈጋቸው ነበሩ።

ቋንቋው የህዝብ መግባቢያ የሆነው አማርኛ ቢሆንም የጐንደር የአጤነት ዘመን በእኩሌታው ኦሮሞና እስላም ነው፡፡

የሸዋ ነገሥታት ዘመን የሚባለው'ን ጊዜ የወሰዱ እንደሆንም ዘውድና ሥልጣነ-መንግሥቱ አክሱማዊነትን ሳይሆን ኢትዮጵያዊነትን የሚያንፀባርቅ ሆኖ ያገኙታል።

አጤ ምኒሊክ በእናታቸው ከነጦና ተዛምደው ወልመዋል። በሚስታቸው በኩልም ባፈናን ፈተው ጣይቱን

ሲያገቡ ከኦሮሞውና ከእስላሙ ተዛምደዋል፡፡ ከነብጡል ጋር ዘር ተዛርተዋል፡፡

የመጨረሻውን ሞአ አንበሳ ኃይለ ሥላሴን የወሰዱ እንደሆንም በእናት ጉራጌነትን፣ በወንድ ቅድም-አያት ኦሮሞነትን በሚስትም እንዲሁ ኦሮሞነትን ይመለከቷል፡፡ ታሪከ ነገሥቱ የሰለሞን ንፁህ ዘር አለኝ ብሎ ለማታለል ሲል ባይጠቅሰውም ይኼ መቸም ዘርና ደም ነውና አይፋቅም፡፡

እንግዲህ፣ በደቡብ አክሱማውያን በኩል ያለው ይህ ሲሆን በሰሜን አክሱማውያን በኩል ያለው የተለየ ነው። የትግራይ መኳንንትና ህዝቡ ኢትዮጵያን አገሬ፣ ሰንደቅ ዓላማዋን ሰንደቅ-ዓላማየ ብሎ ተቀብሏል። ለዚህም እንደሌላው ኢትዮጵያዊ፣ አንዳንዴም ከዚያ በላይ የህይወትና የኑሮ መስዋዕትነት ሲከፍል ቆይቷል።

መንግሥት ይገባኛል ብሎ ስለሚያምን ግን የኢትዮጵያን መንግሥት በሙሉ ልቡ አልተቀበለም። በዘር፣ በቋንቋና በባህል በኩል ውህደትና ቅይጡ አይሻኝም ብሎ በአብዛኛው የራሱን የትግሬ ጥራት ጠብቆ ቆይቷል።

የትግራይ መኳንንት ከዘውድ መገለላቸውንም በመሥራችነትና በይዞታ ቅድሚያ የእኛ ናት ከሚሏት ኢትዮጵያ ታሪክ የተገለሉ አርገው ስላዩት የአጤነትን ሥልጣን የሚይዙበትን ሁኔታ ሲያሰሉ ብዙ ዘመን ያሳልፋሉ።

ከሰባት መቶ ዓመት በኋላም ድል እንዳገኙ በቦታው እናያለን። ላሁኑ ወደጀመርነው ወደ መራቤቴ ልጆች እንመለስ።

ስማኝ አንባቢ፣

የመራቤቴ ጐበዞች በመራ-ሽመል ሠራዊትነት ታድመው የኢትዮጵያን ዘውድና መንግሥት ለአክሱም አጤዎች ካስረከቡ ከሦስት መቶ ዓመታት በኋላ፣ የኢትዮጵያንና የህዝቧን ነፃነትና የሥልጣኔ ሂደት ከወራሪ ለመከላከል ዳግም መነሳት ግድ ይሆንባቸዋል።

ይህም እንዲህ ነው።

አክሱማውያኑ የአጤነቱን ሥልጣን መልሰው ከያዙ በኋላ፣ ጥንት የአያቶቻቸውን መንግሥት አክሱም ላይ በእሳት ለመጥፋት የዳረገው በሽታ መልሶ ያገረሽባቸዋል።

ይህም በሽታ ሥሩ ከቤተ-መንግሥት ሆኖ የሚያቆስለው፣ የሚያማቅቀውና የሚጨርሰው ግን ህዝብን ነበር።

በሽታው የሥልጣን ብልግና፣ እብሪት፣ ፍርድ-አልባነት፣ ጭቆናና ብዝበዛን የመሳሰለው የመንግሥት በሽታ ነው። «ሞአ-አንበሳ» ብለው ዳግመኛ የኢትዮጵያን አጤ ለመሆን የበቁት አክሱማውያን ለዚያ ያበቃቸውን ህዝብ በቅንና በፍትህ እንደማስተዳደር ይልቅ ለጥቃት፣ ለስቃይ፣ ለግድያ፣ ለእርዛት፣ ለረሀብ ይዳርጉት ጀመር።

ህዝብ በጣም ያዝናል፣ ወደ አምላኩም አቤት ይላል። ያን ጊዜ የህዝብ አምላክ የህዝብ መበደልንና አቤቱታ ፈጥኖ የሚያይ፣ የሚሰማና ፍርድ የሚሰጥ ነበር። ዛሬማ፣ እንኳንስ ህዝቡ፣ ራሱ አምላክም እየተበደለ ዝም ብሏል።

ያኔ፣ የአጤዎቹን ብልግና ያየና በዚህም የተከፋ አምላክ ከዩዲት እሳቷ የከፋ ቀጪ በአጤው፣ በመሳፍንቱና በመኳንንቱ ላይ ያመጣል።

ግራኝ መሐመድ የተባለ ሱማሌ ጦሩን እየሰበቀ፣ የጐራዴውን ስለት እያብለጨለጨ፣ ሠራዊቱን እንደሰደድ እሳት እያጥመለመለ በአጤ ልብነ-ድንግልና በመንግሥታቸው ላይ መጥቶባቸዋል።

ግራኝም ከዩዲት እሳቷ በከፋ ሁኔታ አጤውንና መኳንንቶቻቸውን ቀጥቷል። አጤው ራሳቸው ከግራኝ በመሸሽ እንደቀበሮ በየጉድጓዱ፣ እንደ ዝንጀሮም በየገደሉና በየዋሻው ሲደበቁና ሲንከራተቱ ኑረው በዚያው የተበላሸ አሟሟት ገጥሟቸዋል።

አጤ ሲሸሽና ሲሞት መንግሥት ይጠፋል፣ አገር ይበተናል፣ ሰንደቅ ዓላማም ይወድቃል። ቅዱስና ክቡር የነበረው ሁሉ ይረከሳል።

እንዲህ ዓይነቱም ሁኔታም የመራ-ሽመል ሠራዊትን ቁጣ ይቀሰቅሳል፣ ደማቸውን ያፈላል፣ እንደ አንበሳም ያስገሳቸዋል። ጦርና ጋሻቸውን ጨብጠው፣ ጐራዴና ምሳራቸውን ስለው፣ እንካሲያቸውንም አሹለው ግራኝ በጦርና በእሳት ያጠፋውን ለማልማት፣ ያረከሰውን ለመቀደስ፣

እሱንም ወደመጣበት ለመመለስ ይነሳሉ።

ግራኝ ስለችሎታውና ስለጀግንነቱ የተነገረለት ኃይለኛ ጠላት ነበር። ከሰው በላይ የሆነ ችሎታ አለው ይላሉ። ጦር ወርውሮ አይስትም፣ ከንዱም ቋጥኝ አንስቶ ለብዙ ርቀት የሚወረውር ነበር ይላሉ።

እንዴ! እስተዛሬም ድረስ ግራኝ ሰላሌ ላይ ቆሞ በግራ እጁ የወረወረው ነበር የሚባል አንዳንድ ቋጥኝ እልፎ እልፎ መራቤቴ ውስጥ አለ። ታዲያ ይህን ሰው የመከቱ የመራ-ሽመል ሠራዊት ናቸው።

ከሸዋ አሳደው፣ አዋሽን አሻግረው፣ በአጋዴን በረሃ ላይም አኳትነው ከዚያው ከተነሳበት ከሶማሌ ምድር መልሰውታል።

የወደቀውን ሰንደቅ ዓላማ አቅንተው፣ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያንን ወደ ቀደመ-ክብራቸው መልሰው፣ የሸሸውንና ሲደበቅ የኖረውን የሞአ አንበሳ አጤም ወደ ቤተ-መንግሥቱ በመመለስ መንግሥት አቁመው፣ መራ-ሽመሎች ወዳገራቸው ተመልሰዋል።

ግራኝ ያኔ ተሸነፈ። ተከታዮቹ የሶማሌ ልጆች ግን ከያን ጊዜ ጀምሮ በኢትዮጵያ ላይ ቂም ይይዛሉ። ለብዙ መቶ ዓመታትም ከወዲያ የህንድ ውቅያኖስን፣ ከወዲህ የዋቢሸበሌን ውኃ እየተጐነጩና ማታቸውንም እየቃሙ ብቀላን ይዶልታሉ።

የብቀላ ጊዜም ይመጣላቸዋል።

ይኼ የነገርኩህ እንግዴህ ከወዲያኛው ዘመን የመራቤቴ ልጆች ስላደረጉት ትግልና ስለከፈሉት መስዋዕትነት ነው። ከወዲህኛው ዘመን ምሳሌ ጥቀስ ቢሉም ቱርክ፣ ግብጥ፣ ደርቡሽ፣ እንግሊዝና ጣሊያን የመሰሉትን ወራሪዎች ያመጧል።

እነዚህ ሁሉ በዘመናቸው ዓለምን ያንቀጠቀጡ፣ ጀግና ያርበደበዱ ኃያላን መንግሥታት ነበሩ። ቱርክ በዘመኑ የዓረቡን ዓለም በሞላ፣ እስያውንና አውሮፓውን በከፊል በሰይፍ እየቀጣ አስገብሮ ገዝቶታል። የሮማውያንን ዘመን የቀበረ፣ የክርስቲያን ዓለሙን በሞላም ያማቀቀ ኃያል መንግሥት

ነበር።

እንዴታ! ቱርክ ኢየሩሳሌምን ሳይቀር ገዝቷል።

ይኼ ኃያል መንግሥት ኢትዮጵያንም ተመኝቶ በቀይ-ባህር በኩል በግብጥ ፓሻዎች እየተረዳ መጥቶ ነበር። ታዲያ ኢትዮጵያ የመራ-ሽመሎች አገር ነችና እንደሌሎቹ አገሮች የምትደፈር ሆና አላገኛትም።

ጀግኖች የኢትዮጵያ ልጆች ሰይፉን በጋሻቸው መክተው፣ የእብሪት ልቡን በጦር ወግተው፣ ባህር ምድር ላይም አኳትነው ወዲያው ከቀይ ባህር ማዶ ወዳለ ምሽጉ መልሰውታል።

አንባቢ፣ አልሰማህ እንደሁ ነው እንጂ ያኔ ዓለም ለቱርክ በተንበረከከበት ጊዜ ከራሳቸው አገር አልፈው ሌላውን ዓለም ከቱርክ እናድናለን ብለው የፎከሩ ኢትዮጵያውያን ብቻ እኮ ነበሩ። ኢስጣንቡል ላይ ሊዘምቱበት ከጅለው ነበር።

አጤው ቴዎድሮስ ራሳቸው
«ታጠቅ ብሎ ፈረስ ካሣ ብሎ ስም፣
አርብ አርብ ይሸበራል ኢየሩሳሌም።»

የተባለላቸው እንዲያው ለይስሙላ እኮ አልነበረም። ያኔ ኢየሩሳሌምን ይገዛ የነበረውን ቱርክን ለመውጋት ከጅሏቸው ስለነበር ነው።

ግብጡም ኢትዮጵያን ለመውረር በዚያው በባህር ምድር በኩል መጥቶ ነበር። ጀለብያውን ተቀምቶ ተመልሷል።

ደርቡሽም ከሱዳን መጥቶ ነበር። የተራውን ጀግና ትተኸው አጤው ዮሐንስ ራሳቸው ተሰውተው ነው የኢትዮጵያ ነፃነት ያኔ የተጠበቀው። እንዴታ አጤ ዮሐንስ የአገሬን ነፃነት፣ አንድነትና ክብር ከምትደፍር አንገቴን ቆርጠህ ራሴን ውሰድ ብለው ሰጥተውታል።

ዓለምን በከፊል ይገዛ የነበረው እንግሊዝም መሣሪያውን በህንድ ዝሆንና በዐረብ ፈረስ ጭኖ ኢትዮጵያን ሊወር መጥቶ ነበር። አጤው ቴዎድሮስና የኢትዮጵያ ልጆች አገራቸውን አሳልፈው ለባዕድ ከመስጠት ሞት የሚመርጡ መሆኑን በሞታቸው አሳይተውታል።

ታዲያ እንግሊዝ ከመገዛት ይልቅ ሞትን የሚመርጡ ሰዎች አገር ቅኝ-ግዛት አይሆነኝም ብሎ በገባበት እግሩ ሳይውል ሳያድር በሩጫ ወጣ። እንግሊዝ ኢትዮጵያውያን ሳይተኩሱበት በቀረርቷቸው ብቻ ተሸፈራርቶ ተመለሰ።

የጣልያኑ ነገርማ ለትንግርት የሚሆን ነው። ጣሊያን ኢትዮጵያን ሊገዛ መጥቶ የነበረው ሁለቴ ነው። መጀመሪያ መድፉን ደግኖ በባህር-ምድር በኩል ቢመጣ በአጤው ምኒልክ የተመራው የኢትዮጵያ ጀግኖች ጦር አድዋ ላይ ነጭ መልኩ የአህያ መንደባለያ አመድ እስኪመስል ድረስ አቡነው፣ አቡነው መለሱት።

በአድዋ የተዋረደው ጣሊያን ቂም ይዞ ዳግመኛ መድፉን ብቻ ሳይሆን ሮቢላኑን መርዝ ጭኖ መጣ። አሁንም እንደበፊቱ አባቶችህና እናቶችህ በአምስት ዓመት ጦርነት መግቢያ መውጫ አሳጥተው፣ እንደልጅም ገርፈው አባረውታል። በዚያ የአምስት ዓመት የወረራ ዘመን ታላቁና ወሳኙ የነፃነት ትግል የተካሄደው መራቤቴ ውስጥ ነበር።

በፌጥራ፣ በዞማ፣ በደራ፣ በሚዳ፣ በወረሞ፣ በላይና በታች ቤት መራቤቴ እንደእነ ደጃቾች አበበና ተሾመ ሸንቁጥ፣ እንደእነራስ አበበ አረጋይ፣ እንደነሻለቃ ይልማ ሺበሺ፣ ከሴቶቹም እንደነ ወይዘሮ በላይነሽ ወልደተንሳይ ያሉ አርበኞች የመራቤቴ ልጆችን እየመሩ ታላቅ የነፃነት ገድል ሰርተዋል።

አምስት ዓመት ሙሉ የመራቤቴ ልጆች ደማቸውን እንደውኃ፣ አፅማቸውን እንደማዳበሪያ ለኢትዮጵያ ነፃነት ችግኝ እየመገቡ እንዲለመልም፣ እንዲያብብና ፍሬም እንዲያፈራ አድርገዋል።

እንዲህም ሆኖ መራ-ሽመሎች ለኢትዮጵያና ለኢትዮጵያዊነታቸው ይደረጉት የዘመናት ትግል፣ ያቀረቡትም የህይወትና የኑሮ መባዕ እጅግ የሰፋ ነው።

* * *

አየሁ እንባቢ፣

ይህን የመርሀቤቴ ሰዎች ገድል የነገርኩሀ ቀደም ሲል ያስተዋወቅሁሀ አራት ሰዎች ኢትዮጵያዊነት መሠረት ምን እንደሆነና የተጓዘበትንም መንገድ እንድትገነዘብ ነው።

አየሁ ወገን፣

እንባቆም፣ ወላሌ፣ ዞማለምና እኔ አጐናፍር ተወልደን ያደግነው በዚሁ መርሀቤቴ፣ በመራምባ መንደር ውስጥ ነው። የተወለድነው በአንድ ዘመን፣ ጣሊያን በአርበኞች ትግል አገራችንን ለቆ ከወጣ በኋላ ነው።

የአራታችንንም አባቶች የአምስቱን ዓመት የወረራ ዘመን ያሳለፉት በአርበኝነት የወራሪውን ጣሊያን ኃይል በከተማ፣ በገጠር፣ በቆላ–በደጋ፣ በማኪ–በሜዳ ሲዋጉ፣ ድል ሲያደርጉና ለአገራቸው መስዋዕት ሲሆኑ ነው።

ያንጊዜም ሆነ ከዚያ በኋላ እስካሁን በጠቅላላው በመርሀቤቴና ከዚያም ባሻገር በአርበኞች አምባ ሁሉ እስተዛሬ እንደሚነገረው የአራቱ አባቶቻችን ጀግንነትና ጀብዱ ብዙ አቻ የማይገኝለት፣ ስማቸውም ዘወትር ከስመ–ጥሩዎች አርበኞች ከነበላይ ዘለቀ ጋር እየተነሳ የሚወሳ ነው።

የእንባቆም አባት ፊታውራሪ ቢሆንኝ፣ የወላሌ አባት ፊታውራሪ ዠማነህ፣ የዞማለም አባት ፊታውራሪ የሰው–ሰውና የእኔ አባት ፊታውራሪ በቃሉ በጦርነቱ ዘመን «አራቱ መራ» በመባል በአንድ የጋራ ስም ይታወቁ ነበር። «አራቱ መራ» ሠራዊታቸውን እያስከተሉ ከጐጃም እስከ ሸዋ ምንጃርና ሸንኮራ ድረስ ዘምተው ያልደመሰሱት የጣሊያን ጦር እንደሌለ ይነገርላቸዋል። ጣሊያንም ራሱ የሞተው በደሙ፣ የተረፈው ደግሞ በቃሉና በብዕሩ መስክሮላቸዋል።

አራቱ አባቶቻችን ከጦርነቱ በፊት ተራ ገበሬዎች ነበሩ። የፊታውራሪነት ማዕረጉን ለአራቱም የሰጡት ራስ አበበ አረጋይ ናቸው። ራስ አበበ በጦርነቱ ዘመን የሰሜን–ሸዋና የአካባቢው አርበኞች የበላይ አዛዥ ነበሩ።

ነፃነት ከተመለሰ በኋላ የአባቶቻችን የፊታውራሪነት ማዕረግ በንጉሠ–ነገሥቱ ፀድቆ ጥቂት ጊዜ ተጠርተውበታል። ግና ወደታች እንደምናየው በፊታውራሪነት ቀርቶ በህይወት ብዙ አልቆዩም።

ለማንኛውም፣ ነፃነትን በትግላቸው አስመልሰው የአገር ሰንደቅ ዓላማ በክብር ከተውለበለበ፣ አጤውም በዙፋናቸው ከተቀመጡ በኋላ አባቶቻችን የቀደመ ሥራቸው የነበረውን ግብርና ለመጀመር ወደመራምባ ይመለሳሉ። በዚያው በተመለሱበት ዘመንም አራቱም ከአምስት ዓመት በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ ከሚስቶቻቸው ጋር ይገናኙና በዘጠነኛው ወር እኛ ለመወለድ በቃን።

የእኛ መወለድ በመሠረቱ የአዲሱ ነፃነት ዘመን የምሥራች ነበር። እኛም ሆነ በዚያን ዘመን የተወለድነው ኢትዮጵያውያን በአባቶቻችን የላብ፣ የደምና የህይወት መስዋዕትነት የተገኘው ነፃነት ተቋዳሽ ለመሆን ብናስብ ብንመኝና ብንጠብቅ ብዙ አልነበረም። ቤተሰቦቻችን እንደእኛው መመኘታቸውና መጠበቃቸው አልቀረም።

ዳሩ ግን፣ በአሳዛኝ መልኩ የኢትዮጵያ ነፃነት የአንዳንድ ኢትዮጵያውያን ነፃነት በግፍ የሚገፈፍበት ሆኖ ገና በጠዋቱ በመገኘቱ የነፃነት አርበኞች የሆኑ አባቶቻችን በግፈኞች እጅ ህይወታቸው ያልፍ ዘንድ ግድ ሆኗል።

ኢትዮጵያ ከጣሊያን ነፃ በወጣች በአስረኛው ዓመት ላይም «አራቱ መራ» ይባሉ የነበሩት አባቶቻችን በንጉሠ ነገሥቱ በአጤው ትዕዛዝ መራምባ ኮረብታ ላይ በገመድ ተንጠልጥለዋል። አጤው በስቅላት ቀጥተዋቸዋል።

ይህ ለምን እንደዶሆነ ለመገንዘብ በጦርነቱ ዘመንና ከጦርነቱ በኋላ በአንዳንድ እንደ «አራቱ መራ» ዓይነት አርበኞችና በአጤው መካከል የተፈጠረውንና እየተጠናከረ መጥቶ በአሰቃቂ የተፈጸመውን ሁኔታ ማጤን ያሻል።

ጣሊያን አገር ሲወር አጤው የግል ባለሟሎቻቸውን አስከትለው ከአገር መውጣታቸው በአንዳንድ አርበኞች ዘንድ እንደክህደት ኩብለላ ታይቷል። የውጭ ጠላት አገሩን ወሮ ህዝቡን በአብሪት ሲገዛና ሲመዘብር እንደምን አጤው

ይኮበልላል። እንደቀደሙ ነገሥታት ህዝቡን አስተባብሮ፣ አርበኛውን አሰልፎ ለመንግሥቱ፣ ለሰንደቅ ዓላማውና ለልዕልናው በግንባር መዋጋትና ማዋጋት ነበረበት የሚሉ ነበሩ።

አለም እንደሚያውቀው፣ ኢትዮጵያ የውጭ ጠላት ሲመጣባት አገርና ህዝብ ጥለው የኮበለሉ አጤው ኃይለ-ሥላሴ በታሪክ የመጀመሪያው ነበሩ። የቀደሙ ነገሥታት ከአርበኞቻቸው ጋር ተሰልፈው መዋጋት ብቻ ሳይሆን ህይወታቸውን ለአገር መስዋዕት እንደዳረጉ እነ ቴዎድሮስን፣ እነዮሐንስን ያስታውሷል።

ይህ በአጤው ላይ አንዳንድ አርበኞች ያላቸው ቅሬታ ሥር እየሰደደ ሄዶ በዚያው በጦርነቱ ዘመን ነፃነት ሲመለስ በአጤው ፈንታ ለኢትዮጵያ አዲስ መሪና አመራር እንመሰርታለን የሚሉ ነበሩ። በተለይ እንደታዋቂው አርበኛ ክቡር ደጃች ታከለ ወልደሐዋርያት ያሉት አጤያዊነትን አስወግዶ ሪፑብሊክ እንመስርት የሚል ሀሳብ ነበራቸው።

ይህ ሁሉ የአርበኞች ቅሬታ ለአጤው ባሉበት አገር በወሬ ወኪሎቻቸው አማካይነት ይደርሳቸዋል። ወደአገር ሲመለሱም ቅድሚያ የሚሰጡት ተግባር ቅሬታ አለባቸው በተባሉት አርበኞች ላይ የበቀል እርምጃ መወሰድ ይሆናል።

ስለሆነም፣ አጤው በአርበኞቹ ደም ነፃነት ተገኝቶ ወደዙፋናቸው ከተመለሱ በኋላ ባንዳን ከፍ-ከፍ፣ አርበኛን ዝቅ ዝቅ ማድረግ ይጀምራሉ። ለዙፋናቸው ዘላቂነት በማሰብም አንዳንድ ቀንደኛ የሚሏቸውን አርበኞች ምክንያት እየፈጠሩ ሀብትና ንብረታቸውን ከመግፈፍና ክብራቸውን ከመቀነስ አንስቶ በእሥርና በሞት መቅጣት ይጀምራሉ።

ለኢትዮጵያ ራሳቸውን መባዕ አድርገው ያቀረቡ እጅግ የተከበሩ ታላቅ የአገር አርበኞችም በአጤው እጅ ይበላሻሉ። ደጃች ታከለ ወልደሐዋርያትን፣ ደጃች በላይ ዘለቀንና ሌሎችን ትውልድ፦

ይህች እናት ኢትዮጵያ ሞኝ ናት ተላላ፣
የሞተላት ቀርቶ የገደላት በላ።

እያለ በሀዘንና በሀፍረት የሚያስታውሰው ለዚህ ነው።

እንደነ በላይ ዘለቀ ያሉት የወንዶች ወንድ ቀን ጥሏቸው በባንዳና በፈሪ እጅ አዲስ አበባ ላይ በገመድ ሲንጠለጠሉ ከምሬታቸው የተነሳ

«አንቺ እናት ኢትዮጵያ በድየሽ ከሆነ ነፍሴን አይማራት። በድለሽም ከሆነ ወንድ አይፈጠርብሽ።»

ብለው ከመራገም በቀር አማራጭ አልነበራቸውም። በእርግጥ የኢትዮጵያ ትውልድ እርግማኑን ተሸክሟል። ከጣሊያን ወዲህ በነታከለ ወልደሐዋርያትና በነበላይ ዘለቀ ደረጃ የሚታይ ወንድ በኢትዮጵያ ውስጥ ተፈጥሮ እንደሆነ አላየነውም። እየን ብሎ የጠቆመም የለ።

ለ«አራቱ መራ» የመራምባ ስቅላት አመቺ ሁኔታ የፈጠረው አጠቃላይ ሂደት እንግዲህ ይህ ነበር። በቀጥታ ለስቅላታቸው ያበቃቸው ግን አጤው የአራቱንም ርስት ቀምተው መሣሪያቸውን ለመንግሥት እንዲያስረክቡ ትዕዛዝ መስጠታቸው ነበር።

መርሀቤቴ ውስጥ እንደባህል ሆኖ ለወንድ ልጅ ሦስት ታላቅ የመብት ምሶሶዎች አሉ። እነዚህም ሚስት፣ ርስትና ብረት ናቸው። ማንም ሰው ቢሆን እነዚህን ይደፍር ዘንድ አይችልም። እንደ «አራቱ መራ» ላሉት አርበኞች ደግሞ የርስትና የብረታቸው መደፈር በቀላሉ ሊታለፍ የሚችል አልነበረም። በተለይም ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው «አራቱ-መራ» አጤውን በኮብላይነትና በባንዳ ሿሚነት የሚወቅሷቸው ስለነበር በቀጥታ መደፈራቸው ደግመው መሣሪያ እንዲያነሱ አስገድዷቸዋል።

በዚህም የተነሳ «አራቱ-መራ» ጥቂት ደጋፊዎቻቸውን አስከትለው ወደ ዠማ ወንዝ በሽፍትነት ድጋሚ ይወርዳሉ። በአርበኝነት ያስገኙት የአገር ነፃነት የግል ነፃነታቸውን የገፈፋቸው መስሎ በመታየቱም ታላቅ ቅሬታና ቂምም ይፈጠራል።

አራቱ-መራ ከሸፈቱ በኋላ ለስድስት ወራት ያህል ድፍን መርሀቤቴን ከአጤው ግዛት ቁጥጥር ውጭ አድርገውት ቆዩ። በወዲህ በዠማም በኩል ሆነ በወዲያ በወንጭት በኩል ከአገሬው ኑዋሪ በቀር ማንም ሊገባ አልቻለም። በአውራጃው

ውስጥ የነበሩት የአጤው ተሿሚዎችም በሙሉ አገሩን ለቀው እንዲወጡ ሆነ።

መርሀቤቴ የጉጃም አዋሳኝ በመሆኑና በጊዜው በጉጃምም ውስጥ አጤው ላይ የመሸፈት አዝማሚያ በመኖሩ በመንግሥት አካባቢ ታላቅ ሥጋት መፈጠሩ አልቀረም። ሁኔታው በጦርነት የሚፈታ አልነበረም።

አጤው መላ የማያጡ ሰው ነበሩና ከመርሀቤቴ ተወላጆች መካከል በአርበኝነታቸው የታወቁ፣ ግና ለእሳቸው ታማኝ የነበሩ ሰዎችን በአማላጅነት ወደ «አራቱ መራ» ይልካሉ። እነዚህ የተላኩትም ሰዎች በሁለቱ ታዋቂ የመርሀቤቴ አርበኞች በደጃች ፀሐዩ እንቁስላሴና በደጃች ሽዋረገድ በሼ የሚመሩ ነበሩ።

የአጤው አማላጆች ደጃች ፀሐዩና ደጃች ሽዋረገድ ከብዙ ጥረትና የአገሬው ካህናት ድጋፍ ከታከለበት በኋላ «አራቱ–መራ» ከአጤው የተሰጣቸውን ይቅርታ ተቀብለው ከሽፍትነት እንዲመለሱ ለማድረግ ቻሉ። በአጤው የተሰጠው የእርቅ ቃልም—

– አራቱ መራ ከነሠራዊታቸው ከሽፍትነት ተመልሰው ሰላማዊ ኑሮ እንዲጀምሩ፣
– አጤውን ይቅርታ እንዲጠይቁ፣
– አጤው የአራቱንም የፊታውራሪነት ማዕረግ እንዲያፀድቁ፣
– ርስታቸውን እንዲመልሱ የሚደነግግ ነበር።

በዚህ መልኩ ከአጤ ጋር ታርቀናል ብለው አራቱ መራ እጃቸውን ይሰጣሉ።

አጤው ግን በቃላቸው አልረጉም። አማላጆቹ እነደጃች እንቁስላሴ ወደ አዲስ አበባ ከተመለሱ በኋላ፣ ሌላ በሻለቃ የሚመራ ጦር ወደመርሀቤቴ ተልኮ «አራቱ መራ» አገር ሰላም ነው ብለው እንደተቀመጡ ከየቤታቸው ከቦ ያዛቸው።

ከበባው የተካሄደው ማለዳ ጠዋት ነበር። ቀትር ላይ ሲሆን መራምባ ኮረብታ ላይ አውጥተው አራቱንም በአጤው ትዕዛዝ ሰቀሏቸው።

የአራቱ መራ ስቅላት እንደተሰማ መርሀቤቴ በሙሉ

ሸፈተ። ከዳር ዳር እስከዳር የጀግኖቻችንን ደም እንበቀላለን ብሎ ተነሳ። እንደሚነገረው በስቅላቱ እንኳን የአገሬው ሰው የአገሩ አውሬ ሁሉ ተቆጥቶ ነበር ይባላል። በአጤው ላይ ብቻ ሳይሆን በዚያን ጊዜ የአጤው ደጋፊ መስለው በታዩ ሌሎች እንደነደጃች ፀሐዩ እንቁስላሴ ባሉ የመርሀቤቴ አርበኞች ላይም ታላቅ የህዝብ ቅሬታ ተፈጠረ።

በመሰረቱ ደጃች ፀሐዩ እንቁስላሴና ደጃች ሽዋረገድ በሼ ለብዙ ጊዜ ዳግም የመርሀቤቴን ምድር አልረገጡም። ህዝቡም ለረጅም ጊዜ ቂም ይዞባቸው ስለነበር በደርጉ ዘመን አገራችን ብለው ቢሸፍቱ እየያዘ በመስጠት በመትረየስ አስባርኳቸዋል።

የመርሀቤቴ አመፅ ብዙ ወራት ከቆየ በኋላ ደጃች ገለታ ቆሮች በሚባሉ አርበኛ አስታራቂነት ሊያከትም ችሏል። ደጃዝማች ሰላም በመፍጠራቸው በህዝቡም ዘንድ የሚታመኑ ሆነው በመገኘታቸው የመርሀቤቴ ገዥ ሆነው ብዙ ዓመታት ያገለግላሉ።

* * *

እንግዲህ፣ አጤው አባቶቻችንን በሰቀሉበት ዓመት ወላሌ፣ እንባቆም፣ ዞማለምና እኔ የአሥር ዓመት ልጆች ገደማ ነበርን። አባቶቻችንም ሲሰቀሉ፣ የተሰቀለ በድናቸውንም የቀን ፀሐይ ሲመታው፣ በኋላም ከተሰቀሉበት ወርደው በመራምባ ሚካኤል ሲቀበሩ ከዚያው ሆነን ተመልክተናል። የተፈጸመውን ሁሉ በጆሮ ሰምተን ሳይሆን ምስሉ በህሊና ዘላለም ተቀርጾ በሚቀር የልጅነት ዓይን ዓይተን መስክረናል።

የኢትዮጵያዊነታችን ግንዛቤ መንደርደሪያ የሚሆነንም ያ–አሰቃቂ ሁኔታ ነበር። አራታችን በየፊናችን ኢትዮጵያዊነትን በመሻት በተጓዝንባቸው መንገዶች ሁሉ ያ–ሁኔታ አይለየንም።

የኢትዮጵያ አብዮት እስከፈነዳበት እስከ 1966 ድረስ የአራታችንም የህይወትና የኢትዮጵያዊነት ፍለጋ ጉዞ ሳይለያይ፣ እየተደጋገፈ በአንድ ላይ ሲያመራ ቆይቷል።

የልጅነት ዘመናችንን በአንድ ላይ በከብት እረኝነትና በወፍ ጥበቃ ያሳለፍነው በዚያው በመራምባ መንደር ነው።

በኋላም ደጃች ገለታ ቆርቾ በአውራጃው ከተማ አስኳላ ትምህርት ካስጀመሩ በኋላ ከፊደል ቆጠራ እስከስድስተኛ አብረን ተምረናል።

ከ7ኛ እስከ 12ኛ ክፍል ያለውን ደግሞ አብረን ደብረ–ብርሃን ውስጥ ኃይለ–ማርያም ማሞ ትምህርት ቤት ተምረናል።

በመካከሉ አራታችንም በተለያዩ ጊዜያት ትምህርታችንን አንዳንዴ ለወራት፣ ሌላ ጊዜም ለዓመት በማቋረጥ ወደአባቶቻችን አገር ወደ መርሀቤቴ በመመለስ እንደልጅነታችን በእረኝነትና በእርሻ አሳልፈናል። በእነዚህ ዓመታት ሁሉ የተለያየንበት አንዳችም ጊዜ የለ። ግንኙነታችን እንደጓደኛ ሳይሆን እንደወንድምና እህት እጅግ የጠበቀ ነበር።

ይህ ሁሉ ግን በ1966 ይደናቀፍና አራታችንም የየግል ጉዞ እንጀምራለን። ከዚህ በኋላ እያንዳንዳችን ስለደረስንበት የኢትዮጵያዊነት ግንዛቤና በላያችንም ላይ ስላለፈው ባለታሪኮቹ ራሳቸው ይናገሩታል።

* * *

እልቂት

አንባቢ!

እስካሁን ከእኔ ጋር ከሆንክ ቀደም ሲል ወደተጀመረው ወደ ሦስቱ ባልንጀሮቼ ህይወት ልመልስህ።

ወላሌ ዣማነህ አዲስ አበባ ወድቆ ከነበረበት ጉዳና ተነስቶ፣ ዞማለም የሰውሰውም ከታሰረችበት የጉድጓድ እሥር ቤት ተፈታ ወደ መራምባ መንደር ከወጡ በኋላ ያረፉት በሦስተኛው ባልንጀራችን፣ በገበሬው በእንባቆም ቢሆነኝ ቤት ነው።

ወላሌን ከወደቀበት አንስቶ ወደ መራምባ መውሰዱ ምንም ችግር አልነበረበትም። ኢትዮጵያዊነቱ ብቻ ሳይሆን ስብዕናው በጊዜ ተራክሶ እንደ እቃ የተጣለን ሰው የት ሄደ? የሚል የለም። እሱ በተነሳ በማግስቱ ያን የነበረበትን የአርበኞች ህንፃ ሥር የልመና ቦታም ሌላ የከፋ ወይም ያነሰ ሰቆቃ በላዩ ደለፈ ዜጋ እንደሚተካበት አያጠራጥርም።

ዞማለምን ከታሰረችበት ማስፈታቱ ግን ቀላል አልነበረም። ብዙ ውጣ ውረድ፣ ድካምና ንዋይ ጠይቋል። አንድ ዓመት ያህል ስትታሰር ፍርድ ቤት ቀርባ በአቃቤ ህግ የተከሰሰችበት፣ በምስክር የተረታችበት፣ በዳኛም የተፈረደባት ወንጀል የለም።

ኢትዮጵያ ሰው ያለ ወንጀሉ፣ አለያም ወንጀል በሀሰት ወንጀይ እንደጥብቆ እየተሰፋ የሚጠለቅለት አገር በመሆኗ ዞማለምን ለማስፈታት ጠበቃ ማቆምም ሆነ ለዳኛ አቤት ማለት አላስፈለገም። ህግ ሳይኖር፣ ቢኖርም ሳይከበር በህግ ልዳኝ ማለት ከንቱ ድካምና ምኞት ነው። ምናልባት በዛሬዋ ኢትዮጵያ በህግ ተከሶ በህግ የሚቀጣና በህግ ነፃ የሚሆን ሰው እንደሌባና ነፍሰ–ገዳይ ያለው ተራ ወንጀለኛ ብቻ ነው። እንደዞማለም ያለው ንፁህ ዜጋ ክስና ቅጣቱ የሚፈፀምበት ከህግ ባሻገር ባለ የእብሪት ሸንጐ ነው።

በዚህ ሸንጐ ላይ የተመሰረተ ክስንና የተላለፈ ቅጣትን ለማስነሳት ለማዘዝ ሥልጣን ያለውን ሰው ማፋለግና እጅ መንሻውን ማሳመር ያስፈልጋል። ጊዜው በህግ ሳይሆን

በሥልጣንና በጉቦ ጉዳይ የሚፈፀምበት ነዋ!

የእኛም ትኩረት በዚሁ ላይ ነበር። በመጨረሻው አዲስ አበባና መራቤቴ ጊዜ ከፍ ከፍ ያደረጋቸው ተሿሚዎች ተፈልገው በመገኘታቸው አጥጋቢ እጅ መንሻ በአቅራቢ በኩል ከተሰጠ በኋላ ዞማለም ለመፈታት ችላለች። ጥያቄ የለም። አቤቱታ የለም። ይቅርታ የለም። ፍትህ የለም። ሥልጣንና ጉቦ ቢሻው ያስራል – ባይሻው ይፈታል። ህይወትን በፈቀደው ያዝበታል። በእንዲህ ዓይነት ዓለም የሚኖር ሰው ያለ ቦታው እንደ ኢዮብ «የሰጠ ቢነሳ የለበት ወቀሳ» ቢል ለትዝብት አይዳረግም። እኛም ዞማለምን የፈቱልንን ሰዎች ከማመስገን በቀር ያለፍርድ የተገፈፈውን የእህታችንን ነፃነት በልመናና በጉቦ አስመለስነው ብለን አናማም። ዋናው ነገር ሌላ ወንጀል እስኪቀመር ድረስ እህታችን ለአንድ ሰሞንም ቢሆን ነፃ መሆኗ ነበር። የአንድ ሰሞን ነፃነት! አዎ ህይወት እንዲህ ነው።

በዚህ መልኩ አራቱ የልጅነት ባልንጀሮች መራምባ ውስጥ ከተሰባሰብን በኋላ ታላቁን የአገራችንን በዓል በአንድነት ለማክበርና በኢትዮጵያዊነታችን ጉዞ ላይም ስለገጠመን አንዳችን ለሌሎቻችን የምሥክርነት ቃል ለመስጠት በቃን።

* * *

ጥር 10 ቀን የከተራ በዓል ነው። በዚህ ቀን፣ ከሰዓት በኋላ ዡንበር ስታዘቀዝቅ የመራምባ ሚካኤል ታቦት በካህናቱና በኑዋሪዎቹ ታጅቦ ወደ ጥምቀተ–ባህሩ ይወርዳል። ከዚያም ከሌሎች አምባ ታቦቶች ጋር የጥምቀት በዓልን ካስከበረ በኋላ በሦስተኛው ቀን፣ በእለተ ንግሡ በወጣበት አኳኋን ታጅቦ ወደ ቤተ–ክርስቲያኑ ይመለሳል።

ይህ ክርስትና በመራቤቴ ከተሰበከ ጀምሮ በየዓመቱ ሳይቋረጥ ሲከበር የመጣ ባህል፣ ልምድና እምነት ነው። ለአጠቃላዩ የመርሀቤቴም ሆነ የመራምባ ሰው ከጥምቀት የሚተካከል አውደ–ዓመት ባለመኖሩ እጅግ ደምቆ በጠቅላላ

ህብረተሰብ ተሳታፊነት ይከበራል።

በዚህ ቀን ወላሌና ዞማለም ታቦቱን አጅበው ወደ ጥምቀተ–ባህሩ ለመሄድ በመምረጣቸው እኔና እንባቆም በዓሉን ከከፍተኛ ቦታ ላይ ሆነን ለማየት እንዲያመቸን ወደ መራምባ ኮረብታ ወጣን።

የወጣነው ጠዋት ነው። ታቦቱ ከሰዓት ወጥቶ መጓዝ እስኪጀምር፣ የጉረምሳ ቶክራና ቀረርቶ እስቲያስተጋባ፣ የወዛዝርቱም እልልታ እስኪቀልጥ ድረስ ሁለታችን የምንጫወተው ብዙ ጉዳይ ነበረን።

አባቶቻችን ከብዙ ዓመታት በፊት ተሰቅለውበት ከነበረው ቦታ ጥቂት እልፍ ብሎ ካለ የዋርካ ዛፍ ሥር ቁጭ ካልን በኋላም–

«መራ–ጌታ! እንዴት ነው ክራሞትህ?» አልኩት። እንባቆምን የምንጠራው «መራ–ጌታ» ብለን ነው።

«አይ ወንድሜ፣ መራ–ሃይማኖት! ምን ብዬ ልንገርህ፣ እንዴት ላውጋህ? አከራረሜ በምን ቋንቋ ይነገራል። የእኔ ክራሞት የተጉለጉለ ልቃቂት ነው፣ መቋጠሪያ የሌለው፣ ውሉ የጠፋበት» አለና በትካዜ ከኮረብታው ባሻገር አርቆ ይመለከት ጀመር።

«እስኪ የቅርቡን ሞክረው» አልኩት።

«የቅርቡ የሚጀምረው ከሩቁ ነው። የሩቁም ከቅርቡ ይጀምራል። መላው የጠፋበት ህይወት» አለና በድጋሚ ፀጥ አለ። ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ በረጅሙ ተነፈሰና ኢትዮጵያዊነትን እሱ እንዳየው ሊያወጋኝ ተነሳ።

እነሆ እንደበቱም ይናገር ዘንድ ተከፈተ።

«ያን ጊዜ አብዮቱ ሲፈነዳ አንተ ወደ ውጭ አገር ሄድህ። ወላሌ መኩንን ስለነበር ከአብዮቱ ጋር ቆመ። ዞማለም ደግሞ በመኩንኖቹ ጉን ሌላ አብዮት ለማካሄድ ከእህአፓ ድርጅት ጋር ተሰለፈች።

እኔ ምንጊዜም ምኞቴ ወደ አባቴ አገር ለመመለስ

ስለነበር ከተማን ወደኋላ በመተው የእግሬን ትቢያ አራግፌ እዚሁ መራምባ መጣሁ። ለመምጣት ያነሳሳኝ የመሬት አዋጅ ነው። አዋጁ ቀደም ሲል በአገራችን የነበረውን የመሬት አያያዝና ከዚህ ይመነጭ የነበረውን በደል በማስወገድ ለማንኛውም ገበሬ የእርሻ መሬት በነፃ ለመስጠት ቃል ገብቷል።

እንደእኔ ርስት መሬት እያጣን ወይንም የአባቶቻችንን ርስት እንበለ-ፍትህ እየተቀማን በገዛ አገራችን መሬት-የለሽ ለሆንን ታላቅ ሽረት ነበር። እንደምታስታውሰው፣ ከመንደሬ ወደ ከተማ የገባሁት፣ በአስኳላ ትምህርት የደከምኩት፣ ኑሮዬን ለመለወጥ ለራሴም ከአገር የተለየ እድገት ፈልጌ አልነበረም። የመሬት ማጣት ነው ከመንደሬ ያሰደደኝ። እትብቴ ከተቀበረበት የአባቴ እምባ አውጥቶ የጣለኝ የመሬት ጉዳይ ነበር።

ዛዲያ መሬት መሬት ለሌለው ይሰጣል ሲባል ምንም ሳላንገራግርና ጥርጣሬ ሳይኖረኝ ከተማውን ለተወላዶቹ ትቼ እኔ እንደአባቴ፣ በሬ ጠምጄ፣ እርፍ ጨብጬ፣ አፈር ገፍቼ ልኖር መጣሁ። የምመኘው ስለነበር መሬት-ለአራሹ ሲባል በህይወቴ ታምር ያየሁ ነበር የመሰለኝ።

እንደተመለስኩ የመንደሩ ሰው ሁሉ ተወላጅ መሆኔን መሰከረልኝና የእርሻ መሬት ተለክቶ ተሰጠኝ። ሰውም ተባብሮ ቤት ሰራልኝና ማለፊያ ጐጆ ውስጥ ገባሁ። ጉልላቱ ያማረ፣ የጠዳ፣ ማለፊያ ቤት ነበር።

የመጀመሪያውን ዓመት ለብቻዬም፣ በደቦም እርሼ ብዙ ጭነት ማሽላ ነበር ጐተራ ያገባሁት። ከጤፉም ወደ ገበያ የሚወጣ ያህል አምርቻለሁ። እኔ ብቻ ሳልሆን በዚያ በመጀመሪያው ዓመት የእርሻ መሬት ከፍፍልና በተገኘውም አዝመራ የተደሰተው አገር ሁሳ ነበር። ገበሬው አበጅቶ ሸረል።

በየቤቱ ጥጋብና ደስታ ነበር። ብዙም ወጣት ሽር ያለ ድግስ እየተደገሰለት ተድሯል። የእኛ አገር፣ ማሽላ ሲተርፍ ሠርጉን መደገስ ነው!!

ታዲያማ ወንድሜ፣ መራ ሃይማኖት-

የእኔም ሆነ የአገሬው ደስታ ዘላቂ አልነበረም። መንግሥት እጁን ዘረጋና ደስታችንን ሁሉ በጥብጦ አተላ አደረገው። አበለሻሸው።

ልክ በዓመቱ የገበሬ ማህበር ምረጡና ተደራጁ የሚል ትዕዛዝ መጣብን። እኛም መደራጀት መልካም፣ ምን ችግር አለ ብለን ተደራጀን። ለማህበሩ መሪ የሚሆኑም የተከበሩ የመንደሩን ሰዎች መራረጥን።

ታዲያ ነገሩ እኛ እንዳልነው የሚሆን አልነበረም። በአንድ የአስር አለቃ የሚመሩ የከተማ ገበሬ ማህበር አቋቋሚዎች መጡና እኛ ያቋቋምነውን ማህበር አፍርሰው ሌላ አዲስ ማህበር አቋቋሙ። የማህበሩ ሹማምንት የሚሆኑትንም ራሳቸው መረጡና እነዚህ ናቸው አለቆቻችሁ ተስማምታችኋል አሉን። በትዕዛዝ ተስማምታችኋል አሉን።

ችግሩ ከዚህ ይጀምራል። የከተማው ሹማምንት እኛን ለመግዛት፣ ለማሰራትና ለመቅረጥ እንዲያመቻቸው ለእነሱ በሙሉ ልብ የሚገዙትን ሰዎች እየመረጡ ነው የሾሙብን። በዚህም የመንደሩ ስመ-ጥሩ ሽማግሌ፣ ወጣት፣ አሮጊት፣ እያለ አርሶ የማይበላውን፣ ነግዶ የማያተርፈውን፣ ተናግሮ የማያሳምረውን የአገር አውደልዳይና ባለጌ አለቃ እያረጉ ሾሙብን። እነዚህ ቀን ያነሳቸው ምግባረ-እኩይ ሰዎችም በማን-አለብኝነት ቀለዱብን።

በመጀመሪያ፣ መንግሥት የእርሻ መሬት እንደገና አከፋፍሉ ብሏል ብለው የአገሩን መሬት ሁሉ በሥራቸው አደረጉት። ከዚህ መሬት ላይ ደህና የሆነውን ለሙን መሬት እየመረጡ «የህብረት እርሻ» ብለው ሰየሙት።

ከዚህ የተረፈውን ትንሽ ለምነት ያለውን መሬት ያለ እፍረት ጉቦ እየጠየቁ ጠቦት፣ ሙክትና፣ ወይፈን ለጐተተላቸው ሰጡት።

የቀረነው የበሬ ግንባር የምታህል የማታፈራ ጭንጫ መሬት እየተሸነሸነች ተሰጠችን። መሬት በነፃ ህልምና ተዓምር መሆኑ ቀርቶም ቅዠት ሆነ። የሚያስፈራ ቅዠት።

እየውማ እንግዲህ፣ አሁን ሰው እንዴት ድንጋይ ላይ አርሶ ያመርታል ተብሎ ነው። ያውም እኮ ቢታረስ ነው።

ለማረስስ ጊዜው የት ተገኘ ብለህ።

«የህብረት እርሻ» ብለው የወሰዱትን መሬት እንድናርስ፣ እንድንዘራ፣ እንድናርም፣ እንድንወቃ፣ የታዘዝነው እኛው ገበሬዎቹ ነን። «የህብረቱ እርሻ» ምርት ከትንሽ እስከ ትልቅ ጉልበታችን ደክሞበት ከተሰበሰበ በኋላ በአጋሰስ እየተጫነ ወደ ከተማ ይሄዳል። የአብዮቱ ቀለብ ነው። እኛ እሸት እንኳ አንጠረጥርለትም።

አሳራችን በዚህ አላበቃም። ከህብረቱ እርሻ» ስንመለስ የማህበር ስብሰባ ብለው ይጠሩናል። ማህበሩ ደግሞ ብዙ ነው። የገበሬ ማህበር ስብሰባ አለ። የሴቶች ማህበር ስብሰባ አለ። የወጣቶች ማህበር ስብሰባ አለ። በስብሰባ ያልታሰረ ማንም የለም። በነጋ በጠባ እየተሰበሰብን ከላይ ከመንግስት የሚመጣውን ዲስኩር እንሰማለን። እንዲያው ያታክቱናል እንጂ አይገባንም።

የምንገብረው ግብር አይነቱ ብዙ ነው። የመሬት ግብር አለ፣ የእናት አገር ጥሪ ግብር አለ፣ የየማህበሩ ግብር አለ፣ ብቻ ምን አደከመህ ዝንበር በወጣች ቁጥር ግብር አግቡ ሆነ።

የግብሩ አከፋፈል ደግሞ ሌላ ራሱን የቻለ የበደል ዳውላ ነው።

መንግሥት ግብሩን በእህል በቁና ሰፍሮ አይቀበልም። በከብትም አይቀበልም። በጉልበት ስራም አይቀበልም። የፈለገው ገንዘብ ብቻ ነበር። ግብር በብር አግቡ ተብለን ተገደድን።

ታዲያ ብሩ ከየት ይመጣል? እኛ ገበሬዎች እንጅ ደሞዝ የሚቆረጥልን ሠራተኞች አይደለን። አሳቡ ያችን ጭረን ያመረትናትን እህል ከቀለባችን እየነፈግን ገበያ እንድናወጣና ሸጠን ብሩን እንድንገብር ነው። እህል በጉተራ ቀርቶ በቅል ከቤት እንዳይቀመጥ።

ለነገሩ የምንሸጠውን ነገር፣ እህልም ሆነ ከብት ገበያ አውጥተን ባወጣው ብንሸጠው ደግ ነበር። እንደድሮው ከተማ አውጥተን አለያም ወንዜ ተሻግረን ሄደን ውድ በሆነበት ዋጋ ብንሸጠው ትንሽ እናገኝበት ነበር። ለእኛ ትርፍ እንዲኖረን

ሳይሆን ጥቂት ከቤት የምንበላው እህል እንዲተርፈን።

ታዲያ መንግሥት፣ «የለም፣ ገበያ ወስዳችሁ ለገዥ አትሸጡም። ይኼ የመንግሥት ሥራ ነው። እናንተ እህላችሁንም ሆነ ከብታችሁን እያመጣችሁ «የእርሻ ሰብል ገበያ» ለሚባል የመንግሥት ድርጅት ብቻ ሽጡ አለን። እሱ ለእኛ የሚሰጠን ዋጋ ለግብር የሚበቃም አልነበር። መንግሥት ከእኛ በግዳጅ በርካሽ ይገዛና ወስዶ በትርፍ ትርፍ ይሸጠዋል። እኛም ያንኑ በርካሽ የሸጥንለትን ነገር፣ ከብትም ይሁን እህል እንግዛ ብንል እንዲሁ አትርፎ ይሸጥልናል። ነገሩ እንዲያው መላ የሌለው ነው። ሰው እንዴት ንብረቱን በርካሽ ሸጦ እንደገና ያንኑ ንብረት ከሸጠለት ሰው በውድ ዋጋ ይገዛል።

እንዲህ እየሆን ትንሽ ጊዜ ከገፋን በኋላ ደግሞ ሌላ ቤተሰባችንን የሚያስጨንቅ ነገር መጣ። ይኸውም «የእናት አገር ጥሪ» የተባለው ብሔራዊ ውትድርና ጉዳይ ነው።

አገር ከውስጥና ከውጭ በጠላት ተከባለችና ወንድ የሆንክ ሁሉ ተነስ ለእናት ሀገርህ ተባለ። እስካሁን የገበርከው የላብህ ዋጋ አይበቃምና ደምና ህይወትህን ገብር መሆኑ ነው።

ይህ በአዋጅ በተነገረ ሰሞን ከከተማ ወታደር መልማዮች በየመንደሩ እየሄዱ ጤናማውን ሁሉ እያጋዙ ወሰዱት። የቀረ ወጣት አንድም በመንደራችን የለም። አንዳንድ አንሄድም እያሉ በየገደሉ፣ በየዋሻው የተደበቁት እንኳ እንደቀበሮ እየታደኑ ተይዘው ከቅጣት ጋር ተወሰዱ።

የእኔም አንድና ብቸኛ ወንድ ልጄ፣ ምትኬ፣ ክንዴ፣ የስሜ መጠርያ፣ የዘር ወራሼ ከጉያየ በግድ ተነጥቆ የተወሰደው ያኔ ነበር። እንደወጣ ቀረ። ዋ ልጄ!

አየህ፣ ወዳጄ፣ መራ–ሃይማኖት–

መንግሥት እንዲህ የእርሻ መሬት በማሳጣት፣ አርሰን እንዳንበላ ጊዜያችንን በየምክንያቱ በማባከን፣ የደከምንበትን ዋጋ እያሳጣ፣ ከሁሉም በላይ አርሶ መኖር የሚችለውን ጤናማውን ገበሬ እያስገደደ ጦርነት በመውሰድ ደረጃ በደረጃ አመቻችቶ ነው ለታላቁ ጠኔ የሰጠን።

ታላቁ ጠኔ ከመምጣቱ በፊት በመርሀቤቴ በሞላው

ረሀብ ነበር። ተጠግቦ የታደረበት አንድም ቤት አይገኝ። ባቋላ ተቆርጥማ ለሁለት እየተካፈልን ነው የኖርነው።

የጠኔው ዳመና በመርሀቤቴ ሰማይ ባንጃበበ ጊዜም የእልቅት ድምፅ ያልተሰማበት ቤት የለም። መልአከ–ሞት የእያንዳንዱን ገበሬ ቤት በጭካኔ እየበረገደ ህፃኑን፣ ሽማግሌውን፣ አሮጊቱን፣ ከብቱን በሞላ ወሰደው። አልቅሶ ለመቅበር እንኳ አቅም የነበረው ሰው አልነበረም። የእኔም የአይን ብርሃንና ሲቷ ልጄ እንባለ–ማርያም እንደታቀፍኳት ህቅ–ብላ የቀረችው ያኔ ነበር።

የሰው ልጅ አፅም በየቤቱ፣ በየደጃፉ፣ በየመንገዱ ወድቆ ቀረ። የመከራ ዘመን የገበሬ ቤተሰብ እልቂት!

ብዙ ህዝብ ካለቀ በኋላ ጥቂት አቅም የነበረን ርዳታ ፍለጋ እየተጐተትን ወደ አለም ከተማ ወጣን። ከዚያም እንደደረስን ከተማውን እንደእኛ ከአውራጃው በሙሉ የመጣ ርዳታ ፈላጊ አጨናንቆት አገኘነው።

ለአንድ ሣምንት ያህል እዚያው ዳቦውንም ብስኩቱንም ነፍሳችን እንድትቆይ ያህል እያቃመሱን ከቆየን በኋላ ለም ወደሆነ አገር ለሰፈራ ትሄዳላችሁ ብለው ነገሩን።

ብዙው ሰው የአባት፣ የእናት አገራችንን ጥለን የትም አንሄድም። ብንሞትም፣ ብንኖርም በአገራችን እንጂ ሌላ አገር መሄድ አይሻንም ብሎ አጉረመረመ። ታዲያ አቅም የሌለው ደካማ ህዝብ ማጉረምረም ምን ፋይዳ አለው። ሮጦ እንኳ ለማምለጥ የሚችል አንድም ሰው አልነበር። ጉልበት ያለው መንግሥት ብቻ ነው። ጉልበተኛም የፈቀደውን ያደርግ ዘንድ የታወቀ ነው። አደረገም።

ታዲማ፣ ይኸውልህ ወንድሜ፣

ታላቁ ጠኔ በጀመረ በሁለተኛው ዓመት ላይ በግንቦት ወር ታላቅ የጭነት መኪናዎችና አውቶብሶች መጥተው በዓለም ከተማ የተገኘውን ተረጅ በሞላ እየጠራረጉ ወሰዱት። ሰው አትውሰዱን እያለ ብዙ ግርግር፣ ኡኡታ ተፈጥሮ ነበር።

ድካሜን፣ መራቤን አይታችሁ ሳልሞት ከአገሬ አትውሰዱኝ ብሎ ሰው ጮኸ። እግዚዎ አለ። ማ ቢሰማው! የሚሰማ መንግሥትም ሆነ አምላክ ያልነበረበት ጊዜ ነው።

በግርግሩ መካከል አንዳንድ ከሞት የተረፉ ቤተሰቦችም እንኳ ተለያዩ። እናት ባንዱ መኪና ተገዳ ትጫናለች፣ ልጅ በሌላ ተጭኖ ይሄዳል። ሄዶ መድረሻው ደሞ የተለያየ ስለነበር ጠኔ ያለየውን ቤተሰብ መንግሥት በሰፈራ ለያየው። የአገራችን ሰው እንደ በጋ ደመና በያለበት ተበተነ።

እኔ የነበርኩበት አውቶቡስ ከሌሎች ሦስት አውቶቡሶች ጋር ተከታትሎ የሄደው ወለጋ ውስጥ አሶሳ ከሚባል የጠረፍ ቦታ ነው። ከያ ለመድረስ ሦስት ቀን ተጉዘናል። በዚያው በጉዞ ላይም አውቶቡሱ ላይ እየሞተ በየመንገዱ የተቀበረው ብዙ ነው። የፍዳ ዘመን።

አሶሳ እንደደረስን ከየሀገሩ የመጡ እንደኛው ያሉ ተረጅዎች አገኘን። ከወሎ የወጡ ነበሩ። ከትግራይ የመጡ ነበሩ። ከከምባታ የመጡ ነበሩ። ከሲዳሞና ከባሌም የመጡ ነበሩ። መቸም በታላቅ ጠኔ ዘመን በረሀብ ቸነፈር ያልተቀጣ የለም።

እኛ ከተለያዩ አገሮች የመጣነው ረሀብተኞች በአሶሳ ውስጥ ጐጆ እየተሰጠን አዲስ ኑሮ ጀመርን።

አገሩ በውነቱ ለም ነው። ሌላ እህል ባይሞክርበትም የዘሩትን እጥፍ–ድርብ አርጐ በቆሎ ያመርታል። ያገሬው የወለጋ ሰው ቀለቡ ለጥቆ በቆሎ ነው።

ካነሳሁት አይቀር፣ ያገሬው ሰው፣ ወለጋው እንዴት ያለ መልካም ህዝብ መሰለህ። ደግ፣ አዛኝ፣ እንግዳ ተቀባይ ነው። መላው ወለጋው አረሞ ነው። ታዲያ እኛ ተቸግረን አገሩ ስንሄድ ቤታችንን እየሰራ፣ ከብቱን እያመጣ እየሰጠ፣ ወተቱን–ቅቤውን እያመጣ ከችሞ አስተናገደን። እግዚሩና መንግሥት የነፈገንን ድሃው ወለጌ አብቸነቸነን። እንዲያው በህይወት የቆየነው በዚሁ በደጉ አረሞ ድጋፍ ነው። አመስግኜ አልዘልቀውም።

ታዲያ ምን ያደርጋል፣ የእልቂት መጋረጃ ገና አልተዘጋም ነበርና ፍጻሜያችን ለእሳት ሆነ አለና መራ–ጌታ እንባቆም ሁለት አይኖቹን በእጆቹ ሸፍኖ በተቀመጠበት ወደፊትና ወደኋላ እያዋዠቀ በፀጥታ ተቀመጠ።

እኔም እስካሁን ከነገረኝ የባሰ ሀዘን ትዝታ ላይ

እንደደረሰ ከሁኔታው በመገንዘብ ሳልናገር አቀርቅሬ ዝም አልኩ። የፀጥታው ጊዜ እየረዘመ በመሄዱ የሀዘን ትዝታውን ለማስተው የሆነ ነገር መናገር ፈለግሁ። የምናገረው ነገር ግን ፈፅሞ በአእምሮዬ ሊመጣልኝ አልቻለም።

በዚህ ሁኔታ ትንሽ ጊዜ ካሳለፍን በኋላ፣ መራ–ጌታ እንባቆም በከባዱ ተንፍሶ ያየውን ሰቆቃ መደምደሚያ ይናገር ዘንድ ጀመረ።

“ቀኑ አርብ ነበር፣ እለቱ ቂርቆስ። ካልጠፋ ቀን ያ የመከራ ቀን ለምን አርብ፣ የቂርቆስ እለት እንደዋለ አላውቅም። ምናልባት እኔ የማላውቀው የረቀቀ ምስጢር ይኖረዋል ወይም የአጋንንት ልጆች ለጥፋት የሚዘምቱት በዚያ እለት ይሆናል። አላውቅም።

ክርስቶስ የተሰቀለው አርብ ነው። ህፃኑ ቂርቆስም በአረማውያን በእሳት ነዷል። በዚህ መከራ በተገጣጠመበት፣ የመከራ መዘከሪያ ቀን ነው የእኛም መከራ የመጣው።

ታዲያ በዚያ እለት፣ ሁልጊዜም እንደማደርገው ማለዳ ገና ዠንበር ሳትወጣ ከመኝታዬ ተነሳሁና ወደዚያው ወደ ህብረት እርሻችን አመራሁ። ጊዜው የአረም ጊዜ ስለነበር አካሄዴ ለማረም ነው። ከሰው ሁሉ በፊት እርሻ የምገኘው እኔ ነኝ። ይህም እኔ ከሰው በላይ ሥራ ወድጄ ሳይሆን የእንቅልፍ ችግር አለብኝ። ሌሊቱ አይተኛልኝም። እንቅልፍ ካልወሰደ ደግሞ ቁንጫና ትኋኑ አያስተኛም። ስለዚህ በጠዋት እነሳና ወደሥራ እሄዳለሁ።

ረፋዳው ላይ ሲሆን የመንደሩ ሰው በሞላ ይመጣል። ያንጊዜ ነው የገበሬ ማህበር ፀሐፊው መዝገቡን ይዞ ይመጣና ያልመጣውን የሚቆጣጠረው።

በዚያ በአርብ ቀን፣ በእለተ–ቂርቆስ ግን እንደተለመደው ረፋዳው ላይ የመንደሩ ሰው ለሥራው ሳይመጣ ቀረ። መዝገብ ያዡውም አልመጣ። የት ሄዱ ብዬ ጥቂት ማሰቤም አልቀረ። ከአሁን አሁን ይመጣሉ ብዬ ብጠብቅም እስከ እኩለ ቀን ድረስ አንድም ሰው ዝር አልል አለ።

ታዲያ፣ አይ ምናልባት እኔ ሳልሰማ የሠፈሬ ስብሰባ

ተጠርቶ ይሆናልና የትሄድህ እንዳልባል ወደ ቤት ልመለስ አልኩና አረሜን ትቼ ወደ መንደራችን ጉዞ ጀመርኩ።

ወደመንደራችን ስዳረስ ለየት ያለ ሁኔታ በሩቅ ተመለከትሁ። ነገሩ ምን እንደሆነ አላወቅሁም። ልቤ ግን ተጨንቋል። ቀስ ብዬ ወደ መንደሩ ተጠጋሁና ሁሉንም ከቅርብ ከሚያሳይና የሚነገረውንም ከሚያሰማ ቦታ ላይ ቁጥቋጦ ውስጥ ቁጭ አልኩና መመልከት ጀመርኩ።

የመንደሩ ሰው ወንዱም፣ ሴቱም ልጁም ሁሉ ወጥቶ ሜዳው ላይ ተሰብስቧል። ከሌሎች መንደሮችም የመጡ ሠፋሪዎች ስላሉ ቁጥራቸው በብዙ መቶ የሚቆጠር ነው።

ሠፋሪው ዙሪያውን የተለያየ ጠመንጃ በታጠቁ ሰዎች ተከቧል። ታጣቂዎቹ የገበሬ ማህበር አብዮት ጠባቂዎች አይደሉም። አንዳቸውንም አላውቃቸውም። የመንግስት ወታደሮች አይመስሉም። የመንግስት ወታደሮች ሁልጊዜ በየምክንያቱ ስለሚመጡ በአለባበሳቸውና በሁኔታቸው እናውቃቸዋለን።

እነዚህ ሠፋሪውን የከበቡት ታጣቂዎች ትጥቃቸውና ሁኔታቸው እንደወታደር ሳይሆን እንደ ሽፍታ ነው። ቁምጣ የታጠቁ፣ ባርኔጣ ያደረጉና ያላደረጉ፣ ኮት የለበሱና ያልለበሱ አሉባቸው። የብዙዎቹ የራስ ፀጉር ጉፈሬ ነው። አንዳንድ ፀጉራቸውን የተላጩም አሉባቸው።

ሠፋሪው በሞላ በእነዚህ ታጣቂዎች ዙሪያውን ተከቦ እንደመንጋ ቆሟል። ሌሎች ታጣቂዎች በየቤቱ እየሄዱ የተኙውን ሰው እየገፈተሩ ያመጡና ከስብስቡ ይጨምራሉ።

ይህን ሁኔታ ለግማሽ ሰዓት ያህል ከተመለከትሁ በኋላ አራት ብረት የያዙ ሰዎች በሌሎች ብረት በታጠቁ ሰዎች ታጅበው በተርታ ቁመው ከነበሩት አራት የጭነት መኪናዎች ከአንደኛው ሲወጡና ወደተሰበሰበው ሰው ሲሄዱ አየሁ።

እነዚህ አራቱ ሰዎች በሁኔታቸውና በአጀባቸው የታጣቂዎቹ አለቆች ይመስላሉ።

ከተሰበሰበው ሰው እንደደረሱም አንደኛው አለቃ መናገር ጀመረ። ንግግሩ አልተሰማኝም። ትንሽ ከተናገረ በኋላ ትዕዛዝ የሰጠ መሰለኝ። ከተሰበሰቡት ሰዎች መካከል ከፊል

የሚሆኑት ከሌሎቹ ተለይተው ወደፊት በመውጣት ተለይተው ሲቆሙ አየሁ።

አለቃው ስም እየጠራ የለያቸው አልመሰለኝም። ለምን እንደተለዩና ምን ብሎስ እንደለያቸው አላውቅም። ቀደም ሲል የተሰበሰበውን ሰው ከበው የነበሩት ሰዎች በፍጥነት ራመድ ራመድ እያሉ እነዚህን ተለይተው እንዲቆሙ የታዘዙትን ሲከቡ ተመለከትኩ።

ወዲያው አለቃው ቀደም ሲል ከነበረው ተሰብሳቢ መካከል ተለይተው እንዲቆሙ ላልታዘዙት ንግግር ካደረገ በኋላ ወደቤታቸው እንዲሄዱ ነገራቸው።

በአስቸኳይ ወደየቤታቸው እንዲሄዱና በራቸውንም እንዲዘጉ የታዘዙ ይመስላል፣ ሁሉም ሮጥ፣ ሮጥ፣ እያሉ ወደቤታቸው ሲሄዱና በሮቻቸውን ሲዘጉ አየሁ።

ከዚህ በኋላም ጥቂት ፀጥታ ሰፈነ። ተለይተው የቆሙት ሰዎች አሁንም እንደተከበቡ ናቸው። አለቆቹ ታጅበው በድጋሚ ወደመኪናቸው ሄዱ።

ለብቻ የቆሙትን ሰዎች አንድ በአንድ አተኩሬ መመልከት ጀመርኩ። ህፃናት ልጆች የታቀፉ እናቶች አሉ። በእናትና አባቶቻቸው እግር ስር ቁመው ወይም ቁጭ ብለው የሚሆነውን ምናልባት እንደ እኔ በመገረም የሚመለከቱ ሌሎች ነፍስ ያላወቁ ህፃናትም ነበሩ።

እረኞችም ነበሩባቸው። ሁሉንም አንድ በአንድ አውቃቸዋለሁ። እንዲያውም እኔ ዘንድ እየመጡ ስለአባቶቻቸው አገር ወሬና ተረት መስማት የሚወዱ እረኞች ናቸው። ከብሔራዊ ውትድርና መቅሰፍት ካመለጡ ማለፊያ ገበሬዎች የሚሆኑ ናቸው።

በተወለዱበት አገር ከመንግስት በደል አንስቶ እስከጠኔ ድረስ ብዙ መከራ ያዩ የገበሬ አባወራዎችም ከተሰበሰቡት መካከል ነበሩ። ከብዙዎቹ ጋር ሀዘንም ደስታም አብረን ተካፍለናል።

የደከሙ ሽማግሌዎችና አሮጊቶችም አብረው ቆመዋል። አንድ ከማርጀታቸው የተነሳ ከቦታ ቦታ እያዘልን የምንወስዳቸው ሽማግሌ ሰውየም እንኳ ነበሩ። ከመቶ ዓመት

በላይ ይሆናቸዋል። እሳቸውም ከቤታቸው ወጥተው እዚሁ ቆመዋል።

የተሰበሰቡትን ሰዎች አንድ በአንድ አይቼ ስጨርስ መንስዔው ምን እንደሆነ ያላወቅሁት ስጋትና ፍርሃት ሰውነቴን ወረረው። ለምን ተለይተው ሰበሰቧቸው ብዬ ራሴን ደጋግሜ መጠየቅ ጀመርኩ። መልስ ባለማግኘቴም ደግ ደጉን ማሰብ ጀመርኩ።

ምናልባት የረሀቡ ዘመን ስላለፈ ወደየመጡበት አገር ሊመልሳቸው ይሆናል፣ አለያም ወደ ሌላ ቦታ ሊያሰፍሯቸው ይሆናል ብዬ ራሴን ለማፅናናት ሞከርኩ። መፅናናት ግን አልተቻለም። መረበሼና የልቤ ትርታ እንደከበሮ መምታቱ ባሰበት።

በድጋሚ ሰዎቹን ተመለከትኩና ከሌሎቹ ያስለያቸው ምን እንደሆነ ለማወቅ ሞከርኩ። እኔ እስከማውቀው ድረስ ሰፋሪው በሙሉ ከረሀብ ሞት የተረፈና ከየትውልድ አገሩ ተገዶ በሰፋሪነት የመጣ ነው። በመከራ የተሳሰረ ህዝብ ነው። ያንዱ ሰፋሪ የሰቆቃ መዝገብ ከሌላው ይበዛል የማይባል ሁሉም ራሱን የቻለ ዘግናኝ ነው። ታዲያ መለየትን ምን አመጣው?

ትንሽ በሀሳብ ላይ እንዳለሁ አንድ ካሁን ቀደም በአእምሮዬ ውል ብሎ የማያውቅ ነገር ከፊቴ ድቅን አለ። እነዚህን የተለዩትን ሰዎች ከሌሎቹ የሚለያቸው የመጡበት አገር ይሆናል አልኩ። ሰዎቹን በከፍል በከፍል እያደረግሁ የመጡበትን አገር በአእምሮዬ መደብኩት።

ከፊሉ፣ ከጐንደርና ከጐጃም የመጡ ናቸው። ከፊሉ ከወሎ ውስጥ ከተለያየ ቦታ የመጡ ናቸው። ከፊሉም እንደ መራቤቴ ካለው የሰሜን ሸዋ ግዛት የመጡ ናቸው።

ሌሎች ምድብ ውስጥ የማይገቡ ከተለያየ አገር የመጡም አንዳንድ አሉ።

ሁሉንም የሚያገናኛቸው ቋንቋቸው አማርኛ መሆኑ ብቻ ነው። ያው አማርኛቸውም ቢሆን ለውጭ ተመልካች እንጅ ለሰዎቹ አንድ ነው ሊባል አይችልም።

ሌሎቹ ወደየቤታቸው እንዲሄዱ የተነገራቸው አማርኛ

ተናጋሪ ቢሆኑም ሌላ የእናት–አባት ቋንቋም ይናገራሉ።

ይህን ሁኔታ በአእምሮዬ ከደመደምኩ በኋላ ምክንያቱን ማሰባሰብ ስጀምር ቀደም ሲል ወደ መኪና ከሄዱት የታጣቂዎቹ አለቆች መካከል አንደኛው ወደተሰበሰቡት ሰዎች ሲመጣ አየሁት።

ትንሽ ንግግር ካደረገ በኋላም የተሰበሰቡትን ሰዎች ወደ ገበሬ ማህበሩ አዳራሽ እንዲሄዱ አዘዛቸው። ዙርያውን ከበው የነበሩት ታጣቂዎች ሰዎቹን ከፊት አስቀድመው ወደ አዳራሹ ሲወስዷቸው ተመለከትኩ።

ሰዎቹ አዳራሹ ከገቡ በኋላ በሩ ከውጭ በኩል ተዘጋ። ህፃናቱም፣ ወጣቱም፣ ወንዱም፣ ሴቱም፣ ሽማግሌውም አሮጊቱም አብሮ ታጉሮ ተዘጋበት። ከዚያ በኋላ ታጣቂዎቹ አዳራሹን ከበው ቆሙና ሌላ አንድ ሰዓት ያህል ቆዩ። አለቆቹ መኪና ውስጥ ምክክር የያዙ ይመስላል። ነገሩ አልገባኝም።

በመጨረሻው አራቱም አለቆች ከመኪናው ወጡና ሰዎቹ ተሰብስበው ከነበሩበት ቦታ ላይ ቆሙ። ወዲያው ከአንደኛው መኪና ላይ ታጣቂዎቹ ተለቅ ተለቅ ባለ ጀሪካ የሆነ ነገር ይዘው ወደ አዳራሹ አመሩ። ከዚያም እንደደረሱ ሁለቱ ታጣቂዎች አንዳንድ ጀሪካ እየያዙ በመሰላል አዳራሹ ጣርያ ላይ ወጡና የያዙትን ማርከፍከፍ ጀመሩ። ሌሎቹ ከታች የነበሩት ታጣቂዎችም እንዲሁ የያዙትን በአዳራሹ ዙሪያ አርከፈከፉት።

ይህ ከሆነ በኋላ ታጣቂዎቹ ከአዳራሹ ራቅ ራቅ እያሉ መሳሪያቸውን ደግነው ቆሙ።

ሜዳው ላይ ቆመው የነበሩት አራቱ የታጣቂ አለቆች ወደ አዳራሹ አመሩና እያንዳንዳቸው በአዳራሹ አራት ማዕዘን ቆሙ። በሰሜን፣ በደቡብ፣ በምሥራቅ፣ በምዕራብ። ከዚያም ታጣቂዎቹ ለእያንዳንዱ አለቃ እንደ ችቦ ያለ ነገር እያመጡ ሰጡና ወደቦታቸው ሄደው ቆሙ።

አራቱ አለቆች በአንድነት ከኪሳቸው ክብሪት እያወጡ ችቦውን ለኮሱና በተመሳሳይ እርምጃ ወደ አዳራሹ ተጠግተው በየፊናቸው ያለውን የአዳራሽ ማዕዘን ለኮሱት።

አለቆቹ አዳራሹን ለኩሰው ወደ ኋላ ራቅ ብለው

ሲቆሙ የእሳቱ ነበልባል ከመቅፅበት አዳረሰው። ወዲያውም ዙርያውን ከበው የነበሩት ታጣቂዎች በእሳት በመጋየት ላይ በነበረው አዳራሽ ላይ ከየአቅጣጫው የተኩስ እሩምታ ከፈቱበት።

ከዚህ በኋላ የሆነውን አላስታውስም ራሴን ስቼ ወድቄያለሁ። አይኔም አላየም፣ ጆሮዬም አልሰማም።

ራሴን ስቼ ከወደቅሁበት ከዚያች ቁጥቋጦ ውስጥ የነቃሁት ከብዙ ሰዓት በኋላ ዡንበር ልትጠልቅ ስትል ነው።

ያየሁትም ታወሰኝና ከቁጥቋጦው ወጥቼ ወደ መንደሩ አመራሁ። ብዙ ሰው ተቃጥሎ አመድ የሆነውን አዳራሽ በፀጥታ ከቦ ቆሟል። ከበው በሀዘን ከቆሙት መካከል ከትግራይ፣ ከከምባታ፣ ከሐረርና ከባሌ የመጡ ሠፋሪዎች አሉ። ከሰፈራው ውጭ ካሉ መንደሮች የመጡ የአገሩ ተወላጅ የሆኑ የወለጋ ገበሬዎችም ነበሩ።

አንገቴን አቀርቅሬ ወደተሰበሰበው ሰው እንደተጠጋሁ ሁሉም አይኑን ወደ እኔ አዞረና በድንጋጤ ተመለከተኝ። ምናልባት የሙት መንፈስ የሚያዩ ካልሆነ በቀር ከእሳት መትረፌን ማመን አዳጋች ነበር። የሆነውን ሁሉም ያውቃሉ። እድሌ ከተቃጠሉት ሰዎች ጋር እንደነበርም አይስቱትም።

ሰዎቹ ገለል ገለል ሲሉልኝ ወደተቃጠለው አዳራሽ ተጠጋሁ። ከአመድ በቀር የተረፈ አንድም ነገር አልነበር። አመዱ ካለበት ቦታ በእሳት የተቃጠለ፣ የተኮማተረ የሰው ሥጋ ከሩቅ ይሸታል፣ ይጨሳል፣ ይንጣጣል። የአብዛኛው ሰው ሥጋ በሞላ ተቃጥሎ የሚታየው የአፅም ስብስብ ነው። አስፈሪ የአፅም ስብስብ። የእኔም ባለቤት፣ የልጆቼ እናት፣ የሀዘንና የደስታ ተካፋዬ በዚያ እሳት አመድ ሆነች። ተቃጠለች፣ ነደደች፣ ጓዴ ወርቀዘቦ በእሳት ቀለጠች።

በመሰረቱ በዚያን ሰዓት የሚሰማኝ ይህ ነበር ማለት አልችልም። ስሜት የሚባል ነገር በሰውነቴ አልነበረም። በድን ሆኛለሁ። ዙርያውን የነበሩትን ሰዎች ቀና እያልኩ ተመለከትኩ። አንድ እንኳ ያላቀረቀረ አልነበረም። ወንዱም ሴቱም በፀጥታ እንባውን ያዘራል፣ ያለቅሳል። የለቅሶውን ምክንያት የሚያውቀው አልቃሹ ነው።

እኔ በመፍዘዝ፣ ሰው በፀጥታ በማልቀስ ላይ እንደቆየን ጊዜው መሽቶ ለአይን መያዝ ሲጀምር አንድ ሰው መጥቶ እጄን ትከሻዬ ላይ አርጐ ወደ ዳር ይዞኝ ወጣ።

ከዚያም ከመጣበት በቅሎ ላይ ከአንድ ሌላ ሰው ጋር ተረዳድተው አስቀመጡኝና እሱ በቅሎውን እየጐተተ ከመንደሩ ወጥተን አመራን።

የሄድነው አንድ አያና ዋቅጅራ የሚባል የአገሩ ገበሬ ቤት ነው። በራሱ በቅሎ አስቀምጦ ከዚያ እልቂት ቦታም ይዞኝ የሄደው እሱ ነው።

በአያና ዋቅጅራ ቤት እንክብካቤ እየተደረገልኝ ራሴን እስካውቅ ድረስ አንድ ሣምንት ቆየሁ።

በሁለተኛው ሣምንት መጀመሪያ ላይ በጠዋት አያና ዋቅጅራ በቅሎውን ጭኖ—

«ኢንባቆም፣ ተነስ ጉዞ እንጀምራለን» አለኝ። ከቤቱ እንደወጣሁ ሌላ ሁለት ሰዎችን አየሁ። የሰፈሩ መንደሩ ነዋሪዎችና ጐረቤቶች ናቸው። አንደኛው ተክላይ አብርሃ ከትግራይ የመጣ ነው። ሁለተኛው ደሌቦ ሆጤ የሚባል ከከምባታ የመጣ ሰፋሪ ነው።

«ኢንባቆም» አለ አያና ዋቅጅራ በዝግታና ሌሎቹ ሁለቱ ጠጋ እንዲሉን በእጁ እያመለከተ።

«ተክላይና ደሌቦ ከእኔ ጋር ሆነን ከዘመድ እንድትቀላቀል፣ ከሀዘንህም እንድትፅናና ወደ አገርህ ልንወስድህ ነው የጫነውና እንሂድ» አለኝ።

ሦስቱንም በየተራ ቀና ብዬ አየኋቸው። ሁሉም በሀሳቡ በመስማማት አንገታቸውን ነቀነቁ። ለእኔ ደህንነት አስበው ሊያደርጉ የተነሱት አደጋ ላይ ሊጥላቸው የሚችል መሆኑ ቢገባኝም አልተከራከርኩም። ሀሳባቸውን ተቀብዬ መንገድ ጀመርን።

እንዲህም ሆኖ ጠዋት ገና ወፍ ጭው ጭው ሲል ከአሶሳ ተነስተን የእግር ጉዞአችንን ቀጠልንና ከአንድ ሳምንት በኋላ በጐጃም በኩል አድርገን መርሀቤቴ ደረስን።

መርሀቤቴ ካደረሱኝ በኋላ በሰፈራው ምክንያት የተዋወቅኋቸው ወዳጆቼ የወለጋው ተወላጅ አያና ዋቅጅራ፣

የትግራዩ ተወላጅ ተክላይ አብርሃና የከምባታው የተወላጅ ደሌቦ ሆጤሶ ሳይውሉ ሳያድሩ የመልስ ጉዞአቸውን ቀጠሉ። ስላደረጉልኝ ሁሉ አመስግኛቸው ስንለያይም አያና እንዲህ አለ።

"ወንድሜ እንባቆም ሆይ አሶሳ የተፈፀመውን ምንጊዜም ስታስታውሰው ለትውልድም ስትናገረው እንደምትኖር አውቃለሁ። እኛም እንዲሁ የምናስታውሰውና የምንናገረው የሀዘን ገድል ነው። ነገር ግን አሶሳ የተፈፀመውን ባሰብክ ቁጥር እኛ ወንድሞችህንም አስበን። ስለእኛም ለልጆችህና ለትውልድ ንገር። የሰይጣን ልጆች በአብሪት በአገራችንና በእኛም ስም ከሰሩት ኃጢአት እጃችን የጠራ እንደሆነ ታውቃለህ። የተቃጠልን፣ የሞትን ሁላችን ነን። ይህን ለትውልድ ንገረው።" አለና በወንድማዊነት አቀፈኝ።

ለዚህ ወዳጄ የምሰጠው መልስ አልነበረም። የአባቶቻችንን የምሥጋናና የምርቃት ሥርዓት በማስታወስም ወደ መሬት ጐንበስ ብዬ የአገሬን አፈር በሁለት እጄ ዘገንሁ። ወደ ሦስቱም በየተራ ቀረብኩናም በአገሬ የጥንት ሰዎች ደንብ እመርቃችሁ ዘንድ ፍቀዱልኝ።

እሽታቸውንም ባገኘሁ ጊዜም የያዝኩትን አፈር በላያቸው በየተራ እየበተንሁ «ይህን የመራ አፈር የረገጠ፣ በዚህ የኖረ፣ ከዚህ በሚወጣው የተመገበ፣ ከዚህ ለሚወጣውም እንክብካቤ ያደረገ፣ በአፈሩ የተጠመቀ የዘላለም የመራ ወዳጅ፣ ወንድምና አገር ነው። ትውልድም በኩራት እያመሰገነ ያስበዋል።» ካልኳቸውና ከተሳሳምን በኋላ ተለያየን።

በማለት መራ—ጌታ እንባቆም በእጁ ይዞት የነበረውን አፈር በተን አድርጐ ታሪኩን አቆመ። በድጋሚም በመካከላችን ሙሉ ፀጥታ ሆነ። ረዘም ላለ ጊዜ በእንዲህ ሁኔታ ከቆየን በኋላም ምንም ሳንነጋገር ሁላታችንም ብድግ ብለን በአንድነት ጥምቀተ—ባህሩ ወዳለበት ቦታ ጉዞ ጀመርን። በመንገድ ላይ ከሁለታችን የወጣ አንድም እንኳ ቃል አልነበረም።

* * *

የመራምባ ሚካኤል የከተራ እለት ከቤተክርስቲያኑ ወጥቶ እስከ እለተ ክብሩ፣ እስከ ቃና–ዘገሊላ ድረስ፣ ለሁለት ቀናት ጥምቀተ ባህር ያድራል።

በእነዚህ ቀናት የመንደሩ ሰው በሞላ፤ ልጁም አዋቂውም ታቦቱን አጅቦ ከዚያው ከጥምቀተ ባህሩ ማደሩ ልምድና ባህል ነው። የታመመ ሰው፣ ነፍሰ ጡር፣ ወይም አመጣት ካልሆኑ በቀር ታቦት ከደጅ አድሮ ወደ ቤት አይመለሱም።

በዚህም መሠረት፣ የከተራ እለት ሚካኤልን ወደ ጊዜያዊ ማደሪያው አስገብተን የካህናቱ ሀሌታ፣ የሰውም ቀረርቶና ጭፈራ ካበቃ በኋላ እንባቆምና ዞማለም ወደ እኔ መጥተው አንተና ወላሴ እቤት ሂዱችሁ እደሩና ጠዋት ኑ አሉኝ።

የወላሴ ጤንነትና ቁመና ውጭ ለማደር አይፈቀድለትም። አንድ እግር፣ አንድ እጅ፣ አንድ አይን የሌለው ሰው እንደልቡ ተመቻችቶ የጥር ብርድንም ተከላክሎ ከደጅ ማደር አይሆንለትም። የወላሴ ወደቤት መመለስም አግባብ ያለው ነበር።

ብቻውን እንዳይሆን እኔ እንዳስተዳድረው መደረጉም አግባብ ይመስላል። ሆኖም ግን ሁለታችን ወደቤት እንድንመለስ የሆነው ለወላሴ ብቻ ታስቦ ሳይሆን ለእኔም ታስቦ እንደሆነ አልጠፋኝም። የከተማ ሰው ስለሆንኩ ውጭ ማደሩ አይመቸውም ብለው በማሰብ ያደረጉት ነበር። የከተማ ሰው በመሆኔም በእነሱ ዓይን የአገሬ ሰው ሊያደርገው የሚችለውን ማድረግ የሚሳነኝ ነኝ። ከወላሴ በተለየ መልኩ እኔም ስንኩል ነኝ። የአባትና እናቴ ባህልና ልምድ ከላዩ ተሰንክሏል።

ለማንኛውም በእንባቆምና በዞማለም ሀሳብ ተስማማንና ከወላሴ ጋር ወደ ቤት ተመለስን።

ማታ መደብ ላይ ተቀምጠን ለጥምቀት የተጠመቀ

የማሽላ ጠላችንን እየጠጣን ብዙ ከተጨዋወትን በኋላ፣

«መራ–ሽመል፣ ለመሆኑ ከእንግዴህ ኑሮህ የሚቆጣጠው እንዴት ነው?» አልኩት።

«ስለምን መራ–ሽመል ትለኛለህ። እንደ እኔ ያለ አካለ ጉደሎ ሰው፤ አንድ እጅ፣ አንድ እግር፣ እንድ አይን የሌለው ሰው መራ–ሽመል ይባል ዘንድ አይገባም» አለ ቆጣ ብሎ።

«እኔም ሆንኩ አገሬው መራ–ሽመል ያልንህ ከጉድለትህ በፊት ነው። መራ–ሽመል የሚባል ሰውም እንደሚቆስልና እንደሚሞት የታወቀ ነው። ለዚህ እንዳንተ ዝግጁ ያልሆነ ሰው መራ–ሽመል አይባልም። ስለዚህ በአካለ–ሙሉነትም ሆነ በአካለ ጉደሎነት ለእኛ መራ–ሽመል ነህ» አልኩት።

«ተወኝ እባክህ፣ ወንድሜ መራ–ሃይማኖት እንዲያው ወላሴ ብለህ ጥራኝ» አለ።

«አንተ መራ–ሽመል ካልሆንክ እኔ መራ–ሃይማኖት የመባሉ ክብሩስ፣ ማዕረጉስ፣ ምግባሩስ ከወዴት አለኝ? አታየኝም በዚህ በከበረ ቀን እንኳ እንደ መራ–ሃይማኖቶች ቆሜ የመራውያንን ታሪክ፣ ልምድና ባህል ለትውልድ መስበክ ሲገባኝ ከዚህ ቁጭ ብያለሁ።»

«እሱማ የጥንቱ ነበር» አለኝ። እኔን ለማፅናናት እየሞከረ።

«እኔም የምልህ እንዲያው ነው። መራ–ሽመል እንድልህ ካልፈለግህ በደንቡ የመንግስት ማዕረግህ ሻምበል ወላሴ ብዬ ልጥራህ» አልኩት።

«ቢሉስ ይልቅ መራ–ሽመል በለኝ» አለና የሸክና ጠላውን ተጎነጨ።

«መራ–ሽመል፣ ቅድም እንዳልኩህ ታዲያ የወደፊቱ ክራሞትህ እንዴት ነው የሚሆነው» አልኩት።

«ወንድሜ፣ ባልንጀሬ፣ ራሴን አላጠፋም። በእርግጥ ይህን ለማድረግ ብዙ ሳላስብ አልቀረሁም። ግን አሁን ይህ አይከጅለኝም። ባለፉት ወራት በዚሁ በአባቴ አገር ከልጅነት ባልንጀሮቼ ከአንተ፣ ከእንባቆምና ከዞማለም ጋር ያሳለፍኩት ጊዜ ሀዘንና ምሬቴን ባያስረሳኝም መለስተኛ ደስታ ሰጥቶኛል።

ይህን ደስታ በፈቃዴ አሳጠፋውም» ሲል፣

«ሀዘንና ምሬትህን ለወደፊቱ ኑሮ መልካምነት ስትል መተው፣ መርሳት አለብህ» አልኩት።

መልስ ሳይሰጠኝ ለትንሽ ጊዜ ዝም ካለ በኋላ ወደ ኋላ መደቡን ደገፍ ብሎ «ስማኝ ወንድሜ ላጫውትህ» አለና የሀዘንና የምሬቱን መንስዔ ማስታወስ ጀመረ።

«አንድ እግሬን፣ አንድ እጄን፣ አንድ ዓይኔን ለነፃነቷ፣ ለአንድነቷና ለክብሯ መባዕ አድርጌ በጀግንነት መሰዊያ ላይ ያቀረብኩላት አገሬ ኢትዮጵያ የሰጠችኝ ቦታ በአይንህ ያየኸው ነው። የላቤ፣ የደሜ፣ የአካሌ ዋጋ ከእራፊ ጨርቅና ከቆረቆንዳ ያነሰ ሆኖ ከሰው መተላለፊያ አውራ ጐዳና ላይ ወድቄ ነው ያገኘኸኝ። እንደ አተላ ተደፍቼ፣ እንደ ቆሻሻ ተገፍቼ፣ ህዝብ ተጠይፎኝ እያለፈ፣ መንግሥት በነጋ በጠባ እርኩስነቴን እየመሰከረ። አዎ! እንዲህ ሆኜ ነው ያገኘኸኝ።

ብካይ ሰቆቃ፣ መካድና የመልካም ምግባር ዋጋ በደል መሆኑ በዘር የሚተላለፍ ከሆነ የአባቴን አግኝቻለሁ። ምናልባት የአባትህን ሳይሆን የራስህን የሥራ ዋጋ አገኘህ የሚለኝም ካለ፣ በፀጋ ፅዋዬን እቀበላለሁ።

ታስታውሳለህ፣ አባቴ ለነፃነት፣ ለአገርና ለሰንደቅ ዓላማ ሲል አምስት ዓመት ሙሉ በቆላ በደጋ ላብና ደሙን እያፈሰሰ እንዳልተዋጋ፤ የጠላት ጦር የማይበሳው የአገር ጋሻ መከታ አርጎ ራሱን እንዳልሰጠ፤ ነፃነትና መንግሥት ሲመለሱ በሦስት ክንድ ገመድ ነው ከዚህ በላይ ከላይ ከኮረብታው ላይ ያንጠለጠሉት። ጣሊያን ያቃተውን የእኛው የኢትዮጵያ አጤ ፈፀሙት። የእኔ ብቻ ሳይሆን የአንተ፣ የእንባቆምና የዞማለም አባትም ያ ነበር አገራቸው የከፈለቻቸው ዋጋ። በባንዳ እጅ መሰቀል!!

ከልጅነት ጀምሮ ህሊናየን ሲያውከውና ህይወቴን ሙሉም ሲያሳድደኝ የኖረው ያ ሁኔታ ነበር። የአባቴን ኑሮ እንደገና ለመኖር፣ ለአገሩ የከፈለውን መስዋዕትነትም ደግሜ ለመክፈል፣ እሱ የተነሳውን ክብር አግኝቼ በሞቴም እንኳ ቢሆን ስሙን በይፋ ከጀግኖች አምባ ለማስጠራት ነበር ምኞቴ። ብቀላ ነበር የገፋፋኝ።

ለዚህ ነበር አስራ ሁለተኛ ክፍል እንደጨረስን አንተ፣ እንባቆምና ዞማለም ወደ ዩኒቨርስቲ ስትሄዱ እኔ ወታደር ለመሆን ሐረር ጦር አካዳሚ የገባሁት። ፍላጐቴ፣ ስሜቴ፣ አገሬን በወታደርነት ማገልገል ነበር። ጦር ሜዳ መዋል፣ ለአገር አንድነትና ነፃነት፣ ለሰንደቅ ዓላማ ክብር መዋጋት መታገል፤ ከጀግኖች መካከል መቆም፣ ይህን ነበር የተመኘሁት። እናንተም እንደቆየው የአገራችን ልምድ «መራ-ሽመል» ያላችሁኝ ለዚሁ ነበር። ያወጣችሁልኝን ስም ስለወደድኩትም እንደስሙ ለመኖር ነበር ጥረቴ።

ከሐረር ጦር አካዳሚ ሌሎቹ ጓዶቼ በምክትል መቶ አለቅነት ተመርቀው ሲወጡ እኔ በሙሉ መቶ አለቅነት ነው ተመርቄ የወጣሁት። ለዚህም ያበቃኝ በስልጠና ላይ በነበርኩበት ጊዜ የሶማሌ ጦር ኦጋዴን ጠረፍ አካባቢ ድንበር እየተሻገረ ያስቸግር ነበርና ድንበራችንን ዳግም እንዳይደፈር ትምህርት እንድንሰጠው በምሥጢር ተወሰነ። ለዚህም ግዳጅ አራት ሰዎች ተመረጥንና ለሁለት ወራት ከሰለጠንን በኋላ ዘላን መስለን ግመል እየሳብን ወደ ሶማሌ ግዛት እንድናልፍ ሆነ። አላማው ድንበር እያለፈ የሚያስቸግረውን የሶማሌ ጦር በቀጥታ ለመግጠም ሳይሆን ከኋላ ደጀን የሆነውን የጠላት ጦር ካምፕ ለመምታት ነበር። ተልዕኳችን ተሳክቶም ያን የሶማሌ ካምፕ በፈንጅ አመድ ካደረግን በኋላ ያለ ምንም ችግር ወደ ጦር ሰፈራችን ተመልሰናል። መቶ አለቅነት ያሰጠኝም ይኼ ነበር። የጠላት ህይወት ለመጀመሪያ ጊዜ በእጄ ያለፈው፣ የሰው ደም የሸተተኝ ያኔ ነበር። ከዚያን ወዲህ ብዙ ጠላት በእጄ ወድቋል። አጋጥሞኝ በምህረት ወይም በምርኮ ያለፍኩት የአገሬ የኢትዮጵያ ጠላት የለም።

ከጦር አካዳሚው ተመርቀን በወጣንበት ዓመት የኢትዮጵያ አብዮት ጀመረ። እኔም እንደአብዛኛው ወጣት መኰንን የአብዮቱ ግንባር ቀደም ደጋፊና አራማጅም ነበርኩ። አብዮቱን በሚመለከት ለእኔ አማራጭ የሌላቸውና በሙሉ እምነት የቆምኩባቸው መሠረታዊ ግቦች ነበሩ። ከመነሻው ጀምሮ እስከመጨረሻው በዚህ ላይ ያለኝ እምነት

አልተለወጠም። እነዚህንም ከዳር ለማድረስ ባደረግሁት ሁሉ ደስታ እንጂ ፀፀትና ቅሬታ የለኝም። ፀፀቴ በወታደርነቴ ብቻ ሳይሆን በኢትዮጵያዊነቴም በመሸነፌ ነው።

ዛዲያ ምንድናቸው ግቦቼ ትለኝ ይሆናል።

የመጀመሪያው፤ ከውስጥ የነበረውን የህዝብና የአገር ጠላት በማያዳግም ሁኔታ መደምሰስ ነበር። ይህም ጠላት በዚያን ጊዜ የነበረው የአጤው፣ የመሳፍንቱ፣ የመኳንንቱና የባላባቱ ሥርዓት ነው። ይህ ሥርዓት ከሥሩ ካልታጨደ ለእናት አገሩ የሞተው፣ እየሞተ ያለውና የሚሞተው ህዝብ መብትና ነፃነት ያገኛል የሚል እምነት አልነበረኝም። እንዴት ሆኖ?

መንግሥቱ ንዋይ የጀመረውን ሥራ ከፍጻሜ የማድረስ ግዴታ እንዳለብኝ ነው ያየሁት። የገፋፋኝ አብዮታዊ ስሜት፣ ወይም በጊዜው የነበረው የአይዲኦሎጂ እምነት ሳይሆን ምናልባት በቀል ሊሆን ይችላል። የመደብ ትግል ሳይሆን የብቀላ ትግል ሊሆን ይችላል። ልዩነት የለውም። የሁሉም ውጤት አንድ ነው።

የታሪክ አጋጣሚ አርበኛው አባቴን ያለ ፍርድ የሰቀለውን ሥርዓት ከምፈርድበት ጊዜ ላይ ስለጣለኝም በፈራጁ ላይ የሚፈረድበት ጊዜ ነበር።

ስለሆነም፣ በአብዮቱ መጀመሪያ አመታት የቀድሞውን ሥርዓት ተቀዳሚ አገልጋዮች ከአጤው ጀምሮ እስከአነስተኛው ባላምባራስ ድረስ በቁጥጥር ሥር ማድረግ ነበር ግዳጃችን። እንደከብት እየነዳን ነው አስረን ያጉርናቸው። አብዛኛው የዘመናት በደሉን እየረሳ ሳይቃወም ነው ወደ እስር የመጣው። በዳይ ቢረሳ ተበዳይ እንደማይረሳ ያጤነ ብዙም የለ። አንዳንድ የመኳንንት ሚስቶች ሀብታችንን አትንኩ እንጂ እንካችሁ ባሎቻችንን ለጊዜው በጥበቃ ስር አውሏቸው እያሉ እያመጡ አስረከቡን። ባልም ሀብትም አይተርፍም።

አንዳንድ ተጠራጥረው በየገጠሩ የሸፈቱም ነበሩ። እነዚህ የነበረውን ሁኔታ ተጠራጥረው ተታኩሰው እንደ ወንድ ለመሞት የሸፈቱትን በእውነቱ አደንቃለሁ። ከቅጣት ግን አልዳኑም።

ደጃዝማች ፀሐዬ እንቆሥላሴና ወንድሞቻቸው፣ ደጃዝማች ሸዋረገድ በሺና ወንድሞቻቸው ወደ መርሀቤቴ ሄደው ሸፈቱ በተባለ ጊዜ የተሰማኝን ደስታ ይህ ነው ልልህ አልችልም። አባቴ ለአገር ነፃነት በመቆምና ፍትህ በመሻት በሸፈተበት የዠማ በረሃ ዘምቼ ለአብዮቱ ሳይሆን እኔና እነሱ ለምናውቀው ያልተከፈለ እዳ ስል ያለ ምህረት ደመሰስኳቸው።

ወደላይ ወደ መንዝ ተሻግሬም የሸፈቱትን የራስ ብሩ ልጆች አንድ ባንድ ቀጣኋቸው። ያመለጠኝ የለም። የፍርድ ጊዜ ነበርና ፈረድኩባቸው። ከጣሊያን ወዲህ ለአርባ ዓመታት ያህል ሰብአዊ ክብሩ፣ መብቱና ነፃነቱ ተገፎ ጠኔ ሲተነፍስ ወደኖረ ህዝብ አገር «አገራችን» ብለው መሸፈታቸው የዋህነት ነበር።

ከዘመቻ ወደ አዲስ አበባ ስመለስ መንግሥቱ ነዋይ የጀመረውን ሥራ ፈፅመን፣ መንግሥትም በራስ እምሩ መሪነት አቁመን ወደ ጦር ሠፈራችን ለመመለስ የተማማልነው ተከዶ፤ ደርግ የሚባል የወታደር መንግሥት ተቋቁሞ መኮንኖች የስልጣን ሽኩቻ ሲያደርጉ አገኘሁ።

በዚሁ ሽኩቻ የተነሳ እኔም ከሐረር ምሩቃን ጓዶቼ ጋር ተይገፎ ለጥቂት ቀናት ታስሬያለሁ። በሁዋላ ግን የጣልነውን መንግሥት በሚመለከት አቋሜ ግልፅ በመሆኑና የሥልጣን ፍላጐት የሌለኝ ወታደር መሆኔ ሲታወቅ ተፈታሁ።

እንደተፈታሁም የታሰሩትን መሳፍንትና መኳንንት በሚመለከት መንግሥቱ ንዋይ የጀመረውን ሥራ ፈፀምነው። በእኔ አመለካከት ያን ጊዜ ለመጨረሻ ጊዜ የበደል ሁሉ መንስዔ የነበረው ሸክም ከኢትዮጵያና ከኢትዮጵያውያን ትከሻ ወረደ።

ቅር የምሰኝበት፣ የማዝንበት፣ የምፀፀትበት አንዳችም ነገር የለ። ያለአግባብ በእጄ የፈሰሰ ደም ካለ የአባቴ አፅም ይፍረድብኝ፣ መንፈሱ ከተሰቀለበት ወርዶ ይሞግተኝ።

ይህ እንግዲህ እኔ አብዮቱን በሚመለከት የነበረኝ የመጀመሪያው ግብ ነው።

ሁለተኛው ግብ፤ የኢትዮጵያ ዳር ድንበር ማስከበር፣ ለነፃነቷ መቆምና አንድነቷን መጠበቅ ነበር።

ለዚህም፣ የደርግ መንግሥት ሥልጣን ከያዘ ጀምሮ ከጠረፍና ከጦርነት የተለየሁበት ጊዜ የለም።

መጀመሪያ የገጠመን የሶማሌ ጦርነት ነበር። የሶማሌ መንግሥት የኢትዮጵያን በውስጥ በኩል በአብዮት መታወክ አጋጣሚ አድርጐ ወጋን። መውጋት ብቻ ሳይሆን ይገባኛል የሚለውን የኦጋዴንን ግዛት አልፎ እስከ ድሬዳዋ ድረስ በመምጣት አገራችንን ወረረ። እግረ-መንገዱንም በቂ ትጥቅና ዝግጅት ሳያደርግ የነበረውን የኢትዮጵያ የጠረፍ ወታደር ያለ ምህረት ፈጀው። የሶማሌ ጦር ከጠረፍ እስከ ድሬዳዋ ሲመጣ በምርኮ የያዘው አንድም ወታደር የለ። ሁሉንም ፈጅቶታል።

ይህ ለአገራችን ታላቅ ውርደት ነበር። ለጊዜው የመሣርያና የሰው ኃይል ችግር ስለነበረን ብዙዎቻችን ውርደታችንን ታቅፈን ቁጣ ከመተንፈስ በቀር ማድረግ የምንችለው አልነበረም።

የነበረውን የሰው ኃይል ችግር ለመቀነስ የክተት አዋጅ ታወጀና የኢትዮጵያ ህዝብ ገበሬውም፣ ሠራተኛውም፣ ወጣቱም፣ ሽማግሌውም በአንድነት ለአገሩ ሊዋጋ ተነሳ። በእውነቱ እጅግ የሚያኮራ የህዝብ ምላሽ ነበር። አብዛኛው «አገሬ» እያለ በስሜት የተነሳ ስለነበር ብዙም ወታደራዊ ስልጠና ሳይሰጠውና በቂ ትጥቅ ሳይኖረው ወደ ጦር ግንባር ዘመተ። የገዛ ጐራዴያቸውን፣ ጩቤያቸውን፣ ጦራቸውን እንኳ ሳይቀር ይዘው የመጡ ነበሩ።

ከዘመተው ውስጥ አብዛኛውን የኦጋዴን በረሃ በልቶት ቀረ። ወደ ሃምሳ ሺህ የሚሆን ወዶ ዘማች ነው የሶማልያን ወራሪ ጦር ከአገር ለማስወጣት የተሰዋው። ከመደበኛው ጦርም ውስጥ ብዙ አልቋል። አሟሟቱ የሚዘገንነውና የሚያሳዝነው ግን የወዶ ዘማቹ ነው። እንደወጣ ቀረ። እኔም አይኔን ያጣሁት ያኔ ነው።

ከሶማሌው ጦርነት በኋላ ወታደሩም ሆነ ወዶ ዘማቹ እረፍትና ምሥጋና ሳያገኝ ወደ ሰሜን የጦር ግንባር እንዲዘምት ሆነ። ወንበዴዎች ኤርትራን ለመገንጠል ከምንጊዜውም በበለጠ ተደራጅተው መጥተው ነበር።

እንዲያውም እኔ ጦር እየመራሁ ከኦጋዴን ኤርትራ ስደርስ ያልተያዘው አሥመራ ከተማና ሌሎች ጥቂት የወታደር ምሽጐች ነበሩ። ወንበዴውን ወግቶ ለማስለቀቅና የአገር አንድነትን ለማስከበር የፈሰሰው ደም፣ የተከሰከሰው አጥንትና የባከነው የሰው ህይወት ይህ ነው ተብሎ በቀላል የሚገመት አይደለም። በሁለቱም ወገን ብዙ እልቅት ተካሂዷል።

የኤርትራውን ጦርነት በመቶ ሺህ የሚቆጠር ሠራዊት፣ አብዛኛው ከወዶ ዘማቹ ተሰውቶ በድል አበቃነው። ድሉ ግን ጊዜያዊ ነበር። የኤርትራው ጦርነት እንደ ሶማሌው ጦርነት ዘላቂ ወታደራዊ መፍትሔ የሚገኝለት አልነበረም።

ለምን ትለኝ ይሆናል።

አየህ! ሶማሌ ሄደን የተዋጋነው የውጭ ጠላት ነበር። አገራችንን ገምሶ ሊወስድ የመጣ የውጭ ጠላት ነው። የኤርትራው የውጭ ጠላት አይደለም። ጠላታችን የሆነው የእኛው ህዝብ፣ ወገናችን ነው። የምንወጋው ጠላት እንደእኛው ለእናት አገሩ ለኢትዮጵያ አያት ቅድመ አያቱ ብዙ መስዋዕትነት የከፈሉለት ነው። እንደእኛው ኢትዮጵያዊ ነው።

የኤርትራ ጦርነት የወንድማማቾች ጦርነት ነበር። በዚህም በብዙ ሺህ የሚቆጠር ሠራዊት ከሁለቱም ወገን በውጭ ጠላት ጦር ሳይሆን በገዛ ወንድሙ ይደመሰሳል።

እጅግ የከፋና የመረረ ጦርነት ነበር። የድሃው ልጅ አለቀ።

ወንድሜ! ጦርነትን ባሰብኩ ቁጥር እጅግ የሚያሳዝነኝ በጦር ሜዳ ለአገሩ የሞተው የደሃው ልጅ ብቻ መሆኑ ነው። በጦር የተሰዋው የገበሬው፣ የከተማው ድሃ ልጅ ብቻ ነው። የድሃ ደም ፈሰሰ በከንቱ!

ለአገሩ በጦር ሜዳ የዋለውን አገር፣ ህዝብና መንግሥት ውለታውን መመለስ ቀርቶ አሟሟትህን ያሳምርልህ እንኳ አላለውም። ድሃው ዜጋ እንደውሻ ልጅ የትም ወደቀ።

አሥራ አራት ዓመት ሙሉ ያለ እረፍት ጦር ሜዳ ከቆየሁ በኋላ በመጨረሻው ከረን ላይ ተጐድቼ ወደ ከተማ ለህክምና መጣሁ። ህክምናው ብዙም አልነበር። ቁስሌን አሻሽገው፣ የተመታ እጄንም እንዲህ እንደምታየው ክንዴ

ላይ ጉምደው «ጀግኖች አምባ» ጣሉኝ።

«ጀግኖች አምባ» በጦር ሜዳ አካለ ጉደሎ ለሆንና ደጋፊ ዘመድ ለሌለን መንግሥት እንደመጠሪያ አድርጐ የሰራልን ነበር። በዚያ ግቢ ሁለት እግሩ ተቆርጦ መቆም፣ መራመድ የማይችል፣ እጁም እግሩም ተቆርጦ ልዩ ፍጡር የሚመስል፤ አይን የሌለው፤ ፊቱ የሰው መልክ የማይመስል፤ እንዲያው የተለያየ አካሉ በአሰቃቂ ሁኔታ ተለይቶት ለታሪክ ህያው የሆነ የአገር ወታደር ነበር።

ለአገሩ ሲል ከፍተኛውን መስዋዕት ለመክፈል የፈቀደ ሰው ነው። ግን ሞት እንኳ አልለመነው ብሎት ይንገላታል፣ ይሰቃያል።

ታዲያ ይኸውልህ ወንድሜ፣ «ጀግኖች አምባ» በገባሁ በሁለተኛው ዓመት ላይ እስካሁን ሁላችንም የአምባው ኑዋሪዎች ያየነው መከራ አልበቃ ኖሮ ሌላ የመከራ መጋረጃ ተከፈተ።

በጠላትነት ለብዙ ዓመታት ሲወጉንና ስንወጋቸው የነበሩት ኃይሎች የደርግን መንግሥት አሸንፈው አዲስ አበባ መጡና የራሳቸውን መንግሥት መሰረቱ። አዲስ መንግሥት ሲቆም የአሮጌው መንግሥት መዋቅር በጠላትነት አውግዞ መበተን የተለመደ በመሆኑም ብተናው፣ ቅጣቱና እስሩ በሰፊው ተጀመረ።

ለኢትዮጵያ ነፃነትና አንድነት ተብሎ ከየቤቱ፣ ከየመንደሩ፣ ከእርሻው በግድ እየተያዘ የዘመተው የኢትዮጵያ ወታደር በሙሉ በአዲሱ መንግሥት «የአገርና የህዝብ ጠላት» ተብሎ በመም ስለተፈረደበት ያለ ጡረታ መብት፣ ያለ ምስጋና፣ ያለ ክብር ውርደትና ስድብ ተከናንቦ ተበተነ። ከጦርነት ከሞት የተረፈው የድሃ ልጅ ወታደር ሁሉ አገሬ ብሎ የተዋጋላት አገር ጣለችውና በየመንገዱ ወድቆ ቀረ። ለማኝ ሆነ።

በያው ሰሞን እኛንም የአዲሱ መንግሥት ባለሥልጣኖች መጡና «ከጀግኖች አምባ» ውጡ አሉን። እኛ ለእነሱ «ጀግና» አልነበርንም። መንደሩም «የጀግና አምባ» አልነበረም። ለአገር የተሰዋን ሳይሆን አገር የበደልን ተደርጐ

ታዩና የት እንደምንገባ እንኳ ሀሳብ ሳይሰጥ እንደቆሻሻ አውጥተው ጣሉን።

ያ ሁሉ የአምባው አካለ ስንኩል ከመንደር ላይ ተጥሎ መሄጃውን ሳያውቅ ከፊሉ ሲንፏቀቅ፣ ከፊሉ በደረቱ ሲሳብ፣ ከፊሉም መንፏቀቅና መሳቡ ተስኖት እንደ ገንዳ መንገድ ላይ ሲንከባለል ማየት እጅግ የሚዘገንን ነበር።

ያ ሁላ ለአገሩ አካሉን ቆርጦ የሰጠ ጀግና ችግሩ ቢብስበት «ጳባካችሁ ስለወንድ ልጅ አምላክ በአንዳንድ ጥይት ጨርሱን» እያለ አምርሮ ተማፀነ። ጀግናው አለቀሰ። ኤሎሄ አለ። ታዲያ ማን ሰሚ አለና። አገር አልሰማም አለች። ደነቆረች።

እኔም ለሦስት ቀናት ያህል ቀን ፀሐዩን፣ ሌሊት ብርዱን ችዬ ከቆየሁ በኋላ አንድ ወደ አዲስ አበባ የሚመጣ ባለመኪና ዳቦ ሊያከፋፍለን ሲያቆም «ጳባክህ ወገን ከዚህ አንስተህ አዲስ አበባ ጣለኝ» ብዬ ተማፀንኩት። ሰውየው መቸም በእርግጥ ወገን ነበር። እኔን ብቻ ሳይሆን ሌሎች ከእኔ ጋር የነበሩ ሁለት አካለ ስንኩል ወታደሮችንም ይዞን መጣና እዚያው አገኘሁሽ ቦታ አዲስ አበባ ጣለን። ከዚያን ጀምሮ አንተ እስካገኘኸኝ ድረስም የአርበኞች ህንፃን ተገን አርጌ ሞቴን ስጠብቅ ነበር።

አየህ ወንድሜ፣

ዛሬ እጅግ አድርጌ የማዝነውና የምፀፀተው በወታደርነት ባደረግሁት ጉዳይ ወይንም በላዬ ላይ በደረሰው አይደለም። ይህንን እችለዋለሁ። ሊያፅናናኝ የሚችልም ብዙ ነገር አለ። በወታደርነቴ ያደረግሁት ለአገሬና አገሬ ኢትዮጵያን ስል ነው። በዚህ ከተሳሳትኩ አገሬ ልትቀጣኝም ይቅር ልትለኝም ትችላለች። በእኔ ላይ የደረሰውም በሌላው የደረሰ ስለሆነ ህዘኔ የግል ሳይሆን የጋራ፣ የአገር ነው።

የማዝነውና የምፀፀተው፣ የቀረኝን ህይወትም በሰላም እንዳልኖር ህሊናዬ ላይ ተጋርጦ የሚወጋኝ ማድረግ ስችል ሳላደርግ የቀረሁትና ችሎታ ሳይኖረኝ ቀርቶ ሳላደርግ የቀረሁት ነው። በዚህ አገርም ሆነ ትውልድ ሊያፍርብኝና ሊጠይቀኝ ይችላል።

እንደምታውቀው ይዘን የተነሳነው መልካም ዓላማ ሁሉ በውስብስብ ሂደት መንገድና ግቡን ለውጦ ዛሬ ካለንበት መቋጠሪያ የሌለው አዘቅት ውስጥ ጥሎናል። በአብዮት ስም ብዙ ግፍ ተሰርቷል። ብዙ እልቂት ደርሷል። ኢትዮጵያም ክፉኛ ቆስላለች። ለዚህ ሁሉ ተጠያቂው በሥልጣን ላይ የነበሩት የደርግ አባላት ናቸው ብሎ መደምደሙ በቂ አይደለም መጥፎ አድራጐታቸውን ልንገታ፣ ከሥልጣንም ልናስወግዳቸው የምንችልበት ሁኔታ አልጠፋም ነበር። ግን በፍርሐትም ይሁን የከንቱ ተስፋ እሥረኛ በመሆን በዝምታ አለፍናቸው። የዚህ ዝምታ ውጤትም የቀይ ሽብር እልቂት፣ የህዝብ ቁቆናና ፍጅት፣ የኤርትራ መገንጠልና የመንግሥት በጠላት መያዝ ነው። ሌላም ብዙ አለ።

ለውጡ በተጀመረ ማግስት ወይንም ከዚያን ወዲህ የውድቀታችን መንስዔ በሆነው መንግሥት ላይ የቅጣት እርምጃ ብንወስድ ኖሮ ይህ ሁሉ አይደርስም ነበር። አገርና ህዝብም በተለየ ሁኔታ ላይ ይገኙ ነበር። ስለሌላው መናገር አልችልም። እኔ ራሴ ግን በግሌ መንግሥቱንም ሆነ ሌሎቹን መደምሰስ የምችልበት ብዙ አጋጣሚ ነበር። ዛሬ ወደኋላ ሳስበው አንድ ዜጋ ለአገሩ ሊያደርገው ይችለው የነበረው ታላቁ መስዋዕትነትና የጀግንነት ስራም ይህ ነበር። ግን አላደረግሁትም። በዚህ እፀፀታለሁ።

«ትሰማኛለህ መራ—ሃይማኖት» አለ በድንገት

«እሰማለሁ እንጂ፣ ልቦናየም ይከተልሃል» አልኩት

«በል እንግዲህ ለዛሬው ይብቃ እሳቱም ነዶ እያለቀ ነውና ጋደም እንበል» አለና ወዳጄ መራ—ሽመል ወላሌ፣ ወይንም ሻምበል ወላሌ ከተቀመጠበት መደብ ላይ ጋደም አለ።

እኔም በእጄ የያዝኩትን የሽክና ጠላ ተጐንጨሁና እንደሱው ሌሊቱን በእንቅልፍ ልጋተር ጋደም አልኩ።

* * *

ጥር 12 ቀን የቃና ዘገሊላ እለት ከወላሌ ጋር ጠዋት ከቤት ተነስተን ወደ ጥምቀተ—ባህሩ አመራን። ከዚያ እንደደረስንም ታቦቱን አጅቦ ያደረው ሰው ሁሉ የታቦቱን ከዳስ መውጣት በጭፈራ፣ በሆታ፣ በፉከራ፣ በቀረርቶ ሲጠባበቅ አገኘነው።

የመንደሩ እረኞች በተለያዩ ቀለማት አሽብርቀው የሰሯቸውን ቁሮዎች እያሽከረከሩ ታቦቱ ያለበትን ዳስ ይዞራሉ። ለሚቀጥለው ዓመት ባለቁሮ የሚሆኑት ዛሬ ታናናሾቻቸው የሆኑት ልጆች ስለሚሆኑ! ቁሮአቸውን ወስደው ቤተ—ክርስቲያን ሲሰቅሉ የእነሱም የእረኝነት ዘመን ያከትማል። የቁሮ ሥራና የእረኝነት ጊዜ ለሌላ ትውልድ ይተላለፋል።

ረፋዳው ላይ ሲሆን የሚካኤል ታቦት ከዳሱ ወጣና በካህናቱና በመዘምራኑ ሀሌታና ሽብሸባ፣ በወንድና በሴቱ ሆታና እልልታ እየደመቀ ወደ ቤተክርስቲያን መጓዝ ጀመረ። ቤተ—ክርስቲያኑን ሦስት ጊዜ ከዞረ በኋላም በመቅደስ ካለ መንበሩ ላይ ገብቶ ያርፍና ለአንድ ዓመት ያህል ካለበት ሳይንቀሳቀስ የምዕመናኑን ፀሎት፣ ልመና፣ ምሥጋናና ተማፅኖ እየሰማ፣ እየዳኘ፣ እየባረከና እየቀጣ ይቀመጣል፡፡ የመራምባው ሚካኤል እንዲህ ነው።

የሚካኤል አጃቢ ወደየቤቱና ወደየድግሱ ለመሄድ ሲበታተን ዞማለምን በአይኔ ማፋለግ ጀመርኩ። ሰሞኑን በሙሉ እሷን ለብቻዋ ለማነጋገር ሳላስብ አልቀረሁም። ሆኖም ግን እሷን ማነጋገሩ እንደእንባቆምና እንደወላሌ ቀላል ሆኖ ስላላገኘሁት ዛሬ ነገ ስል ቆይቻለሁ።

ዞማለምን ማነጋገሩ የከበደኝ ሴት በመሆኗ አይደለም። በመሠረቱ የእሷ ሴት መሆን አራታችን በነበረንና ባለን ግኑኝነት ላይ አንዳችም ተፅዕኖ አሳድሮ አያውቅ።

ክነበረችበት የጉድጓድ እስር—ቤት እስፈትተን

ካመጣናት ጀምሮ ግን እኔም ሆንኩ እንባቆምና ወላሌ ቀና ብሎ ዓይኗን ማየት፣ ለብቻዋም ማነጋገሩ እየከበደን መጥቷል።

ለዚህም ምክንያቱ እንደ እህት፣ እንደ እናት፣ እንደራሳችንም አርገን በምናያት ዞማለም ላይ የደረሰውን ችግር ሁላችንም ስለምናውቅና እንዳችንም ብንሆን ልናድናት ባለመቻላችን ፀፀት ስለተላበሰን ነው። እንደ ወንድም፣ እንደአባት፣ እንደጓደኛ ከጐኗ ልንቆም ባለመቻላችን ሀፍረት ይሰማናል። የደረሰባት ስቃይ ሰውነታችን በቁጣ ያቃጥለዋል። ከዚህ አንፃር አቅም የለሌን፣ ደካማ ሆነን መገኘታችን ደግሞ የበለጠ በራሳችን ላይ ያስቆጣናል።

እጅና እግሩ የፊጥኝ ታስሮ፣ አፉ ተለጉሞ የገዛ እናቱ ወይንም እህቱ ከፊቱ በግፍ ስትሰቃይ የሚያይ ሰው በቁጣ ከመቃጠል በቀር ምን ማድረግ ይችላል? አንተ አንባቢውስ በእኛ ቦታ ብትሆን ምን ማድረግ ትችላለህ?

በዚህም የተነሳ ዞማለምን በግል ሳላነጋግራት ቆይቻለሁ። ዛሬ ግን ወደመጣሁበት አገር መመለሻዬ ጊዜ ስለደረሰ፣ ምናልባትም ዳግም በህይወት ልንገናኝ ስለማንችል እንደምንም ብዬ ማነጋገር ነበረብኝ። የማነጋግራትንም እያሰብኩ በአይኔ ስፈልግ በርቀት ከሁለት የመራምባ ሴቶች ጋር ቆማ አየኋት።

የለበሰችው ግማሽ ጥለት ቀሚስ ነው። በፋብሪካ ሳይሆን በአገሩ በመራምባ መንደር ሴቶች ጥጥ ተቦጭቆ፣ ተባዝቶ፣ ተፈትሎና ተዳውሮ በሸማኔ በዚያው በመንደሩ የተሰራ። ከኋላ በኩል ብቻ ያለው ጥለት አረንጓዴ ነው። በዚሁ መልክ የተሰራ መቀነትም በቀጭን ወገቧ ላይ ሸብ አርጋለች። ግራና ቀኝ ሳይጣፉ ትከሻዋ ላይ አንገት—ልብስ ጣል ተደርጓል።

ከፊት ለፊት የማየው ቁመናዋ፣ ሰውነቷና አለባበሷ ከጥቂት ወራት በፊት ከጉድጓድ እስር ቤት ያወጣነው በድን አካል መሆኑን ለማመን ያዳግታል። ስናመጣት በህይወት ትቆያለች ብሎ ተስፋ የነበረው ብዙም ሰው አልነበር። ሆኖም፣ ዞማለም ከቀን ወደ ቀን ሰውነቷ እያገገመና እየተጠናከረ

መጥቶ ሙሉ ጤና ሰው ለመሆን በቅታለች። የአእምሮዋን ሁኔታ ለማወቅ አስቸጋሪ ነው። መንፈሷ ስለማገገሙም መናገር አይቻል። በውጭ አካሏ ግን ጤና መሆን ብቻ ሳይሆን ድሮ እንደማውቃት ያማረች፣ የተዋበችና ሞገስ የተላበሰች ሆናለች።

ዞማለም ከሁለቱ ሴቶች ጋር ጀምራ የነበረውን ጨዋታ ጨርሰው ሲለያዩ ወደ እኔ እንድትመጣ በእጄ አመለከትኳና መጣች።

ኩራት በተመላበት የእመቤት አረማመድ በሰው መካከል አሳብራ ወደእኔ ስትመጣም በአንክሮ ተመለከትኳት። አይኖቼ የሚያዩት ደግሞ ወደ አእምሮዬ ጓዳ ገብቶ የቆየ ትዝታ መቀስቀሱ አልቀረም።

አንባቢ፣ ትዝታው ምናልባት አንተ ነው ብለህ የምትገምተው አይደለም። ዞማለምን ሳይና ሳስብ የሚታየኝ ሴትነቷ ሳይሆን እሷ ለእኔ በአእምሮዬ ምሳሌ የምታደርገው ነው። ይህ ደግሞ የእኔ ብቻ ሳይሆን፣ ብታውቃት የአንተ የአንባቢውም የህሊናህና የማንነትህ መሰረት ነው።

ከዚህ የወንድ ሥጋዊ ዓይን በሚያየው አይቶ ዞማለምን ለመግለጥ መሞከር እሷነቷን፣ ክብሯንና እሷ ምሳሌ የምታደርገውን ሁሉ ዝቅ ማድረግ ይሆናል። ይህንንም ስል የዞማለም ውበትና ቁመና ለውደሳ ያንሳል ማለቴ አይደለም።

እመነኝ አንባቢ፣ ስለዞማለም ቁንጅና መናገር ካስፈለገ ብዙ ቅኔ መቀኘት፣ ብዙ ግጥም መግጠም፣ ስንኝ ደርድሮ መዝፈን፣ ሰምና ወርቅ ማዥጐድጐድ ይቻላል። ሰላም ለፀጉርኪ ብሎ ጀምሮ ሰላም ለእግርኪ እስኪባል ድረስ የዞማለም ውበትና ቁንጅና በከንፈር ላይ እንደአገሬ እንደዠማ ወንዝ የሚፈስ ነው። ዞማለምን እንድታያት የምሻው ከዚህ አንፃር አይደለም።

እንድታያት የምሻው ምሳሌ ከምትሆነው ከኢትዮጵያ አንፃር ነው። የኢትዮጵያ ምሳሌ ስልህም አፈወርቅ ተክሌ ቀይ የወርቅ ካባ አልብሶ፣ በአልቦ አስጊጦ፣ በእጇ አደይ አበባ አስይዞ የሳላትን ኢትዮጵያ ማለቴ አይደለም። ይህችኛዋ ኢትዮጵያ በግድግዳህ ላይ ተሰቅላ የልብ ኩራት የምትሰጥህ ምስል ናት።

ዞማለም ምስል ሳትሆን ህያው ናት። በህያውነቷና በዚህም በደረሰባት ሁሉ ነው የኢትዮጵያ ተምሳሊት ሆና የምትታየኝ። ከታች ከእሷ አንደበት የሚነገረውን ስትሰማም እኔ የነገርኩህ የማጋነን አለመሆኑን ትገነዘባለህ።

ዞማለም አጠገቤ ደርሳ ሰላምታ ከተለዋወጥን በኋላ ላነጋግራት የምፈልግ መሆኑን ገልጬላት ከትላንት ወዲያ ከወላሌ ጋር ወደነበርንበት ኮረብታ ወጣን። ኮረብታው አባቶቻችን የተሰቀሉበት ብቻ ሳይሆን የልጅነት ጊዜያችንንም በእረኝነት ያሳለፍንበት በመሆኑ ለሁለታችንም ብዙ ትዝታ አለው።

ኮረብታው ላይ ወጥተን ከተቀመጥን በኋላ ከአንዳችንም ቃል ሳይወጣ ብዙ ጊዜ በፀጥታ ተቀመጥን። ሁለታችንም ማለት የምንፈልገው ብዙ ነገር እንዳለ እናውቃለን። መጀመሩ ግን ቀላል አልነበረም። ከየትስ ይጀምራል።

በመጨረሻው ፀጥታውን የሰበረችው ዞማለም ነበረች።

«መራ–ሃይማኖት» አለች።

«መራ–ሀኪም» ብየ መለስኩ። አሁንም ትንሽ ዝም ካለች በኋላ

"ለምን እንደታሰርኩ ያ ሁሉ ስቃይስ ለምን እንደደረሰብኝ ማወቅ የምትፈልግ ይመስለኛል» አለች።

«መጠየቁ አስፈርቶኝ ነው እንጂ ማወቅስ እፈልጋለሁ። ሆኖም ሀዘን የምቀሰቅስብሽ ከሆነ አትንገሪኝ» አልኩ።

«እርግጥ ነው፣ በእኔ ላይ የደረሰው ብቻ ሳይሆን በአይኖቼ ያየሁትና በጆሮቼ የሰማሁት እንደሬት የሚመር፣ የሚዘገንንና ለሰሚ አጥንት የሚያብረከርክ ነው። ሆኖም ግን መነገር አለበት። አንተ መራ–ሃይማኖት ነህ። የመራ–ሃይማኖት ተግባርም በመራ ልጆች ላይ የደረሰውን ዘግቦ መያዝና ለትውልድ ጆሮ ማድረስ ነው። ስማ፣ አጉናፍር ብቻ አይደለህም። መራ–ሃይማኖትም ነህና ላጫውትህ» አለችና በርቀት ከብዙ ዓመታት በፊት አባቷና አባቴ የተሰቀሉበትን ቦታ እያየች ዝም አለች። እኔም በትዕግስት ጠበቅኳት።

«በደርግ ዘመን የድሃው ልጅ ከእናቱ ጉያ ተነጥቆ እየተወሰደ በጥይት ስለመደብደቡ፣ የሙት እናቶችም የልጆቻቸውን ሬሳ እንዲገዙ ስለመገደዳቸው፣ በጦርነትና በጠኔ ስለደረሰው ታላቅ እልቂት ሁሉ በከፊል ያየኸው፣ በከፊል የሰማኸው፣ እኔም በየጊዜው ባለህበት አገር ሁሉ እየፃፍኩ ያሳወቅሁህ ስለሆነ አሁን ደግሜ አላነሳውም።።።።

ልነግርህ የምወደው ደርግ በወደቀ ማግስት ስለተፈጠረ ሌላ እልቂት ነው። ይህንንም የምነግርህ ምናልባት በነበርክበት አገር ሳለህ ሰምተኸው ከሆነ የተሳሳተ ግንዛቤ እንዳይኖርህ ነው።

አየህ ወንድሜ አጉናፍር፣ መራ–ሃይማኖት!

የደርግ መንግሥት ወድቆ አዲስ መንግሥት ሲቋቋም እኔ አሩሲ ክፍለ አገር አርባ ጉጉ ከሚባል ቦታ ነበርኩ። ከዚያ ሦስት ዓመት ተቀምጫለሁ። ሦስቱን ዓመት ያሳለፍኩትም የኖርዌይ መንግሥት የህክምና ጣቢያ ከነሙሉ እቃው አቋቁሞ ሥራውን እንድመራና መሠረታዊ ጤንነትን ለህብረተሰቡ እንዳዳርስ ጠይቆኝ ስለነበር በዚሁ ላይ ስታከት ነው።

እንደምታውቀው የእኔ ሙያ ጤና ጥበቃ፣ ህክምና ነው። በዚህም ያልዞርኩበት የኢትዮጵያ ግዛት የለም። በጠረፍ፣ በከተማ፣ በቆላ በደጋ እየተዘዋወርኩ የድሆች ድሃ ሊባሉ የሚችሉ የአገራችን የኢትዮጵያን ዜጐች በሙያዬ ከመርዳት ወደ ኋላ ያልኩበት ጊዜ የለም።

ለሥራዬ ፖለቲካ፣ ባህል፣ ቋንቋ፣ ጐሣ እንቅፋት የሆነበት ጊዜ የለም። የእኔ ጦርነት ከበሽታ ጋር ነበር። ጠላቴም ይኸው ነበር። ደርግ በኢህአፓ ምክንያት አራት ዓመት አስሮ ከገረፈኝ ወዲህ ፖለቲካውን ብቻ ሳይሆን ከተማውንም ሁሉ ትቼ ኑሮዬናን ሥራዬ በገጠር ነበር።

ታዲያ አርባ ጉጉ ሦስት ዓመት ስቀመጥ የጤና ጣቢያው ለአገሬው ህዝብ የሰጠው የጤና አገልግሎት በእኔ ሳይሆን በህዝቡ በራሱ ሊነገር የሚችል ነው። ህዝቡ እጅግ በጣም ታታሪ፣ ሰው አክባሪና እንግዳ ተቀባይ ነው። እንደአገሬው ተወላጅ እንጅ እንደባዕድ ወይም እንግዳ

የታየሁበት ጊዜ የለም። ሥራዬን ያየ፣ ስለ ሥራዬ የሰማና ሥራዬ ከሚሰጠው የጤና አልግሎት የተጠቀመ ሁሉ በታላቅ አክብሮት እንደእናት፣ እንደ እህት፣ እንደልጅ ተንከባክቦ ነበር የያዘኝ።

ያ ሁሉ ግን ደርግ ወድቆ አዲስ መንግሥት ሲቋቋም ተቀየረና ገነት ይመስል የነበረው የአርባ–ጉጉ ህይወትና ኑሮ ገሀነም ሆነ። የገሀነሙ አለቆችም ካሁን ቀደም ባላየነው ሁኔታ የእልቂት ሰይፋቸውን መዘው፣ ጦራቸውን ሰብቀው፣ ጠመንጃቸውን አዘቅዝቀው በላያችን መጡ።

እኔ በነበርኩበት በአርባ–ጉጉ አውራጃ፣ በ አቦምሳ ከተማና በአካባቢው የተፈፀመውም እነሆ።

አዲስ መንግሥት አዲስ አበባ ከተቋቋመ በኋላ እንደ አርባ–ጉጉ ያሉ የደቡብ አካባቢዎችን ለማስተዳደር ስልጣን የተሰጠው የኦሀዴድ ለሚባል ድርጅት ነው። ኦሀዴድ የኦረሞ ህዝብ ዲሞክራሲያዊ ድርጅት ማለት ሲሆን ያቋቋመውና ስልጣኑን የሰጠው አዲሱ መንግስት ነው። በዚህ ድርጅት የአርባ–ጉጉ ተወካይና ኃላፊም አቶ ዲማ ጉርሜሳ የሚባሉ ሰው ናቸው።

አቶ ዲማ ጉርሜሳ አርባ-ጉጉ የኦሀዴድን ሠራዊት ይዘው ከመጡ በኋላ የመጀመሪያ ስራ አድርገው የወሰዱት የአውራጃውን ህዝብ በጐሳ ለይቶ መመዝገብ ነበር:: ይህ አዲስ ሁኔታ ቢሆንም ነገሩን ስላላወቅነው ዝም ብለን ጠበቅን:: የጐሳ ምዝገባው ካለቀ በኋላ «አማሮች» ተብለው የተሰየሙት የአርባ -ጉጉ ነዋሪዎች ከሌሎቹ እየተለዩ በየወረዳው ለብቻቸው እንዲሰፍሩ ተደረገ::

እኔ የነበርኩበት አቦምሳ በተባለው ከተማ ነበር። እኔም ያን ጊዜ በህይወቴ ለመጀመሪያ ጊዜ «አማራ» ነሽ ተባልኩና እንደዚሁ እንደእኔ ከተሰየሙ ሰዎች ጋር በአንድ መንደር እንድሆን ተገደድኩ።

በመሰረቱ፣ አቶ ዲማ ጉርሜሣ «አማራ» ብለው ከመሰየማቸው በፊት ራሴን እንደአማራ ያየሁበት ጊዜም የለም። ማየት ቀርቶ ታስቦኝም አያውቅ። ከልጅነት ጀምሮ መላ ህይወቴን ያሳለፍኩት ጥሩ ዜጋ፣ ጥሩ ኢትዮጵያዊ ለመሆን

በመጣር ነው። በጐሳ ደረጃ ራሴን ማየቱ የሚቻለኝ አይደለም። እንደምን ሆኖ ይታሰባል? ከአባት ከእናቴ የወረስኩት ኢትዮጵያዊነትን እንጂ አማራነትን አይመስለኝም።

ምናልባት ከኢትዮጵያዊነት ባነሰ ደረጃ ራሴን ገልጬ ቢሆን በመሬነት ነው። አዎ መርሀቤቴ ነኝ። መርሀቤቴ ደግሞ ሲቸር በቆለኛነት፣ ሲከፋ በሽፍታነት ይታወቃል እንጂ «አማራ» ተብሎ ሲጠራ በከፉም ሆነ በደግ ሰምቼ አላውቅ። እሰማ የነበረው ሰው «አገርህ ከምና ነው?» ተብሎ ሲጠየቅ ከመርሀቤቴ፣ ከመንዝ፣ ከጐንደር፣ ከወሎ፣ ከጐጃም፣ ከምንጃር፣ እንዲህና እንዲህ ሲል ነው። የዚህ አካባቢ ተወላጅ ሁሉ በአጥንቱ ተቆጥሮ «አማራ» ተብሎ ለብቻው ሲገለል ሳይ የመጀመሪያ ጊዜየ ነበር። ለእኔ ያልታየኝ፣ ለእነ ዲማ ጉርሜሳ የታያቸው ምን እንደሆነ አልገባኝም።

ምናልባት ቋንቋ ይሆናል። አማርኛ መናገራችን ከሌላው ለይቶን ከሆነ አማርኛ ብሔራዊ ቋንቋ በመሆኑ የጋራ መግባቢያ ነው። ለዚያውም ቢሆን እኔን ብትወስድ ከአማርኛ ሌላ ኦሮምኛ፣ ጉራጊኛ፣ ትግርኛ፣ አጣርቼ እናገራለሁ። ቋንቋ መለያ ነው ብዬ አልገምትም። እንዲያውስ አብረውኝ «አማራ» ተብለው ከተገለሉት መካከል ከአያት ከቅድም–አያት ጀምሮ አርባ ጉጉ ተወልደው የኖሩ፣ ያለዚህም ሌላ አገርና ህዝብ የማያውቁ ነበሩ። ሁሉም በነዲማ ጉርሜሳ አጥንታቸው እየተቆጠረ «አማራ» ናችሁ ተባሉና አንድነት ተገለልን።

ይህ ከሆነ በኋላ፣ አቶ ዲማ የአካባቢውን «አማራ» ያልተባሉ ሰዎች ሰብስበው «እነዚህ ለብቻ የለየናቸው አማሮች ጠላት ስለሆኑ በጠላትነታቸው የሞት ቅጣት ይገባቸዋል ብላችሁ ፈርሙ» ብለው ትዕዛዝ ይሰጣሉ።

ከተሰበሰበው ሰው መካከል አዛውንት በየተራ እየተነሱ «እነዚህ አማራ ብላችሁ የለያችኋቸው ሰዎች ለእኛ ጠላቶቻችን አይደሉም። እኛ አማራ የሚባል ጠላት የለንም። በሌለን ጠላት ላይ ደግሞ የሞት ፍርድ ፈርደን ለልጅና ለልጅ ልጆቻችን የደም ኃላፊነት አናወርስም። ይልቁንም እነዚህ እናንተ ጠላት ብላችሁ የምትኮንኗቸውን እኛ የምናውቃቸው በሀዘን፣ በደስታችን ያልተለዩን ወንድሞቻችን፣ እህቶቻችን፣

ጋብቻዎቻችንና ጉረቤቶቻችን እንደሆኑ ነው» ብለው ይመልሳሉ። ሌላው የተሰበሰበው ሰው ሁሉ በዚሁ ይስማማና ለመሄድ ሲነሳ አቶ ዲማ ጉርሜሳ ምንሽሩን አቀባብሉ በመነሳት «እነዚህ አሁን የተናገሩት ሰዎች የነፍጠኛ ረዳት ስለሆኑ ይታሰሩ» ብሎ ለተከታዮቹ ትዕዛዝ ይሰጣል።

ተከታዮቹም የአለቃቸውን ትዕዛዝ ተቀብለው ስምንት አዛውንት ያለ አንዳች አክብሮትና ርኅራሄ እያዳፉ አስረው ይወስዳሉ። ሌላው የተሰበሰበው ህዝብም «ሌላ የነፍጠኛ ረዳት ካለ አብረን እርምጃ እንወስድበታለን» የሚል ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶት ተበተነ።

ይህ በሆነ በሦስተኛው ቀን፣ እርብ እለት አቶ ዲማ ጉርሜሳ «አማራን መጨረስ ዛሬ ነው» ብለው ለእልቂት ሠራዊታቸው አዋጅ ነገሩ። የእልቂት ከበሮ ተመታ፣ እምቢልታም ተነፋ፣ የገሀነም በሮች ተከፍተውም በላያችን ላይ የሰቆቃ ዶፍ ያወርዱ ዘንድ ሰዓቱ ደረሰ።

በመጀመሪያ የነበርንበትን መንደር በርቀት በሚተኩስ ፈንጅ መቱት። ፈንጅው በተደጋጋሚ ሲፈነዳ መንደሩን እንዳለ በእሳት አጋየው። ታላቅ ኡኡታና ዋይታም እየተሰማ ሰው ከእሳቱ ለመዳን መሯሯጥ ጀመረ። መንደሩ ተከበ ስለነበር ግን ወዴትም መሮጥ አይቻልም ነበር። ከእሳት ነበልባል ከየቤቱ እየወጣ ያመለጠውን ወንዱንም ሴቱንም ልጁንም አዋቂውንም የአቶ ዲማ ጉርሜሳ ገዳይ ሠራዊት በጥይት ይቀልበው ጀመር።

እኔ በነበርኩበት ቤት በፍራቻ የሚሆነውን የምንጠባበቅ ሃያ ያህል ሰዎች ነበርን። በፈንጅው እሳት ቤቱ ሲቃጠል ጥቂቱ በዚያው አመድ ሆነው ቀሩ። ሌሎቻችን ወደ ውጭ ወጥተን ተራወጥን። ከእኔ ጋር አንድ እርጉዝ ሴትና ሁለት ህፃናት ልጆቿ ነበሩ። ውጭ እንደወጣን እርጉዟ ሴት በጥይት ተመትታ በልጆቿ ፊት ወደቀች። ሁለቱ ህፃናት እናታቸው በድን ላይ ሆነው ሲላቀሱ አየሁና ፈጥኜ ሄጄ እጅ-እጃቸውን እየያዝኩ ሰው ወደሚሮጥበት እየጐተትኳቸው ሮጥኩ።

እጅግ የሚያሳዝንና የሚያስፈራ ትዕይንት ነበር።

አንድ መቶ ያህል ሰው በመንደሩ በእሳት ተቃጥሎ አለቀ። ከእሳት ተርፎ በጥይት የተበላሸውም የዚያኑ ያህል ይሆናል።

ከእሳትና ከጥይት ያመለጠው ሰው እየሮጠ ሄዶ ቤተክርስቲያን ገባ። ከመጣው መዓት ሁሉ የእግዚያብሔር ቤት መጠለያ ይሆነኛል ብሎ ነው። እኔም እነዚያን ሁለት ህፃናት ይዤ የሄድኩት ወደዚያው ወደ ቤተ—ክርስቲያኑ ነበር። ሆኖም ግን አለማወቃችን እንጅ በዚያን ጊዜ የመጣብን የእልቂት ዶፍ ቤተ—እግዚያብሔር የሚፈራም ሆነ የሚያከብር አልነበረም። በአቶ ዲማ ጉርሜሳ የሚመራው የእልቂት ሠራዊት ሃይማኖት አልነበረውም። እንኳን ሰውን እግዜርን ራሱን አማራ ብሎ ከመግደል የሚመለስ አልነበረም። የጭካኔ ቀን!!

የመንደሩ ፍጅት ሲያበቃ የገዳዩ ሠራዊት እኛ ወደተሸሸግንበት ቤተ—ክርስቲያን ጥይቱን እየተኮሰ፣ እየፎከረ፣ እሳት እየተነፈሰ መጣ። ቤተ—ክርስቲያኑ በደረሰ ጊዜም ጥቂቱ ወደ ውስጥ ገቡና በመቅደሱ፣ በጣርያውና በግድግዳው ላይ ተኩስ ከፈቱ። ሰውንም እየረገጡ፣ እያዳፉ፣ እየጐተቱ ከቤተ—ክርስቲያን አስወጡና ውጭ እንደከብት መንጋ ከበቡት። የአባት፣ የእናት፣ የቅድመ አያቶቻችን አምልኮት ሲፈፀምበት የነበረውን፣ የእኛም የእምነታችን ሁሉ መሠረት የነበረውን ቤተ—ክርስቲያንም በፊታችን በእሳት አቃጠሉት። ቅዱሱ ታቦት፣ ፅላተ ሙሴ፣ የእመቤታችን የእግዚዕትነ ማርያም ፅላት በፊታችን በእሳት ተቃጠለ። ቅዱሳን መጻህፍት፣ አልባሳት ሁሉ አመድ ሆነ።

ቤተ—ክርስቲያኑ በመቃጠል ላይ እንዳለ ከመካከላችን የነበሩ ሦስት ቀሳውስትን እጅና እግራቸውን እያሰሩ ወስደው ከሚነደው እሳት ውስጥ ማገዷቸው። ቀሳውስቱ ከፅላቱ ጋር አብረው መንደዳቸውን የመረጡ ይመስላል ምንም አይነት የተቃውሞ ድምፅ አላሰሙም።

ያ ከሆነ በኋላ የተረፍነውን አንድ ሰላሳ የምንሆን ሰዎች ወስዳችሁ ገደል ስደዷቸው የሚል ትዕዛዝ ተሰጠና በአቅራቢያው ወደሚገኝ ገደል ይዘውን ለመሄድ እጅ-ለእጅ አሰሩን። መደብደብ በቻለ የሰውነት አካላችውና እጃቸውም በጨበጠው ሁሉ እየደበደቡም ወደ ገደሉ ይዘውን መሄድ

ጀመሩ። ሃሳባቸው ከነነፍሳችን ገደል ሊጥሉን እንደሆነ ምንም ጥርጥር አልነበር። እኛም እንደፋሲካ ጠቦት ወደ እርዳችን በዝምታ ከመነዳት በቀር ልናደርገው የምንችለው አልነበረም።

ወደ ገደሉ አፋፍ ስንቃረብ አንድ ያልታሰበ ነገር ተፈጠረ። ከኋላችን ብረት የታጠቁ ብዙ ሰዎች ወደ ሰማይ እየተኮሱ ሲገሰግሱ አየን። ከእኛ ይልቅ ይነዱን የነበሩት ሃያ የሚሆኑ የገዳይ ሠራዊት ሲደናገጡም አየን። ምክንያቱን አላወቅንም። ሰዎቹ ከእኛ ሲደርሱ ገዳዮቹንም ለግዳይ የምንነዳውንም መሣሪያቸውን እነጣጥረው ከበቡን። ጠመንጃ የያዘ ብቻ ሳይሆን ጐራዴ፣ ጦር፣ መጥረቢያ፣ ዱላ የያዘ ብዙ ሰው ነበር። ቆመን በማየት ላይ እንዳለንም እነዚህ በኋላ የመጡት ሰዎች በእኛና ለግዳይ በሚነዱን መካከል ገብተው ቆሙ። ይህን ጊዜም በፍርሀትና በድንጋጤ ደንዝዞ የነበረው ሰውነቴ መለስ አለና የሰዎቹን ማንነት መገንዘብ ቻልኩ።

ሰዎቹ ከተለያዩ የአርባ—ጉጉ መንደሮች የመጡ የኦረሞ ተወላጆች ናቸው። ሰሞኑን በእነሱ ስም ሲካሄድ በቆየው የአማራ ፍጅት እጅግ ተቆጥተው ፍጅቱን ለማቆም የመጡ ናቸው። ከእነዚህ ሰዎች መካከል አንድ በስራዬ አውቃቸው የነበሩ ዋቅወያ አባ መጋል የተባሉ አዛውንት ወደ ገዳይ አጃቢዎቻችን ራመድ አሉና

«ጐበዝ፣ የኦረሞ ህዝብ ድርጅት ነን፣ ወኪል ነን፣ ነፃ አውጪ ነን ብላችሁ ከአገራችን ከመምጣታችሁ በፊት እናንተ ማን እንደሆናችሁ አናውቅም። ደርግን አባረርን ብትሉ እሱማ ደግ ነገር አበጃችሁ ብለን ተቀበልናችሁ። የደርግን መውደቅ ደስታ ሳናበቃ እናንተ ደግሞ ከደርግ የባሰ አረመኔ ሥራ በመካከላችን አመጣችሁ። ለስንት ዘመን ከእኛ ጋር ህይወትና ኑሮውን፣ እድሉን፣ ሀዘንና ደስታውን አድርጐ የቆየውን ሰላማዊ ህዝብ በትውልድ አማራ በመሆኑ ብቻ ለይታችሁ ስትፈጁት ሰነበታችሁ። በእኛ በኦረሞም ስም በኦረሞ ትውልድ ያልታየ ጭካኔ ፈፀማችሁ። የሰራችሁት ስራ የአጋንንት ስራ በመሆኑ በእኔ አንደበት አይዘረዘርም። እንኳንስ ለሰው ጆሮ ለአጋንንቱም ጆሮ የሚዘገንን ነው።

የኦረሞ ታሪክ የሚነግረው የኦረሞን ህዝብ ሰላማዊነት

እንጅ እንደዚህ በእናንተ እንደታየው አረመኔነት አይደለም። እኛ በረጅም ታሪካችን ቆላ፣ ደጋ፣ ወንዝ፣ ባህር ሳይወስነን ከመላው የኢትዮጵያ ህዝብ ጋር በወንድምነት፣ በእህትነት አብረን በሰላም የኖርን ነን። ጠላታችን አማራ ወይም ሌላው ህዝብ አይደለም። ጠላታችን መንግስትና እንደዚህ እንደእናንተ ያለው ርጉም ትውልድ ነው። የዛር ልጆች!!

አሁንም እስካሁን በስማችን ለፈፀማችሁት በደል ትውልድ ይቅር ይበለን። ካሁን በኋላ ግን እነዚህንም ሆነ ሌሎች አማሮችን እንጐዳለን ብትሉ በቀል በእጃችን ነው። በደም የመጣውን በደም ለመመለስ ዝግጁ ስለሆን ሳንተላለቅ ወደመጣችሁበት ሂዱ» ብለው አብሯቸው ወደመጣው ሰው ዞወር አሉ። ሰዉም በእጁ የያዘውን መሳሪያ ቀና እያደረገ ከገዳዮቹ ጋር ለመፋለም ዝግጁ መሆኑን ያለ ጥርጥር አሳየ።

ይህን ጊዜ የፈጁንና ሊፈጁን የነበሩት የዲማ ጉርሜሳ ሠራዊት ወደኋላ ፈግፈግ አሉና መነጋገር ጀመሩ። የሚነጋገሩት አይሰማንም ሆኖም ግን በደረሰው የተደናገጡና የሚያደርጉትን ያጡ ይመስላል። ጥቂት ከተጨቃጨቁ በኋላ አንድ አለቃቸው የሚመስል መሣሪያውን እንደደገነ ወደ እኛ መጣና «ነፍጠኛና የነፍጠኛን ረዳት እናጠፋለን። የጐበናዎች ቀረራ እኛን አያስፈራንም። አሁን ግን በዚህ ርምጃ መውሰዱ አስፈላጊ ስላይደለ ውሰዱና አማሮቻችሁን ቀልቧቸው። ሲሰቡ እናርዳቸዋለን።» ብሎ ዛተና ለተከታዮቹ ምልክት ሰጥቶ ተለዩን። የዚያን ቀን እልቂታችንም በዚያ ቆመ።

በዚያን ሰሞን በአርባ—ጉጉ የአማራ ፍጅት ዘመቻ በሰፊው የተያዘበት ጊዜ ስለነበር እንተርፋን የሚል እምነት አልነበረንም። ያዳኑን ኦረሞ ወንድሞቻችንም ይህን ያውቁ ስለነበር ሦስት ቀን በየቤታቸው በትጋት ሲጠብቁን ከቆዩ በኋላ በአራተኛው ቀን በሌሊት ተነስተው ከአርባ—ጉጉ በእግር ይዘውን ወጡ። እስከ አዋሽ ዳር ድረስ ከሸኙን በኋላም በእንባ ተሰነባብተን ተለያየን።

ከዚያ ተነስቼ እኔም በሳምንቱ እዚሁ አባቴ አገር መርሀቤቴ መጣሁ። ሌላ የምሄድበት ቦታም ዘመድም

አልነበረኝም። ያን ሁሉ ፍጅት ካየሁ በኋላም በድሮ ኑሮዬ መቀጠል የሚቻለኝ አልነበረም። የፈለግሁት ሁሉን ትቼ እዚሁ እንዳገሬ ሴቶች እየኖርኩ የሰላም ሞቴን መጠበቅ ብቻ ነበር።

የሰላም ሞትን መመኘቴ የዋህነቴ ነበር። ሞት ምንጊዜውም በሰላም አይመጣም። ስቃይን አስቀድሞ ነው የሚያመጣ። እንዲህም በመሆኑ እዚህ በመጣሁ በሁለተኛው ወር ላይ ደግሞ የዚህ አካባቢ አዲስ ጌቶች ያለ ጥፋት ይዘው፣ ያለፍርድ አስረው ስቃይ ሲቀልቡኝ አገኘሁኝ።

እየሀ ወንድሜ፣

ይህን ሁሉ መንገሬ በላዬ ላይ ባለፈው እንድታዝንልኝ አይደለም። የፈለግሁት በአርባ–ጉጉ ለደረሰው እልቂት ተጠያቂዎቹ ኦሮሞች ሳይሆኑ በኦሮሞ ስም የሚነግዱ አንዳንድ ጨካኞች ብቻ መሆናቸውን እንድታውቅና ለሚጠይቅህ ሁሉ እንድትናገር ነው። ኦረመኔ ጉሳ፣ ብሔር፣ አገር፣ ሃይማኖት የለውም። ጊዜ ሲያመቸው እንደተባይ ይፈላል። ወዲያውም ይጠፋል። ዛሬ የሚታሰበኝና ለእነዚህ ለአገሬ ልጆችም የምነግራቸው እነ ዲማ ጉርሜሳ ስላደረሱት ጥፋት ሳይሆን እነ ዋቅወያ አባ–መጋል ስላሳዩን ወገንነት፣ ወንድምነትና ደግነት ነው።

አገራችን መርሀቤቴን ለብዙ ዓመታት በፍትህ፣ በደግነት፣ በስርዓት፣ በብልሃት የገዙትና አቻ የሌለው የህዝብ ፍቅርና ክብር ያላቸው ደጃች ገለታ ቀርቾ ናቸው የኦረሞን ህዝብ ማያ መነጥራችን። ይህን አትርሳ።»

ዞማለም ይህን ካለች በኋላ ፀጥ አለች። እኔም በትረካዋ መካከል ገብቼ መጠየቁም ሆነ ማቋረጡ አግባብ ስላልመሰለኝ ጆሮዬ የሰማው አእምሮየን እየገነተረው ዝም ብዬ ታሪኳን ለመስማት እጠብቃለሁ። ሆኖም ግን ልትነግረኝ የፈለገችውን ጨርሳ ኖሮ እመር ብላ ከተቀመጠችበት ተነሳችና ፈገግታ እያሳየች «ና በል እንሂድ የሚካኤል ድግስ ያመልጠናል» ብላ እጆችዋን ዘረጋችልኝ።

አነሳሷም ሆነ ፈገግታዋ ግራ ሳያገባኝ አልቀረም።

ሆኖም ዞማለም ሳውቃት እንዲያ ሀዘንን በፈገግታ መከታ የምታቦን ብልህ በመሆኗ አልተገረምኩም። ከተቀመጥኩበት ተነሳሁናም የዘረጋችልኝ እጇን ይዤ ቁልቁል ወደ መንደራችን ወረድን።

በማግስቱ፣ ጥር 13 ቀን ከወዳጆቼና ከመንደሬ ተለይቼ ወደማልመለስበት አገር እሄዳለሁ። ከያ በፊት ግን ጥር 12 ቀን ማታ ከመራምባ ሰዎች ቤት በአንደኛው ተገናኝተን የሚካልን ድግስ እንጋበዛለን። ያም የመጨረሻ ራታችን መሰነባበቻችን – ፀሎተ ሐሙሳችን ይሆናል።

* * *

ስንብትና ኑዛዜ

የጥር ሚካኤልን በታላቅ ድግስ ከሚያከብሩት የመራምባ ሰዎች መካከል አያ ክብረት ደመቀን የሚተካከል የለም። ይልቁንም የጥር ሚካኤል ከታቦት መታሰቢያነት በተጨማሪ የአያ ክብረት ደመቀ ግብር ዕለት እየተባለ መጠራት ከጀመረም ብዙ ጊዜ ሆኗል። የመራምባ ብቻ ሳይሆን ከወንጭት እስከ ዝማ ካሉት የመርሀቤቴ መንደሮች ሁሉ ብዛት ያለው ሰው የግብሩ ተካፋይ ለመሆን ይመጣል።

አያ ክብረት ደመቀ ሚካኤልን የሚዘክሩበት ምክንያት አላቸው። ስማቸው እንደሚያመለክተው፣ ከአብዛኛው የመርሀቤቴ ህዝብ በተቃራኒ ህይወትና ኑሮአቸው የከበረ፣ ያበበ፣ ያፈራና ያማረ ሆኖ አልፏል። በእርግጥ መከራ ሳይጉበኛቸው አልቀረም። ሆኖም ግን በሌላው ላይ ከወረደው የመከራና የስቃይ ዶፍ አንፃር በእሳቸው ላይ የደረሰው እንደ ተግሳፅና ማስጠንቀቂያ የሚታይ ነው።

እድሜያቸው ወደ ሰማንያ ይጠጋል፣ ወይም ያልፋል። የእኔ፣ የእንባቆም የወላሌና ዞማለም አባቶች የእድሜ እቻ ናቸው። ከእኛ አባቶች በተቃራኒ አያ ክብረት ከመንግሥት ጋር ከመፋጠጥ ይልቅ ርቀው መቀመጥን የሚመርጡ ብልህ ሰው በመሆናቸው በእድሜ ቆይተዋል። እድሜያቸውን በሙሉ ያሳለፉትም ራሳቸውንና ቤተሰቦቻቸውን ከመንግሥት እጅ በማግለልና በማራቅ ነው። በኢትዮጵያ ውስጥ ደግሞ መንግሥት ያልዳሰሰው፣ ያልነካውና ያላሻተተው ነገር መለምለሙና ፍሬ መስጠቱ አይቀርም። አያ ክብረት ልጅና ልጅ–ልጆቻቸውን በሰላም፣ በጤና አሳድገው ለወግ ለማዕረግ ያበቁት በእንዲህ ነው።

ለማንኛውም፣ ከሦስቱ ባልንጀሮቼ ጋር ራት ተጠርተን የሄድነው ወደዚሁ ወደ አያ ክብረት ቤት ነበር። እንደደረስንም ተጋባዡ ሁሉ ቦታውን ይዞ የማሽላ ጠላ በአቦሬ እየተቀዳ በዋርማና በሽክና ሲንቆረቆር አገኘን። ወደ ዳሱ እንደገባሁ

ለእኔ በተለይ ያስገረመኝ ትቸው ከሄድሁ ከብዙ ዓመታት በኋላ እንኳ የሁኔታዎች አለመለወጥና ወግና ሥርዓቱም ጥንት በነበረበት ቦታ በጊዜ ቆሞ ማግኘቴ ነበር። ለዚህም የድግሱን ሁኔታ ይመለከቷል።

የሰው መጋበዣ እንደጥንቱ ከእንጨትና ከቅጠል የተሰራ ዳስ ነው። የዳሱ ውስጥ ከዳር እስከዳር ሣርና ገለባ ተጉዝጉዟል። መቀመጫ ወንበር ስለሌለ ተጋባዡ የተቀመጠው መሬት ላይ ነው። ዳሱ ውስጥ ለየት ያለ መቀመጫ ቢኖር የጠፍር አልጋ ነው። ይህም ጋባዡ ከፍ ብለው የሚቀመጡበትና ድግሱ ሲያበቃ ነጠላቸውን ዘርግተው የተጋባዡን ምሥጋና የሚቀበሉበት ነው። የነጠላው አስፈላጊነት ከአመስጋኙ የሚወጡት ቃላት መሬት ጠብ እንዳይሉ ለማቀፍ ነው። አያ ክብረትም ለዚሁ ተዘጋጅተው በክብር ቦታቸው ላይ ተቀምጠዋል። ከእሳቸው ጉን በግራና በቀኝ አዛውንት፣ ባልቴቶችና ካህናት እንደየማዕረጋቸውና እድሜያቸው ከትልቅ እስከ ትንሽ በተዋረድ ተቀምጠዋል።

ተጋባዡ መጠጡን የሚጉነጨው ከየቤቱ ይዞት በመጣው ሽክናና ዋርማ ነው። ብርጭቆ የያዘ ሰው በአይኔ ብፈልግ አላየሁም። አንድ ሁለት ሰዎች ብቻ የአጤ ምኒልክ ኩባያ ተብሎ ይጠራ በነበረው ሲጉነጩ አይቻለሁ። ከአያት ከቅድም አያት የተወረሱና ብዙ ድግስ ያዩ ኩባያዎች መሆን አለባቸው።

ራት የቀረበውም በስፌድና በእግራም ገበታ ነበር:: ባለእግራሙ ገበታ የሚቀርበው በእድሜ ጠና ጠና ላሉት ነው:: የሌላው ገበታ ሰፌድ ነው:: ተጋባዡ በቡድን በቡድን ይቀመጥና ከገበታው ጋር አንዳንድ ድስት ወጥ ይቀርብለታል:: ሙዳ ሥጋም እንዲሁ በተዋረድ ይታደላል::

በዚህ ከመንበረ–መንግሥቱ 180 ኪሎ ሜትር ርቆ በሚገኝ አገር በበጉነት የተለወጠ አንዳችም ነገር የለም። እኔ ብቻ ሳልሆን ከእኔም በፊት የነበረው ትውልድ ትንሳኤ እርጉ ቢመጣ ይህን የጊዜን ሳይንቀሳቀስ መቆም እንደሚገነዘብ አያጠራጥርም። መንግሥቱ ከቀድሞው በበለጠና በፈጠነ ሁኔታ ህብረተሰቡ ውስጥ ዘልቆ መግባቱ ከተሜ

«መሻሻልና ሥልጣኔ» የሚለውን አላመጣም። ቢያመጣውም ምስና ዋጋው ከህብረተሰቡ አቅም በላይ እየሆነ አልተቀበለውም።

ለውጥ ቢኖር በጉጅነቱ በህብረተሰቡና በአገሩ ላይ የተከሰተው ነው። ይህም እኔ በልጅነቴ፣ ከእኔም በፊት የነበረው በዘመኑ ያውቀው የነበረው ገነት መሳይ ኑሮ ደረጃ በደረጃ ወደ ገሀነምነት ተለውጦ መገኘቱ ነው። ሰሞኑን በመራምባ አካባቢ ተዘዋውሬ ያየሁትም ይህንኑ ገጽታ የሚያንፀባርቅ ነው።

በጉጅነቱ የተለወጠው የህብረተሰቡ ኑሮና ህይወት ብቻ አይደለም። ተፈጥሮም ተለውጧል። ውብ የነበረው አገር ክፉኛ ተጉሳቁሎ ከውበቱ ነጥፏል። በልጅነቴ አውቀው የነበረው ማካው ደኑ ሁሉ እንዳለ ወድሟል። ከላዩ ደኑ ሲጠፋ ደግሞ መሬቱ አፈሩ በዝናብና በነፋስ እየተሸረሸረ የቀረው አለት–አፅሙ፣ ድንጋዩ ነው። ይህም አንገት ዞሮ ማየት በሚችልበት አቅጣጫ ሁሉ እንደተናካሸ አውሬ አግጦ ይታያል። በልጅነት ዘመኔ ከብትና ፍየሎቻችንን የምንጠብቅበት ለሙ መሬት፣ ጨፌው ዛሬ የለም። ለነገሩ እንጂ፣ ከብትም ሆነ እረኛ ብዙ አላየሁም። ከብቱን ድርቅና ችግር ፈፅሞታል። እረኛውንም የብሔራዊ ውትድርና እየወሰደ በየጦሩ ሜዳ ሰውቶታል። ከዚያ በተዓምር ድኖ የተመለሰው አካለ–ስንኩሉ በየቤቱ ምሬትና ፀፀቱን ያስታምማል። ለአገልግሎቱና ለመስዋዕትነቱ አንድ እግር ሽንብራ ነቅሎ ይህን ጠርጥር ያለው የለም።

በመራምባም ሆነ በጠቅላላው መርሀቤቴ በየሰው ገጽ ላይ ታላቅ ምሬት፣ ሀዘንና ተስፋ መቁረጥ ይታያል። ያልተበደለ፣ ያላዘነ፣ ያልተከፋ ሰው ያለ አይመስለኝም። ከፊሉ ቤተሰቡን ለተደጋጋሚ ጠኔ አስረክቧል። ከፊሉ በሰፈራ ስም ቤተሰቡ ተለይተውት የት እንዳሉ እንኳ አያውቅም። ከፊሉም ልጆቹ በጥይት ተበላሽተውበታል። ከዚህ የተረፈውን ደግሞ መንግሥት እለት በእለት በእብሪት ያጉሳቁለዋል።

የእኔ በዚያ ህብረተሰብ ውስጥ በዚያን ጊዜ መገኘት ለራሴ እጅግ አሳፋሪና የሚፀፅት ነበር። ተመልካች እንደምን *

እንዳየኝ አላውቅም። ምናልባት እኔን ማየቱ የብዙዎችን ሀዘን አባብሶት ይሆናል። ለምን ለእኔ የተለመነኝ አምላክ ለእነሱ አልተለመናቸውም? የእኔ ኢትዮጵያዊነትስ ከእነሱ በምን ተሽሎ ነው እነሱን የጉበኘ ሰቆቃ ሳይጉበኘኝ የቀረው?

አንባቢ፣

ይህ እኔን ብቻ ሳይሆን አንተ ምናልባት በውጭ አገር ነህ ብዬ የምገምተውንም ይመለከት ይሆናልና አድምጠኝና ለንስሐ ተዘጋጅ።

ማታ ግብዣው ላይ ተቀምጠን ከቀረበልን ገበታ በመመገብ ላይ ሳለን ዞማለም እስካሁን ድረስ እሷም ሆነች ሌሎቹ ባልንጀሮቼ እንባቆምና ወላሌ ባልጠየቁኝ እያልኩ ስፈራ የነበረውን ጉዳይ በድንገት አነሳች።

«አጉናፍር በቃሉ፣ መራ–ሃይማኖት– የእኛንስ ኑሮ አየኸው ሰማኸው። ለመሆኑ የአንተስ የፈረንጅ አገር ኑሮ እንዴት ነው? ኢትዮጵያነቲትንስ ከእኛ በተለየ እንደምን አገኘኸው?» አለች። ወዲያውም እንባቆምና ወላሌ በጥያቄው መስማማታቸውን አንገታቸውን ነቅንቀው በመግለጥ ከእኔ መልስ ለማግኘት ይመለከቱኝ ጀመር።

ከእነዚህ ከሦስቱ ባልንጀሮቼ ኢትዮጵያዊነት አንፃር የእኔ ኢትዮጵያዊነት ሊነገር የሚችል አይደለም። አሳፋሪ ነው። ይህንም ከተገነዘብኩ ቆይቷል። መላ ዘመኔን በከተማና በፈረንጅ አገር ሳባርረው የነበረው ኢትዮጵያዊነት፣ ባገኘሁትም ጊዜ እንደ ህፃን ልጅ ታቅፌ ሳሽሞነሙነው፣ ውዳሴ ከንቱ ሳውረድለት፣ እሽሩሩ ስለው የነበረው ኢትዮጵያዊነት ከንቱ፣ መና ነበር። ከዋናው ኢትዮጵያዊነት በመሸሽ ጥላውን ሳሳድድ ነው እድሜዬን በሙሉ ያባከንኩት። መርሀቤቴ ተመልሼ የሆነውን ሁሉ ካየሁ፣ በተለይም ሦስት ባልንጀሮቼን ካገኘሁ በኋላ ይህ ለእኔ ግልፅ ነበር። ግና ለእነሱ የማይታየውን የእኔን የውስጥ ኢትዮጵያዊነት ህመም ምን ብዬ ልንገራቸው? በምንስ ቋንቋ ባጫውታቸው ሊሰሙኝና ሊገነዘቡኝ ይችላሉ? እንደምንም ብዬ ኑዛዜዬን አሰማ፣ ህፍረትና ፀፀቴንም አደረድር ዘንድ ተነሳሁ። እንደበቴ ተከፍቶ ቃላቱም ከተጨነቀ ህሊናዬ እንደጦር እየተወረወሩ መውጣት

ጀመሩ።

«አጤውን የጣለው ለውጥ መጥቶ ስንለያይ እኔና ዞማለም እዚያው አዲስ አበባ ነበርን። ሁለታችንም የአንድ ድርጅት አባል ነበርን። ሆኖም ግን ድርጅቱ አባላቱን በየአካባቢው በምሥጢር የሚይዝ ስለነበር አንድ ላይ አልነበርንም። ዞማለም የድርጅቱ አባል የሆነችው አምናበት ለአገርና ለህዝብ ጠቃሚ የሆነ መሠረታዊ ለውጥ አመጣለሁ ብላ ነው። እኔ የእሷ አይነት እምነት ነበረኝ ለማለት አልችልም። ብቻ በጊዜው የተራማጅ ድርጅት አባል መሆን የተገባ ስለነበር አባል ሆንኩ። ጺሜንም እንኳ እንደተራማጅ ክርክም አድርጌ እንደነበር አስታውሳለሁ። ሌኒን ስታይል ይሉት ነበር።

እኔ በነበርኩበት ሠፈር በድርጅቱ ክበብ ውስጥ የነበርን አምስት አባላት ነበርን። አምስታችንም ድርጅታችን እንዳዘዘን ከቅስቀሳና ከወረቀት ብተና አንስቶ ድፍረትን እስከሚጠይቀው እንቅስቃሴ ድረስ ስንሳተፍ ከቆየን በኋላ የለውጡ ሁኔታ ከቃላት ጦርነት ወደ ጉልበት ትግል ተሸጋገረ። ድርጅታችን ደርግን በሚቻለው መንገድ ሁሉ ለመፈንገል ሲጥር፣ ደርግ በበኩሉ ድርጅታችንን የማያዳግም ምት መትቶ ፀጥ ለማድረግ ወሰነ። ገላጋዩ ኃይል ነበር።

ይህ ሲሆን፣ አንዳንዶች ነገሩ ወደ እልቂት የሚያመራ መሆኑን አስቀድመው በመገንዘብ ራሳቸውን የማውጫ መንገድ መፈለግ ጀመሩ። ከእነዚህ መካከል ጥቂቱ ገና ጦርነቱ ሳይጀመር በፍርሀት ተማርከው ደርጉን በባንዳነት ለማገልገል እጅ ይሰጣሉ። የቀሩት ከትግሉ ጐራ ወጥተው ወደ ስደት ይፈረጥጣሉ። አብዛኞዎቹ ግን በእምነታቸው ፀንተው ለኢትዮጵያ አብዮት እንሞታለን እንጂ በባንዳነት ወይም በፈሪነት ወዲትም ዞር አንልም ብለው በቁርጥ ተነሱ።

ኢትዮጵያዊነት የተፈተነበት ጊዜ ነበር።

የሽሽት መንገድ ከፈለጉትና ካገኙት መካከል አንዱ እኔ ነኝ። እልቂት በገሀድ በተጀመረበት የቀይ ሽብር ዋዜማ አብረውኝ ለነበሩት የድርጅት ጓዶቼ እንኳ ሳልነግር በፍርሀት ፈርጥጬ ከአገር ወጣሁ። የኢትዮጵያዊነትን ፈተና

ሳልሞክረው እንኳ የወደቅሁበት የመጀመሪያ ጊዜ ነበር።

እኔ ከአገር በወጣሁ በወሩ ወጣቶች እንበለ–ርኅራሔ እንደ አውሬ እየታደኑ መፈጀት ጀመሩ። የእልቂቱን ሰቆቃ መሪር ለማድረግ ተብሎም በግፍ የተገደሉ ወጣቶች አስከሬን ለወላጆቻቸው በብር ተሸጠ። እናቶች ልጆቻቸው ለተገደሉበት ጥይት ዋጋ እየከፈሉ አስከሬን ተቀበሉ። ሳያለቅሱም ቀበሯቸው። ከሞቱት መካከል በድርጅታችን ክበብ ከእኔ ጋር የነበሩት አራቱ ወጣቶችም ይገኙበታል።

አንዱን በተለይ አስታውሰዋለሁ። ምንጊዜም አልረሳውም። አወል ጀማል ይባላል። ከቡታጅራ፣ ከሰባት ቤት ጉራጌ የመጣ ነበር። ይኖር የነበረው አብሬ ከአጐቱ ጋር ነው። አጐቱ ሱቅ ነበራቸው። በዚህ ሱቃቸው ጓዳ እየተገኘሁም ከአወል ጀማል ጋር ብዙ ጊዜ ማት ቅሚያለሁ፣ ሻይ በስኒ ተካፍዬ ጠጥቻለሁ። እሳህን የሚፈሩ፣ የዕለት ኑሮአቸውን ታግለው ለማሸነፍ የሚጥሩ መልካም ቤተሰብ ነበሩ። የአወልም ምኞት በአጐቱ እርዳታ ራሱን አሻሽሎ ተከታይ ወንድም እህቶቹን ለመርዳት ነበር። ሰው ለመሆን በአገር ከአንገት ቀና ብሎ ለመራመድ።

ታዲያ በዚያው በቀውጢው ቀን ጠቋሚ ይመራበትና አወል ጀማልን ለመያዝ የታጠቁ ወታደሮች ወደ አጐቱ ሱቅ ይመጣሉ። ከጊዜው አንፃር አወል ወጥቶ እጁን ቢሰጥ እዚያው የአጐቱን ሱቅ አስደግፈው እንደሚረሽኑት አላጣውም። እጁን አልሰጥም ቢል ደግሞ ሱቁንም በሱቁ ውስጥ ያለውን ሁሉ እንደሚደመስሱና እንደሚፈጁ ያውቃል። አማራጭ ያልነበረው የሞት እንቆቅልሽ ነበር።

በዚህ ሁኔታ ላይ በነበረበት ጊዜ አማራጭ መስሎ የታየው በጓሮ በኩል ከሱቅ ወጥቶ እየተታኮሰ ወደ ወንዝ መውረድ ነበር። ወንዙ ግንፍሌ ነው፣ መታኮሻውም አንድ ስድስት ጥይት ጉራሽ ሽጉጥ ነበር። ያን ሽጉጥ እኔም አውቀዋለሁ። ደርግን ለመታገያ ድርጅት ያስታጠቀው ነበር። በአንድ ሽጉጥ ከባድ መሣሪያ የታጠቁ ወታደሮች ማሸነፍ እንደማይቻል የታወቀ ነው። አወልም ይህን ያጣው አይመስለኝም። ግን ኢትዮጵያዊ ወኔውን በኮስታራቱ አሳይቶ

ለመሞት የመረጠ ነበር። ከሱቁ ብዙም ሳይርቅ ነበር እንደቆሉ በጥይት ተቆልቶ ህይወቱ ያለፈው። ለእመነበት፣ ለአብዮቱ፣ ለኢትዮጵያ መሞት ለእሱ ታላቅ የክብር አክሊል ነበር።

አወል ጀማል ከእናንተ ከመራምባ ባልንጀሮቼ ከተለየሁ ወዲህ የተዋወቅሁትና የማከብረው ወዳጄ ነበር።

ቀይ–ሽብር ሆኖ የእድሜ አቻዎቼ ደም እንደወንዝ ሲፈስ፣ አፅማቸው እንደኮረብታ ሲከመር፣ የእናቶች ዋይታና ሮሮም በተዘጉ የሰማይ በሮች ላይ እያስተጋባ በደመና ተውጦ ሲቀር፤ እልቂት እንደነሐሴ ዶፍ ሜንቀት ነጐድጓዱን እያስተጋባ ሲወርድ — አዎ፣ ያን ጊዜ እኔ ያለ ሀሳብ በተድላ በሰው አገር ነበርኩ። የፈሪ ሰደተኛ! እንደጓደኞቼ ለአገሬ፣ ለህዝቤ፣ ለዓላማዬ ልቁምና ከወንዶች ልቆጠር የሚል የአባቶች ወኔ በውስጤ አልነበረም።»

በራሴ ላይ የተሰማኝን ሀፍረት፣ ፀፀትና ቁጣ በሽክና ጠላ ለማቀዝቀዝ ቀና ስል አይኖቼ በድንገት ከዞማለም አይኖች ጋር ተገጣጠሙና መለያየት አቃታቸው። የአይኖቻችን መገጣጠም ደግሞ ላቀዘቅዘው ያሰብኩትን ስሜት የባሰ አጋግሎ ያፈላው ጀመር። በዚያ ከነበርነው መካከል ዞማለም ስለኢህአፓ፣ ስለቀይ ሽብርና ስለደረሰውም እልቂትና ስቃይ በተሻለ ሁኔታ ታውቃለች። እኔ ትቸው ለኮበለልኩት ትግልም እሷ የከፈለችው ዋጋ ቀላል እንዳልነበርና ለወሬ ዘግናኝ እንደሆነም ሰምቻለሁ።

አይኖቿ የራሴን ቅል ዘልቀው በመግባት በአእምሮዬ ውስጥ ተደብቆ የኖረውን እኔነቴን የሚመረምሩ መሰሉ ተሰማኝ። ለራሴ እንኳ ማየቱ እያሳፈረኝና እያስፈራኝ በህሊናዬ ጓዳ ተደብቆና ጨለማ ለብሶ የቆየው እኔነቴን የምታይብኝ መስሎኝ ተሸማቀቅሁ። ከአገር ከወጣሁ ጀምሮ በተጓዝኩበት መንገድ ላይ ሁሉ የአይኖቿ ብርሃን እንደባትሪ ቦግ እያሉ ከዚያን በፊት ባልታየ ሁኔታ ሲመለከቱኝ ታየኝ።

በቀይ ሽብር ዋዜማ ከአገር ከኮበለልኩ አንስቶ ኢትዮጵያዊነቴ ደረጃ በደረጃ ሲወየብና ሲሸመደመድ ይታያት ይሆናል። ከአገር በወጣሁበት ዓመት ራሴን በአንድ የውጭ አገር የኢሚግሬሽን ኃላፊ ፊት ቆሜ አየሁት።

የሄድኩት የሰውየው አገር የፖለቲካ ጥገኝነት እንዲሰጠኝ ለመጠየቅ ነበር። በዚያን ቀን ፈረንጁ የኢሚግሬሽን ኃላፊ ያለኝና እኔም የሰጠሁት መልስ አይረሳኝም።

ከፊት ለፊቱ ችግሬን የሚያስረዳውን መዝገብ አገላብጦ ካየ በኋላ ፈረንጁ ቀና አለና «የፖለቲካ ጥገኝነት በዚህ አገር ኢትዮጵያዊ ሲጠይቅ አንተ የመጀመሪያው ነህ። በእርግጥ በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ጊዜ ንጉሠ ነገሥቱን ጨምሮ ጥቂት ኢትዮጵያውያን እዚህ በስደት እንደነበሩ ሰምቻለሁ። ያ ግን ሌላ ጊዜ ነበር። እኔም ያኔ አገርና መንግሥት አልነበረኝም።»

በእርግጥም ከ1968 በፊት በየትኛውም አገር ቢሆን ለኢትዮጵያዊ ጥገኝነት መጠየቅ ያልተለመደ ብቻ ሳይሆን አሳፋሪ ነውርም ነበር። እንኳንስ ጠላት ከውጭ ባልመጣበት ጊዜ ቢመጣም እንኳ ኢትዮጵያውያን ታግለው በሞት እንጅ በፍርሀት በህይወት ከአገራቸው የሚለዩ አልነበሩም። እንኳንስ አገርን ያክል ነገር ቀርቶ ስንቱ የአገሬ ሰው የበሬ ግንባር የምታህል ርስቱን አላስነካም እያለ ይሸፍት ነበር። ያ ሁሉ ቀረና በእኛ ትውልድ ዘመን የዜግነት መብትን፣ ነፃነትን፣ ክብርና ኩራትን እያስረከብኩ መኮብለል ሆነ። ይህን የሐፍረት ምዕራፍ በታሪካችን ከጀመሩት እኔም አንዱ ነኝ። ወኔ–አልባ ዘመን በእኛ ተጀመረ።

«ለመሆኑ» አለኝ የኢሚግሬሽን ኃላፊው ፈረንጅ፣ «በኢትዮጵያ ካሉት ኢትዮጵያውያን በተለየ ሁኔታ መንግሥት አንተን ተከታትሎ ሊይዝ፣ ሊያስርና ሊገል የሚፈልግበት ምን ምክንያት አለው?» አለኝ።

የፖለቲካ ጥገኝነት የሞላ ሁሉ እንደሚያውቀው በየትኛውም አገር ለአመልካች የሚቀርበው ወሳኝ ጥያቄ ይኸው ነው። ጥገኝነቱ ሊሰምርም ሆነ ሊከሽፍ የሚችለው ለዚህ ለሚሰጠው አሳማኝና በመረጃ የተጨበጠ መልስ ነው።

ይህ ጥያቄ ይገጥመኛል ብዬ አልጠበቅሁም። ለዚህም ትክክለኛ መልስ ሊሆን የሚችል ነገር በመዝገቤ ላይ አልሰፈረም። ልሰጠው የምችለው መልስ «በሌሎቹ ላይ ያልደረሰ መከራ ይደርስብኛል ብዬ በመስጋት ሳይሆን

በሌሎቹ ላይ የደረሰው እንዳይደርስብኝ ፈርቼ ነው።» ነበር። ይህን መናገር ግን ጥገኝነት አያስገኝም። ስለዚህም ቅጥፈቴን ጀመርኩ፣ ጊዜው ደግሞ ኢትዮጵያውያን በስደተኛነት ገና ያልተሰለቹበት ጊዜ ስለነበር ለመቅጠፍ አመቸኝ።

«አባቴ ያለፍርድ ከተረሸኑት 61 ሰዎች መካከል አንዱ ናቸው። ሁለት ወንድሞቼ ራሳቸውን ተሳዋተው ወህኒ ወርደዋል። እኔም ስፈልግ አምልጨ ነው የመጣሁት።» አልኩት። ያችን በአብዮት መባቻ ላይ ተዘፍና ገጣሚውን ያዠለጠች ዘፈን፣ «ሎሚ ተራ ተራ»ን ወረድኩለት።

የ61ዱ መሣፍንትና መኳንንት «የቅዳሜ እልቂት» አንድ ሰሞን ዘግናኝ የዓለም ዜና ሆኖ ስለሰነበተ ለኢምግሬሽን ኃላፊው እንግዳ ነገር አልሆነበትም። ከተረሸኑት መካከል ያንዱን ስም ጠርቼ አባቴ ነበሩ ማለቴን እብለት እንደሆነ የሚያውቅበት መንገድ አልነበረውም። ጠይቆ እንዳይረዳ እንኳ በአገሩ ውስጥ የኢትዮጵያ ኤምባሲ አልነበረም።

ደርግ በአጤውና በመኳንንቱ ላይ ከስልጣን ማውረድ አንስቶ እስከሞት ቅጣት በወሰደው ርምጃ ላይ መቃወም ቀርቶ መከፋትም እንዳልነበረኝ ሰውየው አያውቅም። እንዲያውም «በቅዳሜው እልቂት» ማግስት ደርግ አበጀ ማለቴን አስታውሳለሁ። አጤው ከዙፋን ወርደው በትንሽ መኪና ዘብጥያ ሲወርዱም መኪናውን እየተከታተሉ «ሌባ፣ ሌባ» ሲሉ ከነበሩት መካከል አንዱ ነበርኩ።

ነገሩ እንዲህ ሆኖ ሳለ ያልተወለድኩበትን ቤት ተወለድኩበት በማለት የማላውቃቸውንም መስፍን ሞት እማኝ አድርጌ የፖለቲካ ጥገኝነት አገኘሁ። ከፈሪነቴና ከወኔ–አልባነቴ በተጨማሪ ያልሆንኩትን ሆኜ ለመገኘት መቅጠፍ የጀመርኩት ያኔ ነበር። እኔን መሰሉ ስደተኛ ሁሉም በአይነቱና በይዘቱ ይለያይ እንጅ በተመሳሳይ ፍርሀት የተገነባና በቅጥፈት የተካነ ነው።

በዚያ በነበርኩበት አገር ሁሉ ዛሬ ነገ ቅጥፈቴ ተጋልጦ ዘብጥያ እወርዳለሁ፣ የባሰውንም ከአገር ውጣ ተብዬ በግዳጅ ወደ ኢትዮጵያ እላካለሁ እያልኩ ሳልሰጋ የቀረሁበት ጊዜ የለም። ደግነቱ ልጅ ተወልዶ ለእረኝነት የሚበቃበትን እድሜ

ያህል ከቆየሁ በኋላ ራሴው ለቅቄ ወደ ሌላ አገር ሌላ ቅጥፈት ይዤ ገባሁ።

በሰው አገር ባዕዳንን ተጐራብቼ ለመኖር ያስገደደኝን እውነተኛ ምክንያት በግንባር መፋለም የጀመርኩት አሜሪካ ከገባሁ በኋላ ነው። ከዚያ በፊት በነበርኩበት አገር ኢትዮጵያውያን ስደተኞች በቁጥር ነበሩ። በዚህም የተነሳ በዓመት ውስጥ የምንገናኝበት ጊዜ በጣም የተወሰነ ነበር። የዚህ ጠቃሚነቱ ሁላችንም በብቸኝነት የፈለግነውን መስለን ለመኖር መቻላችን ነበር። ብቻውን ያለ ሰው ስለራሱም ሆነ ስለዓለም የፈለገውን ማሰብና ማለት ይችላል። እሱነቱንና መሳሳቱን ነፀብራቅ አድርጐ ሊያሳየው የሚችለው ነገር የለም። ሰው መስታወት ካላየ ወይም ተመልካች ካልነገረው የፊቱን ጉድፍ ማየት አይችልም።

አሜሪካ ግን የተለየ ነው። በዚህ አገር ከማንኛውም አገር በበለጠ ኢትዮጵያውያን ተሰባስበው ይገኛሉ። የስደተኛው ሁሉ መጨረሻ ገነት አሜሪካ ነው ቢባል መሳሳት አይሆንም። የድሮ ሰዎች በእርጅና ዘመናቸው «አሟሟቴን አሳምርልኝ፣ ለመንግሥተ–ሰማያትም አብቃኝ» ብለው ይፀልዩ እንደነበር የዘመኑ ኢትዮጵያዊ ስደተኛም «ለአሜሪካ አገር አብቃኝ» ብሎ ይፀልያል ቢባል ማጋነን አይሆንም።

ከአሜሪካ ግዛቶች ደግሞ እንደዋሽንግተን ከተማ ኢትዮጵያውያን በዝተው የሚገኙበት የትም የለ። አርብና ቅዳሜ ዠንበር ስትጠልቅ በአስራ–ስምንተኛው ጐዳና ላይ ወርዶ ያቀና ሰው አሜሪካ ሳይሆን ኢትዮጵያ ያውም መርካቶ፣ ካዛንችስና ፒያሳ ያለ ነው የሚመስለው። ብዛት ያላቸው የኢትዮጵያ ምግብ ቤቶች ግራና ቀኝ ተደርድረዋል። በእያንዳንዱ ምግብ ቤት ተመጋቢም ባይኖር የጠጭው ብዛት በደርግ ዘመን ድራፍት ቢራ አለ በተባለበት ቡና ቤት ይታይ ከነበረው ሰው የሚያንስ አይደለም። የቻለ ተቀምጦ ያልቻለ ቆሞ የኢትዮጵያውያን ስደተኞች የማህተም መጠጥ የሆነውን የሀይንከን ቢራውን አለያም ኮኛኩን ያንደቀድቃል። ኢትዮጵያውያን ስደተኞች ለምን ከመጠጥ ሁሉ እነዚህ ጠንካራና ውድ የሆኑ መጠጦችን እንደሚመርጡ ራሱን የቻለ

ወግ ነው።

ለውጭ ተመልካች ሁሉም ደስተኛ መስለው ይታያሉ። አካባቢያቸው የደስታ ፍፍቴ የሚወርድበት በመሆኑም ከዚህ የተለየ ለመገመት አስቸጋሪ ነው። ለደስታቸው አድማስ መስፋት ደግሞ ከቡና ቤቶቹና ምግብ ቤቶቹ መብዛት በተጨማሪ አገር ያፈራቻቸው አዝማሪዎች በመኖራቸው በየምሽቱ ባማረ ድምፅ ዘፈኑን ያንቆረቁሩታል።

ሆኖም ግን፣ የደስታውን ደመና ዘልቆ ለሚያይ ሰው በኢትዮጵያውያኑ ገፅ ላይ የሚታየው ደስታ ሳይሆን ምንነቱ በውል የማይታወቅ የተሸመደመደ ስሜት ነው። ተለይቶ የደስታም፣ የሀዘንም፣ የብቸኝነትም ተብሎ ሊጠራ የማይችል፣ ምናልባትም እነዚህን ሁሉ አጣምሮ መልክና ቅርፅ የሌለው ስሜት ሊሆን ይችላል። ሽምድምድ ነገር እንደዚያ ነው።

ሰማንያ ከመቋጠሬ በፊት በየዕለቱ፣ ከሰማንያ በኋላ ደግሞ ምክንያት እንዳገኘሁ እኔም ወደነዚሁ ቡና ቤቶች እሄድ ነበር። የምሄድበት ዋናው ምክንያት ለመዝናናት ሳይሆን የእኔነቴን ከንቱ ነፀብራቅ በሌሎች ላይ አይቼ ለመፅናናት፣ ባይተዋር አለመሆኔንም ለማረጋገጥ ነው። እድሜዬ ሰላሳ ከሆነ በኋላ መጠጥና ሙዚቃ እኔን ማዝናናቱን ትተውታልና በዚህ እድሜዬ ቡና ቤት ገብቼ እዝናናለሁ ብል ሽበቴ ሳይቀር ይገረማል።

ባልኮኒ ላይ እቀመጥና ባልኮኒ ላይ ከተቀመጡት ሌሎች ሰዎች አንስቶ በቡና ቤቱ ጠረጴዛዎች ዙርያ የተቀመጡትን ሰዎች አንድ በአንድ፣ ተራ በተራ እቃኛለሁ። አስተያየቴ ሰው የምፈልግ ይመስላል። የማየው ግን በውጭ አካላቸው አምረውና ደምቀው ሀይንከንና ኮኛክ እየተጉነጩ መነሻ፣ መድረሻና እልባት የሌለው ወግ የሚያወጉትን ተጋባዦች አይደለም። እነዚህን በሙሉም ባይሆን ብዙዎቹን አውቃቸዋለሁ። የማየው በእነዚህ በቡና ቤት ደምበኞች ውስጥ እንደእኔ በሀፍረት፣ በፀፀትና በከንቱነት ተተብትቦ መንቀሳቀሻ ያጣ ኢትዮጵያዊ ህሊና እንዳለ ነው። ከውጭ አገር ኑሮዬ እንደምገነዘበው እንዲህ ያለ ህሊና ስለመኖሩ ጥርጥር የለኝም።

ይልቁንም የአብዛኛው ስደተኛ መንፈስ በእንዲህ ያለ የከፋ ሁኔታ ላይ የሚገኝ ነው።

ሆኖም ግን፣ ይህ ደግሞ ከኢትዮጵያውያን ስደተኞች ባህርይ እጅግ አስገራሚው ነው፣ ስደተኞቹ የውስጥ ስሜታቸውንና ማንነታቸውን ለተመልካች እንዳይታይ በህሊናቸው አስርገው አካባቢያቸውን መስለውና ተማስለው ይታያሉ። የውስጥ የህሊና ቤታቸው እየተሸረሸረና እየተናደ የውጭ ማንነታቸው አምሮና ደምቆ ይታያል። ምናልባት ይህ የኢትዮጵያዊነት የረቀቀ ባህርይ ሊሆን ይችላል። ሁለት ተቃራኒዎች፣ ደስታና ሀዘን፣ በአንድነት ተዋህደው የሚኖሩበት ስብዕና ከኢትዮጵያውያን ውጭ ብዙም አይኖርም።

የዞማለም አይኖች የሚመለከቱት ምናልባት የባልኮኒ ደንበኝነቴን፣ የአርብና ቅዳሜ ብቻ አለማዊነቴን ሳይሆን ይችላል። ከሆነ በዚህ አትገረምም። እኔን፣ በእኔም ነፀብራቅ ሌሎችን አይታ ስደት ሁሉ ከንቱ ነው ብላ በቀላሉ መደምደም ትችላለች። ሊያስገርማት የሚችለው የእሁድና የበዓላት ቀናት እኔነቴን ነው።

በሰንበትና ታቦታት በሚነግሱበት እለት ከቤተ–ክርስቲያን አልጠፋም። ባለሁበት ከተማ ደግሞ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ–ክርስቲያን እጥረት የለም። ፅላቱም ካህናቱም በብዛት ይገኛሉ። ይህ ባልከፋ ነበር። ሆኖም ግን ያለነው በስደት አምባ ነውና መሠረታዊ የህሊና ጥያቄዎችን ያነሳል።

ቤተ–ክርስቲያን ከተገኘሁ በሁዋላ ቄሱ «አሀዱ» ብሎ ቅዳሴ ከጀመረ አንስቶ «በሰላም ወደ ቤታችሁ ግቡ» ብለው እስኪያሰናብቱ ድረስ አእምሮዬ ከመንፈሳዊ ትኩረቱ እየዘለለ በአለማዊ ሀተታ ላይ ገብቶ ይተበተባል። ካህናቱንና ምዕመናኑን በራሴ ነፀብራቅ ማየት እጀምርና «ሀገረ–እግዚአብሔር» ተብላ ከምትታወቅ አገር ኢትዮጵያ ስጋዊ ፈተናን ሸሽተን የመጣን ሰዎች በአረማውያን አምባ የምናደርሰው ፀሎት ምን ያህል ተሰሚነት እንዳለው እጠይቃለሁ። እግዚአብሔር ካለበት ከአገረ–እግዚአብሔር

ሸሽተን የመጣን ሰዎች እንደምን አርገን እግዚአብሔር እኛ በምናውቀው መልኩ፣ ባህርዩና ህልውናው በሌለበት ዓለም እንደምንጠራው እንቆቅልሽ ነው።

የአእምሮዬ መንከራተት ከዚህም አልፎ ወደ ቁጣ ያመራል። ለዚህ ብዙ ጊዜ መንስዔ የሚሆነው በአንዳንድ በዓላት ቀን ፀሎት ሲመሩ የማያቸው መንፈሳውያን አባቶች ናቸው። አገር እንደሚያውቀው ከኢትዮጵያ የተሰደደው እንደእኔ ያለው ጨዋው ብቻ ሳይሆን ቤተ–ክርስቲያናችን «ብፁዕ ወቅዱስ» ብላ ማዕረገ–ጵጵስና ፓትርያርክነት የሰጠቻቸው ሁሉ ናቸው። አዎ አራተኛው የኢትዮጵያ ፓትርያርክና ብዛት ያላቸው ሌሎች ሊቀ ጳጳሳትም አገርና ምዕመናንን ለአረማውያን ትተው ወደዚሁ ወደ ስደት አምባ ኮብልለዋል። ህሊና ፓትርያርክና ጳጳሳት እንደምን አርገው ቤተ–እግዚአብሔርንና ምዕመናን ጥለው ይሸሻሉ ብሎ ይጠይቃል? የቀደሙ አበው ካህናትና ጳጳሳት ለኃይማኖታቸውና ለአገራቸው ሲሉ አንገታቸውን በሰይፍ ያስመቱ፣ የሟፍ ቀሚስ ለብሰው በእሳት የተቃጠሉ፣ በመትረየስ የተደበደቡ መሆኑ ሲታወስ ደግሞ የአሁኑ የስደት ጳጳሳት «ብፁዕ ወቅዱስነት» ያስጠይቃል። በአገር ደረጃ ፀፀቱ፣ ሀዘኑና ሀፍረቱ የዛሬው የኢትዮጵያ ትውልድ ወኔ–አልባና ደካማ እየሆነ ከተራው ጨዋ እስከ ፓትርያርክ ድረስ የፍርሀት ኮብላይ ሆኖ መገኘቱ ነው። ለዚህ የኢትዮጵያዊነት ጉድፍ መድኃኒቱ ምን እንደሆነ ለመጠቆም አስቸጋሪ ነው።

እርግጥ ነው ለእንደኔ ያለው ስደተኛ የፓትርያርኩ፣ የጳጳሳቱ፣ የታላቅ ምሁራንና ሊቃውንት መሰደድ እንደመፅናኛ ሆኖ ሊታይ ይችላል። እነሱ ከእኛ የበለጠ ለአገር ጠቃሚ እውቀቱም እምነቱም እያላቸው ከተሰደዱ የእኛ ምን ያስገርማል ይባል ይሆናል። ጉንደሬ እንደሚለው ግምኛ ለትውልድ የምናሳፍር ነን።

በህሊናዬ ውስጥ ሰጥሜ እንዲህ ስባዝቅ ፀጥታ ሰፍኖ ኖሮ፣ ዞማለም መናገር ስትጀምር ቀና አልኩ።

«መራ–ሃይማኖት፣ ወንድሜ አጉናፍር፣ በቀይ ሽብር በራሴም ሆነ በሌሎች የአህአፓ ጓዶቼ ላይ ስለደረሰው መናገር

አልወድም። በተቻለኝ መጠን ለመርሳት ነው የምሞክረው። ያ ጊዜ አረመኔያዊነት የኢትዮጵያውያንን ስብዕና፣ ህልውናና ማንነት የገሰሰበት ጊዜ ነበር። ያም አረመኔነት ከውጭ የመጣብን ሳይሆን ከእኛ ከራሳችን ኢትዮጵያዊነት ውስጥ ፈልቆ የወጣ ነው። ኢትዮጵያዊነት ጨካኝ ገፅታውን ያሳየበት ጊዜ ነው። ይህን ጊዜ መርሳት ብቻ ነው ፈውስ የሚሆነው።

ሆኖም ግን አንተ ከትግሉ ተለይተህ ወደ ውጭ በመሄድህ በኢትዮጵያዊነትህ የምታፍር እንዳይሆን እኛ በአገር የቀረነው ለኢትዮጵያዊነታችንም የሚያኮራ ሥራ እንዳልሰራን ልንገርህ። እኛም የቀረነው እንዳንተው በማንነታችን የምናፍር ስለሆነ ትውልድን ቀና ብለን ማየቱ ያዳግተኛል።

ቀደም ሲል አወል ጀማል ስለሚባል ወዳጅህ አንስተህ ነበር። እንደእሱ አይነቶቹ በጊዜው ላመኑበት አላማ ራሳቸውን መስዋዕት ያደረጉ መሆኑ አያጠያይቅም። ሆኖም ግን ከመስዋዕትነቱ የተገኘው ምንድነው? ያን ያህል የደምና የህይወት መስዋዕት መክፈሉስ አስፈላጊ ነበር ወይ? አወል በወጣት አእምሮው አስተውሎ ከመሰንበት መሞትን መረጠ፣ ቤተሰቦቹ ግን ቢሰነብትላቸው ይመርጡ ነበር። አየህ! በቀይ ሽብር ጊዜ ልጇ ተገሎ ሬሳውን ከገዳይ ላይ ገዝታ ሳታለቅስ እንድትቀብር የተገደደች እናት ምንጊዜም ቢሆን በኢትዮጵያዊነቷ ሀፍረትና ምሬት እንጅ ኩራት አይሰማትም። ለትውልድ ስትነግረው የምትኖረውም በዚያ በክፉ ቀን እሷ ሳትሆን እሷን ኢትዮጵያዊነቷ እንዴት እንደከዳት ነው።

ከሞት የተረፍነውም የተሻለ የሚያኮራ ትዝታ የለንም። ስለራሴው ልንገርህ።

የተያዝኩት ጉንደር ነበር። እንደሰማኸው ጉንደር ደግሞ መላኩ ተፈራ በጉንደር ልጆች ላይ የእልቂት ጉራዴ መዞ ደም እንደውኃ ያፈሰሰበት፣ አፅም እንደተራራ የተቆለለበት አገር ነው። ለጭካኔው በታሪክም ሆነ በተረት ተወዳዳሪ አይገኝለትም። ከእሱ ጉን ግራዚያኒና ጭራቅ ቆመው ቢታዩ መልአክ ይመስላሉ። ሃይማኖትና ህሊና የሌለው የአርባ–አራቱ ታቦት አማላጅነት የማይሰማው ሰው ነበር። በዚህም

የተነሳ ይመስላል የጐንደር ህዝብ ቢጨንቀው፣
መላኩ ተፈራ የእግዜር ታናሽ ወንድም፣
ያሁኑን ማርልን ሁለተኛ አንወልድም።

ብሎ የተማጠነው።

ለሁሉም፣ ከተያዝኩ በኋላ የደረሰብኝን የቅጣት ዓይነትና ስቃይ መዘርዘሩ አያስፈልግም። ከሰውነት ክፍል ከውስጥ እግሬ ጀምሮ እስከ ራሴ ድረስ ተደብድቦ ያልደማና ያልቆሰለ የለም። ከመደብደብ እረፍት አገኝ የነበረው ደብዳቢዎቼ ሲደክማቸው ብቻ ነበር። ስቃዩ ይህ ብቻ አልነበረም። ቢሆን ኖሮ ቁስሉ ሲሽር አብሮ ይረሳኝ ነበር።

በዚያን ጊዜ ሴት ልጅ ተለይታ የምትሰቃይበት ሌላ ምክንያት ነበር። እንደዚያ በስቃይ እጅግ ተዳክሜና ግማሽ ሙት ግማሽ ህያው በነበርኩበት ጊዜ አሰቃዮቼ ሴትነቴን ከመድፈር ወደኋላ አላሉም። ከእናት እንዳልተወለዱ፣ እህት እንደሌላቸው፣ ሴት ልጅም እንደማይኖራቸው፣ በጭካኔ ክብሬን ገፈፉት። ይህ ቁስል አይድንም።

ዛሬ እኔ በኢህአፓ ተደራጅቼ መታገሌን፣ በዚያም ሳቢያ የስቃይ ፅዋ መቅመሴን እንደ ኢትዮጵያዊነት ኩራት አላየውም። የዚያ ሁሉ ስቃይና እልቂት እማኝ ሆኖ ማለፍ ሀፍረትና ፀፀት ብቻ ነው በህሊናን ውስጥ የሚዘራው። በእርግጥ ትግሉ በድል ቢደመደም ኖሮ ትዝታው ሌላ ይሆን ነበር።

ፍሬ ነገሩ ይህ ነው፤ ከተከፈለው መስዋዕትነት ምንም የተገኘ ውጤት ስለሌለ አንተ እዚህ ብትሆን ኖሮ በሞትህ ወይም በእስራትህ ትጨምር ወይም ትቀንስ የነበረው ምንም የለም። ጊዜው የእብደት ዘመን ነበር። ገዳይ፣ ተገዳይ፣ አስገዳይ፤ ገራፊ፣ ተገራፊ፣ አስገራፊ፤ ፈሪና ጉበዝ ሁሉም በአንድነት ያበዱበት ጊዜ ነበር። በጋራ እብደት የጋራ አገራችንን አጠፋን።» አለችና ዞማለም የራሷ ፀፀት ተሰምቷት ዝም አለች።

በእርግጥ «ማን ያውራ የነበረ፣ ማን ያርዳ የቀበረ» እንዲሉ ከእሷ አንፃር ሲታይ የኢህአፓ ትግል ባለችው ሊደመደም ይችል ይሆናል። ይህን ግን ኢህአፓንና አባላቱን

በሚመለከት እኔ በውስጤ የሚሰማኝን ፀፀትና የበታችነት ስሜት አያቀለውም።

ውጤቱ ምንም ይሁን ምን እንደዞማለም በቆራጥነት ለአገራችንና ለህዝባችን ነፃነትና መብት እንታገላለን፤ ለትግላችን ዓላማም አስፈላጊ ከሆነ እንሰዋለን ብሎ የተነሳ ትውልድ በኢትዮጵያ ውስጥ ከጣሊያን ወዲህ ሲታይ ኢህአፓ የኢትዮጵያዊነትን ወኔ የተላበሰ የመጀመሪያው ድርጅት ነው። ዓላማው ባለመሳካቱ ብቻ የታሰሩና የተገደሉበት አባሎቹን መስዋዕትነት ማቅለል ወይም ማራከስ አይቻልም።

ውጭ በቆየሁባቸው ዓመታት ለእኔ እጅግ አስቸጋሪ የነበረው በአንዳንድ አጋጣሚ የማገኛቸውን የቀድሞ የእህአፓ አባላት ቀና ብሎ ማየቱ ነበር። ስተዋወቃቸው ወይም ሌላ ሰው ስለእነሱ ማንነት ሲነግረኝ ምን ያህል ጊዜ በእስር ቤት እንደቆዩ፣ የትና እንዴት እንደተሰቃዩ፣ በስደት በሱዳን፣ በኬንያና በጅቡቲ ስላሳለፉት ችግር እገነዘባለሁ። ብዙዎቹ የእድሜ እኩዮቼ ናቸው። እኔና እነሱን የሚለየን እነሱ በእድሜያቸው በወኔና በቆራጥነት የኢትዮጵያዊነት ግዴታቸውን የተወጡ እኔ ግን ገና በትግሉ ጭስ በርግጌ የኮበለልኩ ወኔ አልባ፣ ፈሪ መሆኔ ነው። ለእነሱ ይህ ልዩነት ላይታያቸው ይችላል። ልዩነትም አያደርጉም። እንደእኔ ያለ ግን እውነተኛ ህሊና ካለው «ምነው ያችን ሰዓት ከጉበዝ አምባ ባሳለፍኩ ኖሮ» ብሎ መፀፀቱ አይቀርም።

እርግጥ ነው አንዳንድ የገዛ ፍርሀታቸውን፣ ድክመታቸውንና ኩብለላቸውን፣ ሲከፋም ባንዳነታቸውን ለመሸፈን ከብዙ ዓመታት በኋላ እንኳ ያለ እፍረት ኢህአፓን የሚኮንኑ፣ የተሰዉትንም ክብር ለመቀነስ የሚጥሩ ሞልተዋል። የፈሪ ልብ የሚሳነው ጦር ሰብቆ መወርወር እንጂ ሀሜትና ስድብ ማናፋቱን ከቶ የሚተካከለው የለም።

የዞማለም ንግግር መደምደሚያ ያስፈነውን ፀጥታ የሰበረው የእኔው ኑዛዜ ነበር። እነሆ ኑዛዜዬንም ቀጠልኩ፦

«ከቀይ ሽብር በኋላ የሶማሌና የኤርትራ ጦርነቶች ተነሱ። በእነዚህ ጦርነቶችም እኔ ከማውቀው ይልቅ እናንተ እዚሁ የነበራችሁት ስለእልቂቱ ብዙ ታውቃላችሁ። ከቀይ

ሽብር የተረፈውን ዜጋ፣ በአብዛኛው ድሃውን ጦርነት በላው። እውነተኞቹ ኢትዮጵያውያን ኢትዮጵያዊነትን እንደእኔ በስም ብቻ ሳይሆን በምግባር የወረሱት ለአገራቸው ተሰዉ።

እኔ ያንጊዜም ቢሆን ውጭ አገር በተድላ ነበርኩ። እዚህ እንደነበራችሁት ለአገሬ ለኢትዮጵያ ነፃነትና አንድነት ልሰለፍ የሚል የሞቀ የጀግና ደም በውስጤ አልነበረም። አገርና ህዝብ በውስጥ በኩል በደርግ፣ በውጭ በኩል በጠላት ሲመዘበር፣ ሲፈጅ፣ ኤሎሄ ሲል እኔ በፈረምች ስደት አምባ ነበርኩ።» አልኩና በገዛ ሀፍረቴ የተሸማቀቀው ሰውነቴ እንዲፍታታ፣ በከንቱነቴ ያረረው አእምሮዬ እንዲቀዘቅዝ፣ አንደበቴም እንዲለሰልስ ከፊቴ ከነበረው ዋርማ ጠላ ደጋግሜ ተጉነጨሁ።

አጠገቤ የነበሩት ወዳጆቼ ድንገት ወዳላሰቡት አቅጣጫ እንደመሩኝ ተገንዝበው ወሬውን ለመለወጥ ጥረት አደረጉ። እኔ ግን ብዙ ጊዜ ውስጥ ውስጤን ሲያብከነክነኝ የነበረው ጉዳይ ስለነበር ለእነሱ መናዘዙን ፈውስ ሆኖ ስላገኘሁት ወሬ መቀየሩ አስፈላጊ አልመሰለኝም። እንባቆም ለማፅናናት በሚል መልክ «ጥሞትና ከእስር ለመዳን ስትሉ ውጭ አገር ብትሄዱም ተምራችኋል። የተማረ ሰው ደግሞ ለአገር ምንጊዜም ጠቃሚ ነው» አለ።

አባባሉ እውነታ ቢኖረው ምንኛ አገርና ህዝብ በታደሉ ነበር። ሆኖም ግን ከራሴ ጀምሮ ከአገር የወጣነው ብዙዎቻችን ትምህርትን፣ እውቀትን ከየግል ሀሊናችን ማስታመሚያነትና ማርኪያነት አልፎ ለአገርና ለወገን የሚጠቅም አርገን እንዳላቀረብነው፣ የዚህም ዓይነት የፀና ምኞት እንዳልነበረን አውቃለሁ።

አዎ፣ ከእኔ በፊት፣ ከእኔ ጋር፣ ከእኔም በኋላ አገራችን ውስጥ ከነበረው እልቂት እያመለጡ ወደ ፈረንጅ አገር የመጡ አሉ። የብዙዎቹ መጨረሻ ማረፊያ ቦታም ዩኒቨርስቲዎች ናቸው። በአውሮፓና በአሜሪካ ዩኒቨርስቲዎችን ምሽግ አርገው የተቀመጡ ኢትዮጵያውያን ቁጥር ቀላል አይደለም። መማር ጥሩ ቢሆንም ተምሮ አገርና ወገን ማገልገል ካልተቻለ ዋጋ የለውም። እነዚህ የዩኒቨርስቲው

የአገር ልጆችም በተማሩት አገርና ወገን ቀርቶ በሙያቸው ሰርተው ራሳቸውን ማሳደር የሚችሉ አልሆኑም።

በዚህም የተነሳ ብዙዎች በያሉበት ዩኒቨርስቲ እድሜ-ልክ ተማሪ ሆነው ይገኛሉ። ዲግሪ በዲግሪ ላይ ይጨምራሉ። በየቤታቸው ግድግዳ ላይም እንደአርበኝነት ኒሻን ዲግሪያቸውን ይደረድራሉ። ይህንንም በማየት ራሳቸውን ያፅናናሉ።

ለምን ወደአገር አይመለሱም? ይሉ ይሆናል። ለዚህ መሠረታዊ ጥያቄ ሁሉም የተማረ ስደተኛ ለራሱ የሚመቸውን መልስ እንደሚያቀነቅን የታወቀ ነው። እኔም በዚሁ የተካንኩ ነኝ። ለእናንተ ለባልንጀሮቼ ግን እውነቱን መናገር ይገባኛል።

የተማረው የማይመለስበት ዋናው ምክንያት ፍራቻ ነው። መጀመሪያውንም ከአገር ያስወጣው ትምህርት ፍለጋ ሳይሆን ፍርሀት ነው። በአገሩ እንደሌሎች በመወለድና በፀጋ ለወረሰው የዜግነት መብት ከመታገል ይልቅ የፈረጠጠ ነው። መብቱን አስቀምቶ ብቻ ሳይሆን አስረክቦ የሸሸ ትውልድ ነው። መታገል መስዋዕትነትን ይጠይቃል። የፈሪ ልቡና ደግሞ የተገነባው በመሰንበት ዘይቤ ስለሆነ መስዋዕትነትን በሆነው መንገድ ያስወግዳል። ታዲያ የመፈርጠማው አቢይ ምክንያት ይህ ሆኖ ሳለ ውጭ አገር ከተደረሰ በኋላ ትምህርት አመቺ የፍርሀት መሸፈኛ ካባ ይሆናል።

ትምህርቱ ካለቀ በኋላም በእያንዳንዱ የተማረ ሰው ልብ ውስጥ ፍራቻው እንደአገራችን ሙክት ይሰባና ወደአገር ለመመለስ እንዳያስብ ያደርገዋል። ለዚህኛው ችግር ደግሞ አገራችን የምትወልደው ሌላ ጥሩ አመቺ ምክንያት አለ። ይህም ያለው መንግሥት አምባገነን ስለሆነ ብንመለስ ይገለናል፣ ያስረናል ወይም አያሰራንም ነው። ስለዚህም፣ ይላል የፈሪ ዘይቤ፣ በዚሁ በውጭ ሆነን አምባገነኑ መንግሥት እንዲወድቅ እንታገላለን።

ፍሬ ነገሩ፣ እኛ ፈረንጅ አገር ድረስ ሄደን የተማርን ስለሆነ እንደሌላው እንደድሃውና እንዳልተማረው በግንባር ተሰልፈን ለዜግነት መብታችን ለመታገል ክብራችን አይፈቅድምና በአገር ያለው ህዝብ ተሰውቶ አምባገነኑን ሲጥል

መጥተን አዲስ መንግሥት እናቆማለን ነው። የፈሪ ልብ ይህን ያስባል። ከአጤ ኃይለ ስላሴ ኩብለላ የተወረሰ የፈሪ ዘይቤ ነው። እርግጠኛ ነኝ የነደጃች ታከለ ወልደሐዋርያትና በላይ ዘለቀ አፅም ይህን እየሰማ በከርሰ መቃብር በንዴት መፈራገጡ አይቀርም። ስደተኛ አፋፍ ላይ ቆሞ ወገኑን የሚያስመታ ነው።

ለመሆኑ በውጭ ያለው የተማረ ኢትዮጵያዊ ለአገሩ እታገላለሁ የሚለው በምን መልኩ ነው ይሉ ይሆናል።

ጦር ሰብቆ፣ ቃታ ስቦ፣ ጉራዴ መዞ አይደለም። ይኼማ የነዘርዓይ ደረስሙያ ነው። በጠላት አገር የጠላት አንገት የሚሰይፍ የጀግና ልብ ከወዴት አለና። «ከመሞት መሰንበት» በሚል ዘይቤ ለተገነባ ሰውነት አፍንጫ እንዲህ ያለው አይሸትም። ሰይፍ ቀርቶ ብዕራቸውን የሚነቀንቁ በቁጥር ናቸው። እነዚህም ብዕራቸውን የሚነቀንቁት በአብዛኛው አገር ውስጥ ባለው የጋራ ጠላት ላይ ሳይሆን እርስ በርሳቸው ነው። ይወነጃጀላሉ፣ ይካካዳሉ፣ ይነታረካሉ። የፈሪ ኑሮ እንዲህ ነው።

ወንድሞቼ፣ እህቴ ዞማለም፣

በውጭ ኢትዮጵያውያን ዘንድ ያለው ትግል የእርስ በእርስ ትግል እንጂ ለአገር ተብሎ የሚደረግ የጋራ ትግል አይደለም። የዚህ ትግል ዓላማም የአንዱ ግለሰብ ወይም ድርጅት ወገን ኢትዮጵያዊነት ከሌላው የተሻለ እንደሆነ እዚያው ስደት ላለው ሰው ለማሳየት ነው። እያንዳንዱ ነው ብሎ ስለሚገምተው ስለራሱ ኢትዮጵያዊነት ምንነት ሀሌታ ያሰማል፣ ከበሮ ይደልቃል፣ ይደነፋል። ሰው መረዳት ያቃተው የሁሉም ኢትዮጵያዊነት ከንቱ ብቻ ሳይሆን በትውልድ አይን አሳፋሪ መሆኑን ነው። ይህ አይታይም። ይህን ማየት የራስን ደካማነት መገንዘብ ይሆናል።

አዎ በተለይ በቅርብ ዓመታት በአገር ደረጃም ሆነ በጉሳ ደረጃ በኢትዮጵያ ያለውን ህዝብ ከጭቆና ቀንበር ለማላቀቅ ያልተቋቋመ ድርጅት የለም። በነጋ በጠባ እንደደርግ ስብሰባ ይደረጋል። በጋራ አገር ውስጥ ያለው ጨቋኝ መንግሥት ይኮነናል። ለመኩነን ወደኋላ የሚል ከቶ ማንም

የለም። እንዲያውም እዚህ ያለውን የወያኔ መንግሥት መኩነን አዲሱ የኢትዮጵያዊነት ምልክት እየሆነ ከመጣ ሰንብቷል። መንግሥት በእርግማን ሲወድቅ መቼ ታይቶ ያውቃል! ያውምኮ የድሮ አባቶችና እናቶች እንደሚያደርጉት ከልብ የመነጨ እርግማን አይደለም። እንዲህ ዓይነቱ እርግማን ቢሆንማ ኖሮ እንደነ ዮዲት፣ ግራኝና መንግስቱ ያሉትን ቀታሌ መንግስት ያስነሳ ነበር። ይህ የስደተኛው እርግማን ግን ለይስሙላ «ተባለ-እኮ» እንዲባል ብቻ የሚደረግ ነው። ፍርሀትን በእርግማን መሸፈን እንዲሉ የስደተኛው ትግል ተጀምሮ የሚቋጨው በከንቱ ፉከራ ነው።

አብዛኛው ስደተኛ ኢትዮጵያዊነትን ቀርቶ ኢትዮጵያ ምን እንደሆነች ማወቁም ያጠራጥራል። ለአብዛኛው ኢትዮጵያ ማለት በምስሏ የሚገለጠው ካርታዋ፣ ሰንደቅ ዓላማዋና የባህል ልብሷ ነው። ከዚህ የጠለቀ የኢትዮጵያዊነት ግንዛቤ ብዙም የለ። ሙሾ የሚወረደው ለምስሉ እንጂ ከምስሉ ባሻገር ላለው የህዝብ ህይወትና ኑሮ አይደለም።

እኔ እስከማውቀው ድረስ በአገር ውስጥ በመንግሥትም ሆነ በተፈጥሮ እጅ በሚደርሰው እልቂት ወገኔ ብሎ ያለቀሰ ወይም የእርዳታ እጁን የዘረጋ ስደተኛ በቁጥር ነው። የእናንተ የወንድሞቼና እህቴ በኢትዮጵያዊነት መሰቃየት ለአብዛኛው የማይገባው፣ እንዲገባውም የማይፈልግ ነው። እንዲህ ነው ስደተኛው።

ከስደተኛው መካከል ብዙ የተማሩና አንቱ የተባሉ አሉ። ሆኖም በስደተኛው አምባ «ዶክተርና ፕሮፌሰር» ተብለው እጅ ከመነሳታቸው ባሻገር ለአገር መታገል ቀርቶ ምህላ ሲያደርጉ አይታዩም። አንዳንዶቹ እንዲያውም እውቀታቸውን የእብሪት መከታ እያደረጉ በአገር ውስጥ ያለውን ህዝብ ወደባሰ ሰቆቃ ሊሰድ የሚችል መርዝ ከመርጨት አልተቆጠቡም።

የትግሬና የኤርትራ ህዝብ ከኢትዮጵያ ካልተባረረ ኢትዮጵያ መፍትሄ አታገኝም የሚሉ አሉ። የኦሮሞ ህዝብ ተገንጥሎ ካልወጣ ለኢትዮጵያ መፍትሄ የለም የሚሉ አሉ። የሶማሌ ህዝብ ካልተገነጠለ ኢትዮጵያ የለም የሚሉ አሉ።

የአንዱ ጕሳ ወኪል ነኝ ባይ ሌላውን ይኰንናል። በጕሳው ውስጥም የአንዱ መንደር ወኪል ነኝ ባይ ሌላውን ይኰንናል። እንዲያው ለነገሩ እንጂ ጕጃምም ኢትዮጵያ አይደለም ብለው የተነሱ ነበሩ።

እኚህ ሁሉ በስደት ያሉ ምሁራን ናቸው። አንዳንዶቹ ለአገራቸውና ለወገናቸው ምንም ሳያደርጉ ረጅም ዘመን በሰው አገር መኖራቸው ህሊናቸውን ይፀፀተውና ድንገት ተነስተው ለኢትዮጵያና ለኢትዮጵያውያን ከእኔ በቀር የሚያስብ የለም ብለው አምባጓሮ ያነሳሉ። ያንኑ በስደት አምባ ያለውንም ህዝብ ይበጠብጡታል። ነገራቸውንም በየመጽሔቱ በየመጽሐፉ ያስነብባሉ። ስብሰባም እየጠሩ ያስተጋባሉ። ስደተኛው በአብዛኛው አገሩን በሚመለከት የፀፀትና የሀፍረት ካባ የተላበሰ በመሆኑ ጉዳዩን ሳይመረምር የዕለቱን ነቢይ «አበጀህ፣ በል ንገረው» እያለ ያሟሙቀዋል። ትንሽ ሰንበት ብሎ ግን ሁሉም ነገር ይረሳና ነቢዩም ተከታዩም ድምፃቸው ይጠፋል። መቸስ ዛር ያለበት ሰው የሚያጓራው ወቅቱን እየጠበቀ አይደለም።

አንድ ሰሞን በትምህርታቸው አንቱ የተባሉ አንድ ፕሮፌሰር እንዲሁ አፈፍ አሉና የትግሬ ዘር በሙሉ ከኢትዮጵያ ከነአገሩ ተቆርሶ ካልወጣ ጤና የለምና በዚህ ተረዳዱኝ ብለው ተነሱ። ብዙም ሰው ለጊዜው ከየራሱ ብሶት አንፃር እየተነሳ «ደግ ነው፣ ምሩ እንከተላለን» አላቸው። ሰውየው ደህና ሰው መሆናቸውን ያውቁ የነበሩ «ተው ወንድሜ፣ ጥላቻ ከመንግሥት ጋር ብቻ ነው። ጠላትም መንግሥት ነው። ገና ለገና ትግሬዎች መንግሥት ያዙ ብለህ መላ የትግሬን ህዝብ አትኰንን። አያምርብህም።» ብለው መከሯቸው። ፕሮፌሰሩ ግን እንዴ እጣን አጭሰዋልና ትግሬውን ብቻ ሳይሆን የሚቃወሟቸውን የገዛ ወዳጆቻቸውን ሁሉ በነገር ይዠልጧቸው ጀመር። እንዲያው ለነገሩ እንጂ እኚሁ ሰውም ሰሞንተኛ ሆነው አልፈዋል።

ሌላው እንደሳቸው የባሰበትም ሞልቷል። እኔ የዚህ አምባ ተወላጅ በመሆኔ ብቻ ጠላታቸው፣ ጨቋኛቸው መሆኔን ሊያስተምሩኝ የፈለጉ ብዙ ነበሩ። ያላወቁት ቢኖር ከሙጃሌ

ጋር አድጌ ለስሜ አንድ ግልገል እንኳ ሳይኖረኝ ካገሬ የወጣሁ መሆኔን ነው። እዚህ አገር ውስጥ ያለው ጨካኝ እዚያም በስደት ዓለም አለ።

ኢትዮጵያን እንደዶሮ አስራ ሁለት ቦታ ከፋፍለው የእያንዳንዱ ክፍል አጤ ለመሆን የልብ ምኞት ያላቸው እዚያው ከፈረንጁ አገር ብዙ ኢትዮጵያውያን አሉ። «የፈረ ልብ ይህን ያስባል» አልኩና ለነገሬ–እልባት አርጌ ዋርማ ጠላየን ቀና አደረግሁ። እኔ ኑዛዜዬን ሳወርድ በዳሱ ውስጥ ያለው ሌላው ተጋባዥ ምግብ መመገቡን አብቅቶ ጭፈራ ቀጥሏል። የእኔና አብረውኝ ያሉት ባልንጀሮቼ አይን ቢያየውም ጆሮአችን ግን ሳይሰማው ቀይቷል።

«እጐናፍር፣ ለመሆኑ ሁኔታዎች ተቀያይረው የተሻለ መንግሥት ቢመጣ ውጭ አገር ያሉት መጥተው የሚረዱን ይመስልሃል?» አለኝ ወላሌ ዥማነህ እኔን ሳይሆን ጦር ሜዳ የተቆረጠ እግሩን እያስተዋለ።

«ዋ ወንድሜ!» አልኩት ለጥያቄው መስሎ የታየኝን መልስ ለመስጠት እያሰብኩ።

«ጥያቄህ ደጃች ታከለ ወልደሐዋርያት በጣሊያን ዘመን የጠየቁትን ይመስላል። በዚያን ጊዜ እሳቸው የነበራቸው ስጋት የጣሊያን ጦር ብቻ ሳይሆን ነፃነት ሲመጣ ፈሪና ባንዳ የሚኖራቸው ቦታ ነበር። ጣሊያንን አሸንፈው እንደሚያባርሩት ስለሚያውቁ አይፈሩትም ነበር። በፈሪና በባንዳ ላይ ግን ጥርጣሬ ነበራቸው። እንደጠረጠሩትም አልቀረ ታግለው ነፃ ባወጧት አገር ፈሪ፣ ኮብላይና ባንዳ ከፍ ከፍ አሉና ትልቁን ሰው አበላሿቸው።

አሁንም እንዲህ ዓይነት ሁኔታ ዳግም ይከሰት ይሆናል ተብሎ ቢገመት ማጋነን ላይሆን ይችላል። ውጭ ያለው ኢትዮጵያዊ በአብዛኛው ውስጣዊ ምኞቱ ከማገልገል ይልቅ መገልገልን፣ ከመታገል ይልቅ በታጋዮች ትከሻ ላይ ተረማምዶ ስልጣን መያዝ፣ ከችግር ይልቅ ምቾት እስከሆነ ድረስ በጥርጣሬ ሊታይ የሚገባው ነው። በደርግ ጊዜም ሆነ በወያኔ ዘመን ለግላቸው አመቺ መስሎ ሲታያቸው ፈርጥጠው ወደ አገር የተመለሱና የሹመት ካባና ላንቃ የለበሱ ነበሩ።

ሁኔታው አላመች ሲላቸው ደግሞ እዚሁ የህዝቡን እጣ ከመካፈል ይልቅ ወደዚያው ወደባህር ማዶ ይኮበልላሉ።

በአገራችን የነበረው፣ ያለውና የሚኖረው የጭቆና መንግሥት ነው። ህዝብ የሚኖረው ለመጨቆን ነው። እናንተ ለአገር የከፈላችሁት ውድ ዋጋ ሁሉ ውጤቱ ጭቆና ነው። ያለ ጭቆና መንግሥት አይኖርም። ለዚህ ደግሞ ድህነታችን ጥሩ ዋስትና ነው። የድሃ አገርና ህዝብ እጣው በጨቋኝ መንግሥት መገዛት ነው። ይህን እስከፊ ሀቅ ስደተኛው አገር ካለው ህዝብ ይልቅ የተሻለ ያውቃልና ደህና መንግሥት መጥቶ ወደ አገሬ እመለሳለሁ የሚል አይመስለኝም። ቢል የስደት ሀዘኑን ለማፅናናት ብቻ ነው። እርግጥ ነው ስለነፃነት፣ ስለዲሞክራሲ፣ ስለእኩልነት፣ ስለመብት መከበር የማያልም የለም። እነዚህ ግን እውን እንደማይሆኑ ሁሉም ያውቃል። ለእነዚህ በግንባር የሚታገል ማንም የለማ! ሁሉም በሩቅ ተቀምጦ አካኪ ዘራፍ ባይ ነው። «ውረድ እንውረድ ተባባሉና፣ አስደበደቡት አፋፍ ቆሙና» እንደሚባለው ያለ ነው የስደተኛው ዘይቤ።

በመሰረቱ፣ ወንድሜ! ኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን ውጭ ካለው ስደተኛ የሚጠብቁት ምንም ነገር የለም። ውጭ ያለው ኢትዮጵያዊ ለአገር ጠቃሚ ከመሆኑ በፊት ልቡ ላይ የተከመረውን የፍርሀቻ ስባት አቅልጦና በአእምሮው ውስጥ ድንኳን የዘረጋውን «ከመሞት መሰንበት» የሚል ዘይቤ አፅድቶ ለራሱ የዜግነት መብት መቆም አለበት።»

«ጉበዝ!» አለ መራ ሽመል ወላሌ፣ «እንዲያው የቆየ ቅዠት እያወጋን የአያ ክብረትን ድግስ ሳንጨፍርበት አሳለፍነው! እኔ እንኳ «አህም – እህ» ብሎ እስክስ ለማለቱ እግሩም፣ እጁም፣ ወገቡም የለኝ እናንተ ግን አመለጣችሁ» ሲል ሁላችንም ቀና እያልን ዳሱንና ተጋባዡን ተመለከትን። ግብዣውም ጭፈራውም አልቆ ተጋባዥ ምርቃቱን በአያ–ክብረት ነጠላ ላይ እያወረደ ከዳሱ በመውጣት ላይ ነበር። እኛ አራቱ መራዎችም በእጃችን የያዝነውን የሸክና ጠላ እየጨለጥን ምርቃታችንን አድርሰን ለመውጣት ተነሳን።

* * *

ጥር 13 ቀን ማለዳ ከሦስቱ ባልንጀሮቼና ሲያስተናግዱኝ ከቆዩት የመራምባ ሰዎች ተሰነባበትኩና ወደ አዲስ አበባ የመልስ ጉዞዬን ጀመርኩ። ከመራምባ መንደር እስከ ፍቼ፣ ሰላሌ ድረስ የምጓዘው በእግርና በበቅሎ ሲሆን፣ ጉዞው አንድ ዠንበር ይፈጃል።

በመሰረቱ እንደ ጥንቱ ሳይሆን ዛሬ ከመርሀቤቴ አዲስ አበባ በግማሽ ቀን ውስጥ በመኪና ሽር ብሎ መግባት ይቻላል። ደርግ ከሰራው ደግ ነገር አንዱ፣ ምናልባትም በመርሀቤቴ ብቸኛው ደግ ነገር፣ በዠማ ወንዝ ላይ ድልድይ መስራቱ ነው። የዠማን ወንዝ በማንኛውም ወራት ያለ ሀሷብ መሻገር በመቻሉም መኪናዎች በጥርጊያ መንገዱ ላይ እየተንኮራኮሩ መመላለስ ጀምረዋል። ሆኖም ግን መርሀቤቴን ለሚያውቀው ከመኪና ይልቅ በእግር መጓዙ ከጭንቀት ያድናል። ጭልጥ ባለው ገደል፣ ጋራ ሸንተረር ጥግና ዙሪያ አርባ አራቱን ታቦት እየተማፀኑ በሲቃ በመኪና መጓዝ ብዙም ጤና አይሆን። የመርሀቤቴ መንገድ ለመኪና የኢትዮጵያ ቤርሙዳ ነው ቢባል ማጋነን አይሆንም። ጭልጥ ካሉ ጭልጥ ነው።

ለማንኛውም፣ ከመኪናው ጉዞ ስጋት ባሻገር እኔ እግረኛነቱን የመረጥኩበት የአባቶቼን አገር ስረግጥ ይህ የመጨረሻው ጊዜ ስለሚሆን የአገሩን አየር ለመተንፈስ፣ ውበቱን ለማድነቅ፣ የህብረተሰቡን ህይወትና ኑሮ በውስጡ ሳልፍ እያየሁ ለህሊናዬ ለማኖር እንዲያስችለኝ ነው። እድሜዬ የሽምግልና ቁልቁለትን ጀምሯል። በልጅነትና በጉልማሳነት ጊዜ የነበረው አካልም መንፈሴም ተዳክሟል። ዳግም ወደ አባቴ አገር ወደ መርሀቤቴ እመለሳለሁ የሚል ተስፋ የለኝም።

እርጅናዬና መዳከሜ ብቻ አይደለም እንደወጣሁ የሚያስቀረኝና ወደ መርሀቤቴ ከመመለስ የሚከለክለኝ። የመጨረሻ ዘመኔን ከባልንጀሮቼ ጋር በመራምባ ባሳልፍ፣ የሽምግልና ጨዋታና ምርቃቴን ለተተኪው ትውልድ ባወርድ፣ ቀኔም ሲደርስ ከመራምባ ሚካኤል ስድስት ክንድ ጉድጓድ ተቆፍሮልኝ ብቀበር ለእኔ ፀጋም፣ ደስታም፣ ረፍትም ነበር።

ይህ እንዳይሆን ግን የወጣትነት፣ የጉልማሳነትና የፍሬያማ ዘመኔን በራሴው ምርጫ አለያም የእርባ ቀን እድል ሆኖ በሰው አገር፣ በባዕዳን መንደር አሳልፌያለሁ። ይህን በማድረጌ ደግሞ ከህብረተሰቡ ህይወትና ኑሮ ብቻ ሳይሆን ከታሪኩም ራሴን አግልያለሁ። በክፉ ቀን ያላፅናናሁትን፣ ሀዘንና ደስታውን ያልተጋራሁትን ህብረተሰብ አሁን በእስተርጅና ዘመኔ መጣሁ ጡረኝ ቅበረኝ ማለት አልችልም።

ይሉኝታዬን ሽምጥጫ የእርጅና ዘመኔን አገሬ ላሳልፍ ብል እንኳ እለት በእለት የማየው የመራምባ ሰው እኔነቴንና ዘመኔንም በከንቱ በሰው አገር ማሳለፌን እያስታወሰ የባሰ ፀፀትና ጭንቀት ያበዛብኛል። ባልንጀሮቼን፣ እንባቆምን፣ ወላሌንና ዞማለምን ባየሁ ቁጥር «በክፉ ቀን ጥለኸኝ ብትኮበልልም በመጨረሻው ከእኛ የተሻለ ያገኘኸው ምንም ሳይኖር ዞረህ ዞረህ ባዶ እጅህን መጣህ።» የሚሉኝ ይመስለኛል። የትዝብት አይኖቻቸውን እፈራለሁ። እነሱ ባሉበት መንደርና አገር በእስተርጅና ጊዜያቸው ራሳቸውን ቀና አድርገው ሊራመዱ የሚችሉበት፣ አንቱ የሚባሉበት ገድል ሰርተዋል። እኔ የዚህ ዓይነቱ መፅናኛና ኩራት የለኝም።

የፍሬያማነት ዘመኔን ባዕዳንን ተጉራብቼ በባዕዳን አምባ በባዕድነት እንደኖርኩ የመጨረሻ ቀኔንም በዚያው ያለ አጣዋች፣ ያለጧሪና ቀባሪ አሳልፍ ዘንድ የተገባ ነው። የእርባ ቀን እድል ሳይሆን በልደት፣ በፀጋና በክብር የወረስኩትን ኢትዮጵያዊነት በማጉደሌ የገጠመኝ ነው።

የበቅሎ ጉዞዬን ወደ ፀሐይ መውጫ ስቀጥል መርሀቤቴ ላይ እየነጋ እኔ ላይ እየጨለመ ይሄዳል። የመራ–ልጅነቴ ይህም በክብር አልብሶኝ የነበረው የኢትዮጵያዊነት ሸማ ከላየ ተገፎ እየሄደ ርቃኔን በመሆኔ ለራሴ ከፋኝ አዘንኩ። የእንባዬንም መውረድ ልቆጣጠረው አልቻልኩም። ኦ–ኢትዮጵያዊነት ብዬ ለራሴ አነባሁ።